ትውልድ መክሸፍን እንደሚፈልገው አድርጎ እንዲቀጥል ባለማድረጉ ስላለው ክሽፈት ካልሆነ በቀር ስለኢትዮጵያ ታሪክ ክሽፈት ጻፉ፤ተመራመሩ ለማለት አይቻልም። እነዚህ በአብዛኛው ራሱ ታምራት ለሚለው የ"ምናባዊት ኢትዮጵያ ማኅበረሰብ" አለመፈጠር ምክንያት ሆነው ክሽፈው ያክሸፉ ናቸው።እንዴት ሆኖ በእኔ ሞት የኢሕአዴግ የሽግግር መንግስት ክሽፈት ከኢትዮጵያ መክሸፍ ትንተና ጋር የሚያያዘው።ኢሕአዴግ የሚባለው መጥፎ ወንበሩ ላይ ሲቀመጥ የኢትዮጵያ መክሸፍ የለየለት ሁኔታ ነው የተፈጠረው። ኦነግ እና ወያኔ ሽግግር በሚባለው ዘመን ተጣልተው በየፊናቸው ባይሄዱ ኖሮ ክሽፈት አይኖርም ነበር ለማለት ከሆነ ከባድ ባልት ነው።

ታምራት "ስለኢትዮጵያ ሲባል ለምን ሐበሻ ልቡ ይፈሳል?" ሲል የጠየቀውን ጥያቄ ኢትዮጵዊነት ገብቶት ነው ብዬ ባስብ ኖሮ እወድለት ነበር። አንዱ የሐበሻን ልብ የሚያፈሰው እንደዚህ እሱ እንደጻፈው ያለ የተሳከረ ጽሑፍ መሆኑን ልነግረው እወዳለሁ። አገር ወዳድነት ሌላ ቦታ የለውም ከመንደርተኝነት መውጣት ነው። ከመንደርተኝነት የወጣ ሰው ስለአገር ወዳድነት ማብራራት የግድ ካለበት እንደሩሲያዊው ሌርሞንቶብ "I love my country, but with a strange love. My reason cannot fathom it." ማለት ብቻ ይበቃዋል። ሌላው ሃተታ በማያንሰራራ ሁኔታ ይበልጥ እንድንክሽፍ ማጨናበር ነው።





# ምዕራፍ ፱
# የትችቶች ትችት

*መግቢያ*

ስለትችቶቹ መናገር ግዴታ መስሎ ስለታየኝ ነው እንጂ ፍላጎቱ የለኝም፤ በመሠረቱ በአንድ መጽሐፍ ላይ ትችት ለመስጠት ብቃቱ ያላቸው ሰዎች ደረሲውንም አንባቢውንም ለማስተማር የሚችሉ ናቸው፤ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚታየው ግን ፊደል የቆጠረ ሁሉ ማንኛውንም መጽሐፍ ለመተቸትና ከሱ ባልተሻሉ አድናቂዎቹ ‹‹አበጀህ የኛ ልጅ!›› ለመባል የሚጠብቅ ሞልቷል፤ እነዚህ ሰዎች የሚተቹትን መጽሐፍ በጥንቃቄ ማንበብ አይጠበቅባቸውም፤ ያልታደሉት አድናቂዎቻቸው ምንም ነገር ቢወረውሩላቸው እልል እያሉ የሚቀበሉ ናቸው፤ እነዚህን ወጣቶች ለእነዚህ ሰዎች መተው ትክክል አይመስለኝምና ያንን በመጠኑም ቢሆን ለመቋቋም ይጠቅማል በማለት ነው፤ አንዳንዶች ተቺዎች በቅድሚያ የእኔን ጠባይ በማጥላላት እነሱ ለራሳቸው ተአማኒነት ለማግኘት ይጥራሉ፤ ምናልባትም በቅድሚያ ማከላከያቸውን ማዘጋጀታቸው ይሆናል፤ እኔ ትችቶችን መቀበል መቻሌን ለማሳየት አንድ የቆየ ምሳሌ በማስረጃነት አቀርባለሁ፤ ሆኖም የእኔ ትችትን መቀበል ወይም አለመቀበል ዋጋ የለውም፤ ትችቱ የማይረባ ከሆነ ይበልጥ የሚጎዳው ማኅበረሰቡን ነው።

በ1966 ዓ.ም. አንድ ትንሽ ጽሑፍ ኢትዮጵያዊነት፤-ልማት በኅብረት በሚል ርእስ አሳትሜ ነበር፤ ዓላማዬ አብዮት የሚባለው ጎርፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደጥፋት እየመራው

ስለነበረ የእብደት ግርግር ከመሰለኝ መስመር ሰዎችን ለማዳን የበኩሌን አስተዋጽኦ ለማድረግ ነበር፤ ዓላማዬን በትክክል የተረዱ የእብደት ግርግሩ ደጋፊዎች፣ አራት ደቂቃን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን የአዲስ ዘመን ጋዜጣን ሰፋፊ ገጾች የሚሞላ ትችት ጻፉ፤ መጽሐፉን ሳይሆን ጸሐፊውን ልባሼ እንዳይሸጥ አድርገው በናርና በሐሰት ቃላት ደበደቡኝ፤ አንዲትም ቃል አልመለስሁላቸውም፤[69] ዛሬ ይህንን መናገሬ ብዙ ሰዎች በሥራዬ ላይ ትችት ሲቀርብብኝ የማልወድና የምቆጣ እያደረጉ ማቅረባቸውን ለማስተባበል ነው።

ትችት አይወድም የሚሉ ሰዎች የአደባባይ ሰው መሆን ምን ማለት እንደሆነ የማያውቁ ናቸው፤ በአገርና በሕዝብ ጉዳይ በአደባባይ የሚናገርና የሚጽፍ ሰው በግለኛነት ስሜት ሊታማ አይገባም፤ የሚያነሣቸው ጉዳዮች ሁሉ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለሚነኩ የሚናገረውንና የሚጽፈውን የማይወዱለት፣ እንዲያውም የሚቃወሙት እንደሚኖሩ ካላወቀ የአእምሮ ጉድለት ያለበት ነው፤ አንዳንድ ሰዎች ግን የአደባባይ ሰው የተናገረውን ለመተቸት እነሱ መብት ሲኖራቸው እሱ መልስ መስጠት እንደሌለበት ያስባሉ፤ ይህ ትክክል አይደለም፤ ሥነ-ምግባር ሊያስተምሩኝ ይቃጣቸዋል፤ ነገሩ ይገባኛል፤ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ይሉኝታ የተቀላቀለበት ጉዳይ ነው፤ አለመመለሴን ጨዋነት አድርገው ይቆጥሩታል፤ አለመመለሴ ግን በትእግስትና በፍርሃት፣ በጨዋነትና በብልግና መሀከል ያሉትን ልዩነቶች በይሉኝታ መሸፈን እንደሚሆን አይገነዘቡም፤ መክሸፍን እንደባህል የጫነብን እንዲህ ያለው

[69] ከአራቱ ደቂቃን ምሁራን ሦስቱ ዛሬ በሕይወት የሉም፤ ነፍሳቸውን በክብር ያኑርላቸው፤ ከሦስቱ አንዱ ከመሞቱ በፊት ሰው ልኮ ይቅርታ እንደጠየቀኝ መናገር አገደዳለሁ፤ አንዱ አሁንም ከደቂቅ ምሁርነት ሳይወጣ አለ፤ በጊዜው እኔ ተናድጄ መልስ ብሰጣቸው ኖሮ ሊጎዳቸው ይችላል የሚል ጥርጣሬ ነበረኝ፤ ሰዎች መልስ እንድሰጥ ቢወተውቱኝም በዚህ ምክንያት ምንም ሳልል ቆየሁ፤ የተጻጻተው ከአራቱ አንዱ ብቻ ቢሆንም፣ እሱም ቢሆን በጻዕረ ሞት ስር በነበረበት ጊዜ ነው፤ ስሕተታቸውን ቢረዱትም አንዳቸውም እንኳን በአደባባይና በግልም ይቅርታ ለመጠየቅ ወኔ ሳያገኙ መቅረታቸው ያሳዝነኛል፤ ነገር ግን በቀን በቀን በቢራ ኀሊናቸውን ለማጠብ እንደሚሞክሩ ተነግሮኛል።





አመለካከት ነው፤ እውነትን ለመቀበል ካልተዘጋጀን አሁንም ከመክሸፍ አናመልጥም፤ ውሸታሞችንና አስመሳዮችን፣ ባለጌዎችንና የሰውን ስም ማጥፋት ብቻ ሥራቸው ያደረጉትን ልናልፋቸው አይገባም፤ እነሱ ይሉኝታ የሚባል ነገር አያውቁም።

ለሌች እንደሚመስላቸው እኔ መማር አላቆምሁም፤ ትችቱ የሚያስተምረኝ ከሆነ እማርበታለሁ፤ የጎደለውን የሚሞላልኝ ከሆነ እሞላበታለሁ፤ የወጣቶችን አስተሳሰብ የሚያበላሽ መስሎ ሲታየኝ ያለይሉኝታ እመልስላቸዋለሁ፤ በጉዳዩ ላይ ለመግፋትና ክርክር ለመክፈት ከሞከሩ እሰየው፤ ከዚያ በታች ከሆነ ነጥሮ ወደባለቤቱ እንዲመለስ አደርገዋለሁ፤ ስለመክሸፍ በተጻፉት ትችቶች ላይ የራሴን ትችት በአጭሩ ለማቅረብ የፈለግሁበት አንድ ጥሩ ምክንያት አለኝ፤ ብዙ የኢትዮጵያ ወጣቶች በአስመሳይ ጮሌዎች ጥላ ስር ወድቀዋል፤ በእርግጥ ወድቀዋል፤ ወጣቶቹ እነዚህ አስመሳይ ጮሌዎች የተናገሩትን ሁሉ ያለምንም ጥያቄ ሳያኙ መዋጥ ባህል አድርገዋል፤ ይህ ክፉ በሽታ ነው፤ የአንድ ትውልድን የአእምሮ ንቃትን የሚያከሽፍ፣ማሰብን የሚያኮላሽና ወደሀሳብ ጥገኝነት የሚያስገባ የአእምሮ ሎሌነት ነው፤ ይህንን በይሉኝታና በዝምታ ለማለፍ አልፈልግም፤ ስለዚህም ወጣቶቹን ከእነዚህ አስመሳይ ጮሌዎች ለማዳን እውነትን ተመርኩዤ አጋልጣቸዋለሁ፤አጋልጣቸዋለሁ ማለት የቁጭት አነጋገር ይመስላል፤ግን ከእውነቱ ጋር አጋጫቸዋለሁ ማለቴ ነው።

## *አንድ በማዕርጉ በዛብህ ትችት ላይ*

በመጀመሪያ የማቀርበው የማዕርጉ በዛብህን ትችት ነው፤ አንባቢ የማዕርጉን ትችት ከአነበበ በኋላ የሌሎቹን ለማንበብ ሚዛን የሚኖረው ይመስለኛል፤ ማዕርጉ መጽሐፉን በሚገባ አንብቦታል፤ መልእክቱን በቅን መንፈስ ተረድቶታል፤ በትምህርቱም በሥራ ልምዱም ለብርቅ ከሚታዩት የዱሮ ተማሪዎች አንዱ ነው፤ ለጸፈውም ትችት ከመጽሐፉ አስፈላጊ የመሰሉትን ማስረጃዎች ጠቅሶአል፤ ቅሬታውን የገለጸው የውጭ አገር ምሁራንን በተመለከተ ነው፤ የሚከተለዉን ይላል፡ --

ይህ በሌለበት ሁኔታ ስለኢትዮጵያ በውጭ ምሁራን የተፃፉትን መረጃዎች መሠረት አድርጎ መፃፉ ትክክል አይደለም ማለቱን መቀበሉ አስቸጋሪ ይሆናል። ዕውቀት ዓለም አቀፋዊ ነው። መላው የዓለም ምሁራን የሚጽፉት፣ የሚመራመሩት፣ ይበልጥ እያጠኑ ሙያዎቻቸውን የሚያዳብሩት ከዚሁ የጋራ ንብረት በሆነው ዓለም አቀፋዊው የዕውቀት ክምችት ላይ በመመስረት ነው። በየክፍለ ትምህርቱ የተለያየ ባህሪ ምክንያት የምርምርና የጥናት ጥበቦቹ በመጠኑ ይለያዩ ይሆናል እንጂ በአጠቃላይ ካለና ከተከማቸ ዕውቀት ወይም መረጃ መዋዋሱ በዚያ ተመስርቶም የበለጠና ያደገ ሥራ መስራቱ ዓይነተኛ የአካዳሚካዊ ሥራ ባህሪ ይመስለኛል።

ማዕርጉ እንዳለው እውቀት ድንበር የለውም፤ ዓለም-አቀፋዊ ነው፤ ማንም ሰው፣ ከየትም አገር የአእምሮው ዝንባሌ ወደመራው ተሰማርቶ እውቀትን መሻት፣ መመርመርና ያገኘውን ለማሰራጨት ሙሉ መብት አለው፤ ይህ ለክርክር አይቀርብም፤ ማንም ሰው ስለሌላ የራሱ ያልሆነ ሕዝብ ታሪክና ባህል አጥንቶና ተመራምሮ ለራሱ ሕዝብ እውቀት ማዳበሪያ የሚሆን መጽሐፍ ማሳተም መብት አለው፤ ይህ ጥያቄ ውስጥ አይገባም፤ ይህንን የሌላ ሕዝብ ታሪክና ባህል ለራሱ ወጣቶች ማስተማር መብቱ ነው፤ እኔ ጥያቄ ያነሣሁትና ተገቢ አይደለም ያልሁት የውጭ ሰዎች ማጥናታቸውንና መጻፋቸውን አይደለም፤ ለራሳቸው ሰዎች ማስተማራቸውንም አይደለም፤ የኔ ችግር የውጭ ሰዎች የኢትዮጵያን ወጣቶች አእምሮ የማነጹን ተግባር ለሌሎች ለባህላችን ባዕድ ለሆኑ ሰዎች ማስረከብ አይገባም የሚል ነው።

ከዚያም በላይ አጠቃላይ እውቀትንና የተለየ እውቀትንም ለያይተን ማየት ያሻናል፤ ከአንድ አገር ሰዎች ከራሳቸው የሚፈልቅ መረጃ ወይንም እውቀት ከዚያ አገር ሕዝብ በራቀ መጠን ጉልበቱ ይቀንሳል፤ የአገሩ ሰዎች መረጃውን ከሌላው የበለጠ እንደልባቸው የሚያገኙ በመሆናቸውና መረጃውንም በመተርጎሙና በማጠናከሩ በኩል የተሻለ በመሆኑ የልጆቻችንን





አእምሮ ለመቅረጽ የአገር ሰው ይሻላል ማለቴ ነው፤ በሌላ በኩልም አንዱ የመክሸፍ መስረጃ አድርጌ ለማቅረብ የሞከርሁት በኢትዮጵያ እውቀት ምሥጢር እየሆነ እንዳይሰራጭ መደረጉን ነበር፤ ከዚያም በላይ የእኔ ተቃውሞ እኛ ስለኢትዮጵያ ታሪክ የምናነበው በውጭ አገር ሰዎች የተጻፈውን፣ አስተማሪዎቻችንም የውጭ አገር ሰዎች መሆናቸውን ነው፤እንዴት ነገሩ ሁሉ እንደሚጠናገር አንድ ምሳሌ ብቻ ላቅርብ፤ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ አንድ ስብሰባ ላይ ስለአጼ ምኒልክ ስንነጋገር አንዱ የታሪክ ሊቅ አንድ ለኢትዮጵያ የማይበጅ የመሰለኝን ነገር ተናገረ፤ ማስረጃው ምን እንደሆነ ሲጠየቅ በአጼ ምኒልክ ዘመን የነበረውን የእንግሊዙን አምባሳደር ጠቀሰ፤ እንዴት ብለህ አጼ ምኒልክ ተናገሩ ያልከውን የእንግሊዙን አምባሳደር እንደማስረጃ ታቀርባለህ ሲባል አምነዋለሁ ብሎ መለሰ፤ እንግዲህ ምን ይባላል? የብሪታንያን ጥቅም በሚመለከት ተአማኒነትን አግኝቶ የተሾመ አምባሳደርን ቃል ተቀብሎ ለኢትዮጵያ ታሪክ በማስረጃነት መጥቀስ ይከብዳል፤ ኢትዮጵያን በሚጠቅም ጉዳይ ላይ ቢሆን ደህና፣ ኢትዮጵያን በሚጎዳ ጉዳይ ግን መሸጦነት ይሆናል።

የ‹ታሪክ ተመራማሪ› ነኝ ለሚለው ሰው በሰጠሁት ትችት ላይ የሚከተለውን ብዬ ነበር፡-

*‹የውጭ ሊቃውንቱ ጥናት ልዩ ጥቅም ቢኖረውም ባይኖረውም ለራሳቸው ሲሉ የሚያደርጉትን ጥናት በጭራሽ ልንቃወም አንችልም፤ የምንቃወመው እነሱ እኛን እንደፈለጉ አድርገው ሊቀርጹን የሚያደርጉትን ሙከራ ነው፤ እኛም እንደጥቁር ሰሌዳ የእነሱን ነጭ ጠመኔ የባሕርይ አድርገን መቀበላችንን ነው።›*

በምእራባውያን ሊቃውንትም መሀከል በዱሮዎቹና በአሁኖቹ ትልቅ ልዩነት አለ፤ የዱሮዎቹ ግእዝ ሳይቀር እየተማሩ በግእዝ የተጻፉትን ሁሉ በየቋንቋቸው ይተረጉሙ ነበር፤ እነዚህ የኢትዮጵያን ታሪክ ያጠኑ የነበረው የየሀገራቸውን ምሁራን እውቀት ለማበልጸግ ነበር፤የኋለኞቹ ምንደኞች ናቸው፤እንኳን

ግእዝ አማርኛም አያውቁም ነበር፤ በዚህ ረገድ ከእኛ ወጣቶች የሚሻሉም አልነበሩም፤ እንግዲህ እነዚህ ነበሩ አስተማሪዎቻችን የሆኑት፤ እኔ የምቃወመው ሁሉም ነገር እያለን ከሰው በታች መሆናችንን ለማስመስከር ብቻ የምናደርገውን የውርደት መንገድ ነው፤ እንኳን ታሪካችንን ቋንቋችንንም ሲያስተምሩን ነበር፤ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛን ሲያስተምር የነበረው አንድ የህንድ ቄስ ነበር፤ በተፈሪ መኮንን ደግሞ አማርኛ አስተማሪያችን የፈረንሳይ ቄስ ነበሩ፤ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ዋናው የታሪክ አስተማሪ የፕሮቴስታንት ካህን ነበረ፤ ከሃይማኖቶቻቸው ጋር ጠብ የለኝም፤ ከእውቀታቸው ጋርም ጠብ የለኝም፤ የኔ ችግር ራሳችን ፊደል ያለን ሕዝብ፤ የራሳችን የጽሑፍ ምንጮች ያለን ሕዝብ እንዴት ሌሎች ከኛው ተምረው የእኛው የራሳችን አስተማሪዎች ይሆኑናል?

ሌላም ችግር አለበት ስለራሳችን የማወቁን ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ወጣቶች አእምሮና ኅሊና በፈለጉት መንገድ እንዲቀርጹ ለውጭ ሰዎች መስጠታችን ነው፤ስለዚህም ልጆቹን በብስኩት እያታለሉ ሃይማኖታቸውን ሳይቀር እንዲለውጡ ተደረገ፤[70] ከዚያም በላይ የጎሣን ስሜት በመቀስቀስ እነዚህ የሃይማኖት አስተማሪዎች ኢትዮጵያን የሚጎዱ ሆነዋል፤ ይህንን ሁሉ በአንድ ላይ በማየት የመክሸፉን መንገድ እንዳፋጠኑልን በተጨባጭ ማስረዳት ይቻላል።

## *ሁለት በታምራት ነገራ ሐተታ ላይ*

ስለታምራት ጽሑፍና አጻጻፍ የክፍሉ ሁሴን ጽሑፍ በቂ ነበር፤ ሆኖም በበኩሌ ልገልጻቸው የምፈልጋቸው ነጥቦች አሉና እኔም ትንሽ እጨምርበታለሁ፤ ብዙ ነገሮችን ለማስተካከል ብፈልግም ታምራት በመጀመሪያው ፓራግራፍ ላይ ሳያውቀው የጻፈው ልቤን (አእምሮዬን ሳይሆን) ነክቶታልና ብዙውን ነገር ለማለፍ በተቻለኝ መጠን እጥራለሁ።

[70] ይህንን ማለት የሃይማኖት ነጻነትን መጋፋት የሚመስላቸው ሰዎች ይኖሩ ይሆናል፤ ግን የሰውን ድካም፣ ደህነቱን ከለላ አድርገው እምነትን ማስለወጥ የሰብአዊ መብትን መጣስ ነው ብሎ መከራከር ይቻላል።





ማንም ሰው ከታምራት ነገራ ጽሑፍ ለመረዳት እንደሚችለው ታምራት ነገራ የተማረና የተመራመረ የለብለብ ትውልድ[71] አባል ነው፤ ከራሱ ጽሑፍ እንደምንገነዘበው ስለጋዜጣ ብቻ ሳይሆን ስለመጻሕፍት አጻጻፍ ደረጃና ሚዛን በሁለት እጆቹ የጨበጠ ምሁር ነኝ ባይ ነው፤ የግራና የቀኙን የፖሊቲካ መስመር የማውቅ ፖሊቲከኛ ነኝ ባይ ነው፤ ከሁሉም በላይ ታምራት የሚታየውን የማያይ፤ የማይታየውን የሚያይ ልዩ ስጦታ ያለው ሰው ነኝ ባይ ነው፤ ከዚህ በላይ የተናገርሁት ሁሉ ታምራት ስለራሱ በተለያዩ መንገዶች በጽሑፉ ከገለጸው ተነሥቼ ነው፤ ክፍሉ ሁሴን ደግሞ በሰጠን መረጃ «የኢትዮጵያዊ አእምሮ» በሚል ርእስ[72] መጽሐፍ እያዘጋጀ መሆኑን አውቀናል፤ እናያለን! ብለን እንለፈው፤ ምኞት አይከለከልምና።

በታምራት ጽሑፍ በመጀመሪያው መስመር ላይ የሚያጋጥመን ግልጽና ጉልህ የማስተዋልና የጥንቀቄ ግድፈት የሰውዬውን ማንነት ፍንትው አድርጎ ያሳየናል፤ ታምራት በራሱ ላይ የጫነው ችሎታና እውነተኛው ችሎታው እንደማይጣጣሙ ጽሑፉ ማስረጃ ነው፤ ታምራት እንዳየው የመጽሐፉ ርእስ «ክሽፈት እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ» የሚል ነው፤ የመጽሐፉ ርእስ እንዲህ አልተጻፈም፤ የመጽሐፉን ርእስ እንዲህ አድርጎ መሳቱ፥ ፊደሎቹን አጣርቶ የማያውቅ ጋዜጠኛ ሆኖ አይመስለኝም፤ የእውነትንና የሐሰትን ሚዛን የያዘው እሱ ብቻ መስሎ ስለሚታየው ማንም አይጠይቀኝም በማለት አድናቂ ወጣት አንባቢዎቹን በመናቅ ነው፤ በምንም መመዘኛ ርእሱን በትክክል ሳያውቅ ስለአንድ መጽሐፍ ሐተታ ለመጻፍ የተነሣ ሰው ክፍሉ እንዳለው የሚለውን አያውቅም።

[71] የለብለብ ትውልድ የምለው የትምህርት ዋጋ ከተቀነሰ በኋላ፤ የዩኒቨርሲቲ ትርጉም ከተለወጠ በኋላ የመጣውን ነው፤

[72] የተባለው በእንግሊዝኛ <The Ethiopian Mind> ነው፤ ሁለት ይሁዲዎች <The Arab Mind> በሚል ርእስ ሁለት መጻሕፍትን ጽፈዋል፤ አረቦችና እኛ የምንመሳሰልባቸው ብዙ ነገሮች ስላሉ ያንን መገልበጥ አያዳግትም፤ ነገር ግን አዲስ ነገር አስቦ ከሆነ ኢትዮጵያዊነትንም አእምሮንም ለማወቅ ዕድሜውን በሙሉ ካልሰጠ (ያም ከበቃው) የእንቁራሪትዋ ዕድል ያጋጥመዋል፤ ነገሩን ለተገነዘበው ሰው በጣም ያስቃል።

በሦስተኛውና በአራተኛው ፓራግራፎች ላይ መጽሐፉ አእምሮውን እንደኮረከረው በጣም እውነተኛ በሚመስል አነጋገር ይገልጻል፤ በነዚህ ፓራግራፎች ላይ ያነሳቸውን ከባድና ጥልቅ ሀሰቦች ገና ብቅ እንዳሉ ድራሻቸውን ማጥፋቱ አእምሮው እንዲህ ያሉትን ከባድና ጥልቅ ሀሳቦች የማጠንጠንና የማስተናገድ ልማድም ሆነ ችሎታ እንደሌለው ያሳያል፤ ቶሎ ያዳልጠውና ወደሚያውቀው ጭቃ እያፈሰ መለጠፍ ይወርዳል፤መጽሐፉ ከጫረበት ሀሳብ፣ ከፍተኛ የሕይወትን መሠረት ከሚነካ ሀሳብ ወደስድብ ይወርዳል፤ እንደገናም ለምሳሌ ‹‹ፖሊቲካዊ ሕይወት **ለካ ከበቀለበት አፈር ሲወጣ ምንም ትርጉም የለውም**፤›› ይልና አዳልጦት ይህንን ብልጭ ያለለትን ትልቅ ቁም-ነገር ጥሎ ወደስድብ ይሸጋገራል፤ ሲያዳልጠውና ሲወድቅ በጭራሽ አይሰማውም፡

ታምራት በመጽሐፉ ውስጥ አዲስ ነገር የለም፤ ስንለው የቆየነው ነው ይላል፤ ስለዚህም የጠላው መስፍን መጻፉን ይመስላል፤ እንዲያውም ታምራት ስለመጽሐፉ ሐተታ ለመጻፍ ተነሥቶ ሲጠጥርበት ጊዜ መስፍንን መውቀጡ ወይም በመስፍን ላይ ከራሱ ላዩ እየፋቀ ጭቃ መለጠፉ ቀላል ሆኖ አግኝቶታል፤ ትዝብት ላይ የጣለውም ይኸው ነው፤ ለምሳሌ ከመጽሐፉ ጋር በማይገናኝ ጉዳይ ገብቶ የወያኔ ጠበቃ በመሆን እኔ የማላምነውንና ያልወጣኝን ነገር ያልተጠየቀ የሐሰት ምስክርም ሆኖ ይናገራል፤ የወያኔን እኩይነት እናገራለሁ፤ ነገር ግን ኢትዮጵያዊነታቸውን በማንኛውም ቦታ፣ በማንኛውም ጊዜ ተጠራጥሬ አላውቅም፤ ለእኔ ኢትዮጵያዊነቱን የሚጠራጠረው ታምራት ነገራም ኢትዮጵያዊ ነው፤ የወያኔ ጠበቃ መስሎ በመታየት አምስት መቶ ሜትር ካሬ ለማግኘት ከሆነ እነሱ ስለሚያውቁ ከጅምሩ የከሸፈ መረጃ ነው፤ ይህንን ሐሜት ወይም ውንጀላ ከጥቂት ዓመታት በፊት ፖል ሄንዜ ከሚባለው የሲአይኤ ሰላይ ጋር ስንነጋገር ለጥፎብኝ ስለነበረ ከከረረ ክርክር በኋላ ‹‹አንተ ነገም ሆነ ተነገ ወዲያ ወደአገርህ ትሄዳለህ፤ መለስና እኔ በጋራ መሬታችን እንቆያለን፤ አንተ ከሁለታችንም ውጭ ትሆናለህ፤›› ብየው ስለነበረ ምናልባት





ታምራት ከፖል ሄንዜ የተማረው ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አሳድሮብኛል፤ ምን ምን እንደሚሸት አዋቂው ታምራት ነው፡፡

በጣም የሚያሳዝነው አንድ ተማርሁ፤ ሌሎችንም አስተምራለሁ ብሎ የሚንቀሳቀስ ሰው ‹‹ሰው›› መሆን አቅቶት ሲንገዳገድ ማየት ነው፤ የታምራትን አእምሮ መንደርተኛነት ጠርንፎ ስለያዘበት ከፍ ብሎ በሰው ደረጃ ምንም ነገር ማየት የማይችልበት ሁኔታ ላይ የደረሰ ይመስላል፤ ለዚህ ነው እኔንም ለብቻዬ እንደግለሰብ ሳይሆን ‹‹ከመሰሎቼ›› ጋር እያለ የባጥ የቆጡን የሚቀባጥረው፤ ራሱን ሰው ቢየደርግ እኔንም እንደሰው ለማየት ይችል ነበር፤ እንዲያውም አንዳንዱን የመጽሐፉን ክፍል ሌሎች ሰዎች እንደጻፉልኝ ሳያፍር ያናገራል፤ የመንደረተኛነት ሕመም በሰው ደረጃ ትዝብት ላይ ይጥላል፡፡

ሌላው የመንደረተኛነት ሕመም እውነትንና እምነትን መለየት አለመቻል ነው፤ ከነፖል ሄንዜ የተማረውም ሊሆን ይችላል፤ ለመሰሎቼና ለእሱ ዓይነት ‹‹የኢትዮጵያ አማኞች›› እያለ ከማላውቃቸው ሌሎች ጋር ያጣምረኛል፤ ለመሆኑ የኢትዮጵያ አማኝ መሆን ምን ማለት ነው? ኢትዮጵያን እሱም ሆነ ፖል ሄንዜ በሚያይበት ዓይን አላያትም፤ ኢትዮጵያና እኔ እንደእሱ ከውስጥና ከውጭ ሆነን የምንገናኝ አይደለንም፤ አሜሪካ ለታምራት እምነት እንደሆነው ኢትዮጵያ ለእኔ እምነት ብቻ አይደለችም፤ ኢትዮጵያ ለእኔ ህልውና ነች፤ በህልውናና በእምነት መሀከል ትልቅ ልዩነት አለ፤ ካርል ማርክስ (ቀኝ-ዘመሙ ፈላስፋ!) ‹‹ህልውና ከእውቀትና ከእምነት ይቀድማል፤›› ይላል፤ ታምራት የአሜሪካ አማኝ ስለሆነ (ከመሰሎቹ ጋር አልልም፤) እኔንም እንደሱው የኢትዮጵያ አማኝ ሊያደርገኝ ይፈልጋል! እኔ እዚያ ታች አልወርድም፤ ሁሌም ለጠላትም ሆነ ለወዳጅ ኢ ት ዮ ጵ ያ ዊ ነኝ፤ መርጬ አይደለም፤ ታምራት የተረተበትን የቆዳዬንም ቀለም መርጬ አይደለም፤ እኔነቱ ነው፡፡

ታምራት ‹‹ግብር›› የሚለውን ቃል ‹‹አስገራሚ›› ይለዋል፤ **ሲተረጉመውም፣‹‹ማንበርከክን፤ማስቃየትን፤አገር ማስፋፋትን፤ ገቢ ከመሰብሰብ ጋር አዋህዶ የያዘ አስገራሚ ፖለቲካዊ ቃል ነው፤..››** ይለናል፤ አይ አለማወቅን – አለማወቅ! ለእንግሊዝኛው ትርጉም

የሚሆነውን ቃል ያውቅ ይሆን? እሱ በሚኖርበት አገርስ በተግባር እንዴት እንደተተረጎመ አስቦበት ይሆን?ለማናቸውም ስለአስገራሚው ቃል ሊቃውንቱ የሚሉትን እስቲ እንስማ፡--

1. **ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፤ (ከሳቴ ብርሃን ተሰማ፤) የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡--**

  **ገበረ** ማለት ስለመሬቱ ለልዩ ልዩ ሥራ የተመደበ ግብርን ለመንግሥት በገባር መሬት የማር ግብርን ከፈለ፤ በቤተ ክርስቲያን የሰሞን ግብርን ገበረ …

  **ገባር** ማለት በርስቱ፣ በመሬቱ ለንጉሥ፣ ለመስፍን፣ ለመኮንን፣ ለመልከኛ የሚገብር፣

2. **ደስታ ተክለ ወልድ፤ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡-**

  **መገበር** ግብር መስጠት፣ ማስቀረጥ፣ መታዘዝ

**ግብር** የማይቀር ግዴታ ነው፤ ለአማርኛው ግብር የእንግሊዝኛ መገላጫዎቹ ቃላት (tribute፣ duty፣ tax፣ toll levy፣ impose) ታምራት አማርኛውን እንዳስጮኸው የእንግሊዝኛውን ቃላት እናስጩሃቸው ካልን የሚከለክል የለም!

የታምራት አስገራሚ ቃል ከየት እንደተገኘ የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው፤ የውጭ አገር ሰዎች ቋንቋውን ባለማወቃቸው ገባር ማለት መሬት የሌለው፣ ጭሰኛ እያሉ ጽፈዋል፤ የዘመኑ ኢትዮጵያውያን ምሁራንም ያንን ተከትለው ጽፈዋል፤ አስተምረዋል፤ እውነቱ ግን ተቀራኒው ነው፤ **መሬት የሌለው ሰው ገባር ሊሆን አይችልም፤ ገባር ጭሰኛ አይደለም፤** ጭሰኛም ገባር አይባልም፤ ገባር የሚለው ስያሜ በአሁኑ ጊዜም አለ፤ ባለመሬቶች ግብር ይከፍላሉ፤ በጥንቱ ሥርዓት ግን እንደዛሬ ግብር በጥሬ ገንዘብ አይከፈልም ነበር፤ የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ወታደሮችና ተከታዮችም እንደዛሬው በጥሬ ገንዘብ ደመወዝ አይከፈላቸውም ነበረ፤ የአገባበሩ ሁኔታ ተለወጠ እንጂ ዛሬም ሆነ ትናንት ግብር መክፈል ወይም መገበር ግዴታ ሆኖ ቀይቷል፤ ታምራት





የአሜሪካን የአገር ውስጥ ገቢ ቢሮ ቢጠይቅ በሚገባ ያስረዱት ነበር፤(ሳይገባው ቀርቶ ነው እንጂ በያመቱ ረጅም የመገበሪያ ሰነድ እየሞላ ለአገር ውስጥ ገቢ ይገብራል፤ ለለዚያ … ውጤቱን ያውቀዋል፤ የአሜሪካንን የአገር ውስጥ ገቢን ጂራፍ ባይቀምሰውም ሳይሰማ መቅረቱ ያለበትን የመረጃ ቀዳዳ ያሳያል!) ለማናቸውም በኢትዮጵያ ዱሮ ጥሬ ገንዘብ ባልነበረበት ጊዜ አባቶቻችን ግሩም የሆነ ዘዴ ፈጥረው ነበር፤ መንግሥት ከገበሬዎች ግብር በጥሬ ገንዘብ ሰብስቦ ለሠራተኞቹ በገንዘብ ደመወዝ መክፈል አይችልም ነበር፤ ስለዚህም አቋራጭ መንገድ ተፈጠረ፤ ግብር ከፋዩን ገበሬ ከደመወዝ ተቀባዩ የመንግሥት ሠራተኛ ጋር በቀጥታ በማገናኘት ገበሬው የተወሰነ እህል እንዲሰጥ ይደረጋል፤ እየቆየ ጉልበተኞቹ ከሥርዓት ውጭ ገባሮቹን (ማለትም ግብር ከፋዮችን) የመፍጨትና ቤት የመሥራት ዓይነት የጉልበት ሥራ እንደግዴታ ይጭኑባቸው ነበር፤ ዘዴው ለዘመኑ ጥሩ የሚባል ነበር፤ ነገር ግን እንደማናቸውም የሰው ሥርዓት እየተበላሸ፤ዓላማውን ስቶ ነበር፤ ስለዚህም ነፍጠኞች በገባሩ ላይ ብዙ በደል ይፈጽሙ ነበር፤ እንደዛሬው ሙስና ማለት ነው (በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ አገር ውስጥ ገቢ -- አስገባሪዎቹ -- ታላላቅ ባለሥልጣኖች በሙስና ተከሰው ቃሊቲ ናቸው።

ታምራት የሚተቸውን መጽሐፍ ተጠንቅቆ ቢያነበው ኖሮ ስለሌላ የፖሊቲካ ቃል ትንሽ የተሻለ ግንዛቤ ያገኝ ነበር፤[73] ከዚህ በታች የጠቀስሁት የታምራት የሚያስደነግጥ አስተያየት እኔን ለመወንጀል ከጻፈው ጋር ሲጣመር ዓላማ እንዳለው የበለጠ ግልጽ ይሆናል።

***‹‹ኢትዮጵያ በእነዚህ የከሸፉ አገራት ዝርዝር መካተቷ አሳማኝ የማይሆንባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። የኢትዮጵያ መንግስት ምንኛ ተዳክሟል፤ተልፈስፍሷል ቢባል በፈለገው***

[73] በእንግሊዝኛ State የሚለው ቃል በመክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሰፋ ያለ ቦታ የያዘ ነበር፤ እሱ አራክሶ የጣለው የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ ነበር፤ ለአንባብያን ስል ላብራራው፣ በአማርኛ ሀገረ-መንግሥት ነው፤ አገር አይደለም።

*ሰዓት የፈለገው የግዛቱ ክልል ውስጥ ያለማቋረጥ አንቀጥቅጦ ግብር ይሰበስባል። የተለያዩ አቅርቦቶችን ለዜጎች ያከፋፍላል ለምሳሌ መንገድ ይሰራል፤ ሰዎችን በሰላም አስወጥቶ በሰላም ያስገባል፤ ለሰራተኛ ደሞዝ ይከፍላል። ይህን አይነት ጠንካራ መንግስት መቼም መንግስት የሚባል ከሌለበት ከሶማሊያ ወይንም የመንግስት ሰራተኛ ደሞዝ ካየ አምስት አመት ከተቆጠረባት ኮንጎ ጋር ማወዳደር አዳጋች ነው። እንደውም ይህ የመንግስት ጥንካሬ (Strong State) ባሕሪይ የኢትዮጵያን መንግስት ከአፍሪካ በርካታ መንግስታት ጋር ሲነጻጸር አልከሸፈም ለማለት ሊጋብዘን ይችላል።›*

እንደዚህ ያለውን የተወሳሰበ ነገር ያዘለ ሥርዓት በአንድ ቃል ያውም በጭራሽ ትርጉሙን በማያውቁት ቃል ለመግለጽ መሞከር ሌሎችን ከማሳሳት በላይ አስተሳሰብንም ያባልጋል፤ የማያውቁትን መጠየቅና ማጥናት የምሁርነት መለያ ነበር፤ በሌላ በኩል ደግሞ እኔን ለማስወንጀል የሚከተለውን ይላል፦

*በዚህ መጽሐፋቸው ፕሮፌሰር መስፍን በተደጋጋሚ "ወያኔ ወያኔ" እያሉ ሲጮሁ እናም ወያኔን እንደ ኢትዮጵያዊ ሳይኾን እንደ አንድ ባዕድ አካል ሲቆጥሩ ሳይ ቆረቆረኝ። እስከመቼ ነው ወያኔ ወያኔ የምንለው? እስከመቼ ነው የእነመለስን ኢትዮጵያዊነት የምንጠራጠረው?*

ይህን ሲጽፍ አለማፈሩ ያስቃል! አዛኝ፣ ቅቤ አንጓች! ታምራት በዚህ በአጭር ጽሑፍ ውስጥ ከኢትዮጵያዊነት መናፍቅ ወደተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊነት፣ ከአፍቃሬ ወያኔነት ወደነቃፊነት ሲገለባበጥ ጥያቄው ማን ገለበጠው ነው እንጂ ለምን ተገለበጠ አይደለም፤ የታምራትም ሆነ የአንዳንድ ሌሎች ተቺዎች ችግር መጽሐፉን ነካ ነካ አድርገው እኔ ላይ መጨፈራቸው ነው፤ አይጠቅማቸውም፤ በዚያ ላይ ስለእኔ የማያውቁትን ሲዘላብዱ (ታምራትም፣ ዳንኤል ክብረትም…) የበለጠ ስሕተት ውስጥ ይገባሉ፤ ለምሳሌ ታምራት ስለእኔ የጻፈውን ሁሉ ያነበበ ከእኔ





ጋር የሠራ፣ ወይም ደባል ሆኖ የኖረ፣ ወይም ተማሪ የነበረ ይመስላቸው ይሆናል፤ አንዱ ወይም ሁለቱ ተገናኝተን ይሆናል፤ ግን እኔ አሁን መንገድ ላይ ባየው አላውቀውም! እሱን ብቻ ሳይሆን አንዳንድ እምነቶቹንም አላውቅም፤ለምሳሌ ስለ ‹‹ምሁራዊ ትሕትና›› የሚለውን ማምታታት ከቤተሰቡ ይሁን ከተማሪ ቤት ያገኘው ግልጽ አይደለም፤ የትሕትናንም የምሁርነትንም ባሕርይ ከሚያውቅ ሰው የሚወጣ አይደለም።

ወደሌሎች ነጥቦች አልገባም፤ ነገር ግን የታምራት ግድፈቶች ከዚህ በላይ የተነሡት ብቻ አለመሆናቸውን ታምራትም ለራሱ ሲል፣ የእሱ አድናቂዎችም ለራሳቸው ሲሉ እየለቀሙ ቢነጋገሩባቸው እውቀታቸውን ያሰፉበት ይሆናል።

በሙሉ የተፈጥሮ ችሎታው ለመጠቀምና ውጤታማ ለመሆን ታምራትን ሰንገው ከያዙት ሁለት ልጓሞች ራሱን ነጻ ማውጣት አለበት፡ ጎሠኛነትና ብትንትንነት፤ ሁለቱን ያገናኛቸውና በአንድ ላይ ያሰራቸውን ገመድ መርምሮ ማግኘት እስኪችል ድረስ ችሎታው ቆሞ-ቀር ይሆናል፤ በውስጡ ትንሽ ጭላንጭል ስለሚታየኝ የእውነትን መንገድ እንዲያገኝና እንዲነቃ ከልቤ እመኝለታለሁ።

## *ሦስት በክፍሉ ትችት ላይ*

የክፍሉ በጣም ስል የሆነ ትችት በቀጥታ ያረፈው በመጽሐፉ ላይ ሳይሆን በታምራት ጽሑፍ ላይ ነው፤ ስለዚህም በእኔ አስተያየት (እኔን እንዳለው ትሕትና ካልጎደለው!) ለታምራት ጥሩ ትምህርት ያለበት ጽሑፍ ነው፤ ስለዚህም ደጋግሞ እንዲያነበው ያስፈልገዋል፤ በተረፈ የክፍሉን ምሁራዊ አመለካከት ከማድነቅ በቀር የምጨምረው የለኝም፤ ማዕርጉ በዛብህና ክፍሉ ሁሴን ባይኖሩበት የተቺዎቹ ደረጃ ከስምንተኛ ክፍል ያላለፈ ይሆን ነበር፤ ስለዚህም በጣም አመሰግናቸዋለሁ።

አራት በዳንኤል ክብረት ትችት ላይ

ሀ) የዳንኤል ክብረት ክሽፈት

መስፍን ወልደ ማርያም ጥር 2005

ለመናገርና ለመጻፍ ያለው ፍጥነት በሚናገርባቸው ጉዳዮች ላይ ካለው እውቀት ጋር አይመጣጠንም፤ እንዲያውም ያውቃል እንዲባል የሚጽፍ እንጂ አውቆ የሚጽፍ አይመስልም፤ አቶ ዳንኤልን ሳላውቀው በጻፈው ላይ አስተያየት ስሰጥ ይህ ሁለተኛዬ ነው፤ ከዚህ በፊት በአንድ ጋዜጣ ላይ በጣም የታወቀውን የአየርላንድ ችጋር በ150 ዓመታት ያህል አቅርቦት በማየቱ አስተያየት ሰጥቼበት ነበር፤ ዛሬ ደግሞ ስለመክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ በጻፈው ላይ አጭር አስተያየት ልስጥ፤ እንዲያው እንትንን እንትን ካላሉት ገብቶ ይፈተፍታል የሚባለውን በመከተል እንጂ ትርፍ ይኖረዋል ብዬ አልገምትም፤ ከደርግ ዘመን ጀምሮ የተለያዩ ካድሬዎች ደብተራዎችም ጭምር ማነብነብን እንደተናጋሪነት ሠልጥነውበታል፤ ስለዚህም ሰውም ማነብነባቸውን እንደእውቀት እየወሰደው ይወናበዳልና በጊዜው መልስ መስጠት ግዴታ ይመስለኛል፤ የሰው ልጅ በምን ይታፈራል? በወንበር፤ በወንበር አይደለም በከንፈር፤ ይባላል፤ነገር ሳላበዛ ጥቂት ነጥቦችን በማንሣት የአቶ ዳንኤልን የማንበብ ችሎታና የተንኮል ክህነት ብቻ ለአንባቢዎች ላሳይ፤ ስለአስተያየቱ አስተያየት መስጠት አስፈላጊ አይደለም።

**አንደኛ**፣ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ ይላል፤ ይህንን ባይነግረን ጥሩ ነበር፤ በመናገሩ ብቻ እንዳናምነው ማስረጃ ይሰጠናል፤ ያላነበበውን ደጋግሜ አንብቤዋለሁ ማለት ያስፈለገበት አስገዳጅ ምክንያት ምንድን ነው? አውቃለሁ ብሎ በመነሣት ለማሞኘት ወይም ለማታለል ካልሆነ በቀር ሌላ ምክንያት ያለ አይመስለኝም፤ እንደአቶ ዳንኤል ያለውን ለማስጠንቀቅ ደጋግሜ አነበብሁት በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ‹‹የዩኒቨርሲቲን ዓለም የማያውቁ ሰዎች ሌላ ትርጉም በመስጠት እንዳይሳሳቱ ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል፤ በአካል በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሆነው ልባቸው ከደብተራ ተንኮል ላልጸዳም ቀናውን የእውነት መንገድ እንዲያመለክታቸው





እመኛለሁ፤›› የሚል ተጽፎ ነበር፤ **ይህንን አቶ ዳንኤል አላነበበውም፤ ካነበበውም አልገባውም።**

**ሁለተኛ**፤ ‹‹ለመሆኑ ታሪክ ይከሽፋል? የክሽፈት ታሪክ ሊኖር ይችላል እንጂ የከሸፈ ታሪክ ሊኖር ይችላል? የስኬት ታሪክ ይኖራል እንጂ የተሳካ ታሪክ ይኖራል? አንድን ታሪክ ከሽፏል ወይም ተሳክቷል የሚያሰኘው ምን ምን ሲሆን ነው? … በመጽሐፉ የምናጣው ታላቁ ነገር ይሄ ነው፤›› በዚህ ትርጉም የማይሰጥ የቃላት ድርደራ ላይ ምንም አስተያየት መስጠት አይጠበቅብኝም፤ ይቀጥልና ‹‹.. የታሪክን ክሽፈትና ስኬት መበየኛ ነገሮችን አስቀድመው በማሳየት አንድ ታሪክ ከሸፈ ወይም ተሳካ የሚያሰኙትን መመዘኛዎች …›› ይላል አቶ ዳንኤል፤ ካላነበበው ‹ደጋግሜ አንብቤዋለሁ› በማለት ብቻ ጭንቅላቱ ውስጥ አይታተምለትም፤ የሚከተለው እንደሚነበብ ሆኖ የተጻፈ ነበር፤ ‹‹መክሸፍ የምለው አንድ የተጀመረ ነገር ሳይጠናቀቅ ወይም ሳይሳካ እንቅፋት ገጥሞት መቀጠል ሳይችል ዓላማው ሲደናቀፍና በፊት ከነበረበት ምንም ያህል ወደፊት ሳይራመድ መቅረቱን ነው፤ ››

**ይህ ተጽፎአል! አላነበበውም፤ ካነበበውም አልገባውም።**

**ሦስተኛ**፤ ‹‹ታሪክ ጸሐፊዎቹን ከታሪኩ ጋር አብሮ መውቀጥ ከተልባ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ ዓይነት ይሆናል››! ይላል፤ ይህ ሰው አንብቤአለሁ፤ አውቃለሁ፤ ሲል በመሃይም ድፍረት ነው፤ የሚከተለው ተጽፎአል፤ ‹‹አንድ ሰው በአገርና በሕዝብ ጉዳይ ላይ ከጻፈ ‹‹ማንም ዜጋ በጉዳዩ ላይ የመሳተፍና ሀሳቡን በሙሉ ነጻነት የመስጠት መብት አለው፤ አለዚያ በየጓዳችን በሐሜት ብቻ እየተዘላዘልን እውነትን አንጥሮ በአደባባይ የማውጣቱን ዘዴ ሳንማር ሌላ ሦስት ሺህ ዓመታት እንቀጥላለን፤ ›› **ይህንን አላነበበውም፤ ካነበበውም አልገባውም።**

**አራተኛ**፤ በራሱ ላይ ሲፈርድ ቶሎ ሳይጽፍ መቆየቱን ለማስረዳት ምናልባት ከእሱ የተሻለ ሰው ቢጽፍ፣ ምናልባት ፕሮፌሰር ባሕሩ ቢጽፍ፣ ምናልባት የታሪክ ሊቃውንቱ ተማሪዎች ቢጽፉ፣ ምናልባት የታሪክ ክፍሉ ቢጽፍ በማለት ጠብቆ እንደነበረ ይገልጻል፤ እነዚህ ሁሉ የፏን ምኞት እሱ በፈለገው ፍጥነት

ሳያሙዋሉለት ቀሩና እንፕሮፌሰር ባሕሩን ላጨበት ሥራ ራሱን አቀረበ፤ የሱ ድፍረት የሌሎቹን እውቀት የሚበልጥ ለማስመሰል ጻፈ፤ድፍረቱን ልናደንቅለት ይገባል፤ በማያውቁት ጉዳይ ደረትን ገልብጦ በሙሉ እምነት ማነብነብ የካድሬዎች ባሕርይ ሆኖ በቤተ እግዚአብሔርም ገብቶአል።

አምስተኛ፤ አቶ ዳንኤል ከአዋቂነት ወደመንፈሳዊነት ይሸጋገርና ‹‹አንድን አካል መልስ ለመስጠት በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ መሄስና መውቀስ ከሞራል አንጻር ፍትሐዊ አይሆንም፤ የሀገሬ ሰው ‹ሙት ወቃሽ አትሁን››› እዚህ ደግሞ ጭራሽ ሊወጣበት ከማይችለው የአለማወቅ ማጥ ውስጥ በድፍረት ገባ! ‹‹ሞራል›› ስለሚለው ነገር ምንም እንደማያውቅ ሳያውቅ አወጀ፤ ድፍረት ብቻውን በምንም መንገድ እውቀት አይሆንም፤ ለመራቀቅ ፈልጎ ራሱን በአለማወቅ አዘቅት ውስጥ ከተተ።

ስድስተኛ፤ በጽሑፉ መደምደሚያ ላይ የደብተራ ተንኮል አፈትልኮ ይወጣል፤ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ያነሣና በደብተራ ተንኮል አንዱን ‹‹ዶክተር›› የሚለውን መልክ የሌለውና ስም የሌለው የደብተራ ምሥጢር ያደርግና፤ ‹‹እኒህ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም ዶክተር ወደመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ዘንድ በማን በኩል እንደሄዱ ፕሮፌሰር መስፍን ያውቃሉ፤›› ብሎ ይለጥፍብኛል፤ እግዚአብሔር ያሳያችሁ ስሙን ያልጠቀሰውንና የማላውቀውን ሰው የእኔን ስም ጠርቶ እንደማውቀው አድርጎ ሌላ ስሙን ያልጠቀሰውንና እኔ የማላውቀው ‹‹ዶክተር›› ወደመንግሥቱ ያቀረበ እያለ ውሸት ሲያጠነጥንና ሲፈትል ጊዜ ያጠፋበት ምክንያት አልገባኝም፤ ተንኮሉ እዚህ ላይ አያበቃም፤ ታደሰ ታምራትን ‹‹መንግሥቱ ከመሸኙቱ በፊት ግን ‹ከዶክተር እገሌ ጋር ቅሬታ አላችሁ መሰል፤ አንዳንድ ነገር ነግሮኝ ነበር፤ እዚያው ተነጋግራችሁ ፍቱት፤ አላቸው፤›› ይልና የመጨረሻዋን የደብተራ ተንኮል ጣል አድርጎ ይደመድማል፤ ‹‹**አሁን እዚህ መጽሐፍ ላይ ቤተ መንግሥቱን አየሁት።›› ምን እንዳየ፣ የት እንዳየ፣ ምንና ምን እንደተገናኘ የደብተራ ምስጢር ነው፤ ያቀረበውን ሁሉ የማን ባለሙዋል ሆኖ ያገኘው እንደሆነም አይናገርም፤ እንዲህ ያለ ሞላጫነት! ስለእውቀት ከተጻፈ መጽሐፍ ተነሥቶ ወደመንግሥቱ





ኃይለ ማርያም ጓዳ ገብቶ፣ ስሙ የማይጠራ ዶክተርን መነሻ አድርጎ፣ ይህን ሁሉ እኔ እንደማውቅ ተናግሮ በድንቁርና ምርጊት ይደፍነዋል! እንዲህ ያለ ሰው ስለእውቀት ለማውራት ለምን ይነሣል? ከበሽታ በቀር ምን ሌላ ይገፋፋዋል?

ከላይ የተጻፈውን ለዳንኤል ክብረት መልስ ከጻፍሁ በኋላ ቁጥራቸው የበዛ የዳንኤል ሎሌዎች የማያቋርጥ ውርጅብኝ አወረዱብኝ፤ ግብረ-ገብነት ሊያስተምሩኝ የስድብ ናዳ አወረዱብኝ፤ ስለዚህም ለነሱም መመለስ ነበረብኝ፤የሚከተለው ጽሑፍ ለነዚህ ለዳንኤል ታማኝ ሎሌዎች የተጻፈ መልስ ነበር።

********************************************************

አምስት በዳንኤል ጭፍሮች ትችት ላይ
አንሰ እቤ አምግዕዝየ ኵሉ ሰብእ ሐሳዊ ውእቱ!
ፍሬ-አልባ ጩኸት
መስፍን ወልደ ማርያም የካቲት 2005

---

አቶ ዳንኤልን አላውቀውም፤ ለካ ብዙ ጭፍሮች ያሉት ሰው ነው፤ በጣም ተንጫጩለት፤ የሎሌ ነገር ሆነና ጩኸታቸው አንድ ነው፤ ጉዳዩን ጭራሽ አያውቁትም፤ ያንገበገባቸው መሪያቸው መነካቱ ነው፤ ለሎሌዎቹ መልስ መስጠት ባልተገባ ነበር፤ ነገር ግን ያደረጉት ትክክል መስሎአቸው እንዳይኩራሩና በያዙት የመክሸፍ መንገድ እንዳይቀጥሉ አንዳንድ ነጥቦችን ላብራራላቸው ፈለግሁ፤ ውጤት ይኖረዋል ብዬ ሳይሆን ለኔው ለራሴና ለማኅበረሰባችን ጤንነት ነው፤ ራሴን ከአቶ ዳንኤል ጭፍሮች ለመከላከል ፈልጌ እንዳይመስል፤ አትኩሮት በጉዳዩ ላይ እንዲሆን ለመሞከር ነው። አንዳንዶቹ ዲያቆን የሚል ቅጽል ባለመጨመሬ ሆን ብዬ መስሎአቸዋል፤ ባለማወቅ ነው፤ ራሴን ተጠራጥሬ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ከፈትሁና የማውቀውን ነገረኝ፤ -- የተካነ፣ ምሥጢር ያየ፤ ቀዳሽ -- የሚል፡ በዚህ መስፈርት እኔም ዱሮ ዲያቆን ነበርሁ፤ ዛሬም ይህንን የሚያሙዋሉ ወጣቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚልዮን ባይሆን በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ይኖራሉ፤ በዚያ ላይ እኔ እንደማውቀው ዲያቆን ሦስት ደረጃዎች ሲኖሩት የዲያቆኖች አለቃ ሊቀ ዲያቆናት

ይባላል፤ አቶ ዳንኤል ሲቀ ዲያቆናትም አልሆነም፤ የአቶ ዳንኤል ዲያቆንነት የቱ ዘንድ እንደሚወድቅና ምን ማለትም እንደሆነ አላውቅም፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም እንዲህ ያለ ማዕርግ መስጠት ጀምራ እንደሆነና ለነማን እንደምትሰጥ አላውቅም፤ እኔ ዱሮ የማውቀው ዲያቆን የቅስና ሥልጣን (በምድር ያሰራችሁት በሰማይም የታሰረ ይሆናል፤) ሲያገኝ መምሬ መባሉን ነው።

ወደተነሣሁበት ጉዳይ ልግባ -- አንድ መጽሐፍ አሳተምሁ፤ አውቃለሁ የሚለው አቶ ዳንኤል ተነሥቶ ስለመጽሐፉም ስለሌላ ሌላም የማያውቀውን ጻፈ፤ ስድስት የማድፈት ነጥቦችን ለቅሜ በማስረጃ እያስደገፍሁ የማያዳግም መልስ ሰጠሁት፤ ይህንን ያደረግሁበት ምክንያት ጭፍሮቹ እንዳሉት ሥራዬን አትንቀፉት በማለት በመታበይ አይደለም፤ ማናቸውም ሥራ አደባባይ ሲወጣ መነቀፉ አይቀርም፤ ስሕተትም አይጠፋም፤ አንድ ሰው በአንድ የአገር ወይም የማኅበረሰብ ጉዳይ ላይ ሲጽፍ ወይም በአደባባይ ሲናገር ራሱን ማጋለጡ ነው፤ የአቶ ዳንኤል ጭፍሮች ይህንን የማያውቁትን ጉዳይ ለእኔ ለማስተማር መከጀላቸው ጨቅላነታቸውን ያሳያል፤ በእኔ ላይ ባወረዱት ውርጅብኝ እንኳን ጉድጓድ ቆፍረው ራሳቸውን ቀብረው ነው፤ እውነተኛ ማንነታቸውን ደብቀው ነው፤ እነዚህ ጭፍሮች ስለመጋለጥ የሚያውቁት የለም፤ ስለዚህም ጉርጓድ ውስጥ ተቀብረው ስለማያውቁት ነገር መጮሁ የመጀመሪያው ስሕተታቸው ነው፤ ለነገሩ ስሕተት አይደለም፤ ወኔ-ቢስነት ነው።

እነዚህ ሁሉ ጭፍሮች ለጩኸት ከመጠራራታቸው በፊት መጽሐፉን ለማንበብና የክርክሩ መነሻ የሆኑትን ነጥቦች ለመጨበጥ አልሞከሩም፤ ወደው አይመስለኝም፤ ንጹታቸውን ለመግለጽና ግዳይ ለመጣል ስለቸኮሉ ለእነሱ ችሎታ የሚቀልለውን

**የአንተ አሽከር፣ የአንተ ቡችላ፣**
**ኩፍ ኩፍ ይላል እንደጉሽ ጠላ!**

በማለት በአደባባይ አቅራሩ፤ የችሎታ ማነስና ችኮላ ተለውሶ ያንን ጫጫታ አስከተለ፤ ገና ይቀጥላል፤ ባገኙን ቦታ





ሁሉ ይህንን ጅብዱአቸውን ሊገልጹልኝ የሞከሩም አሉ፤ ከመሀከላቸው አንድም አንኳን ጉዳዩን ለመገንዘብና በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት የሞከረ አለመኖሩ የአስተሳሰብ ደረጃቸውን በግልጽ ያመለክታል፤ የሁሉም ዘገባ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ነው።

1. መሀከላቸው ስለመጽሐፉ የተናገረ አንድም የለም፤ 2. ከመሀከላቸው አንድም ሰው አቶ ዳንኤል ስለጻፈው የተናገረ የለም፤
3. መጽሐፉን ሳያነቡና የአቶ ዳንኤልን ጽሑፍ ሳያነቡ እንዴት ብለው እኔ በጻፍሁት ብቻ እንደዚያ ያለ የንዴት ጫጫታ ማሰማት ቻሉ?

ጭፍራዎቹ በመጽሐፉና በአቶ ዳንኤል ጽሑፍ መሀከል ምንም ግንኙነት እንዳላዩበት ግልጽ ነው፤ ሊያዩበትም አይችሉም፤ ስለዚህ የእውቀት ጉድለታቸውን በንዴት ተኩት፤ እነሱው ራሳቸው የተገነዘቡትን የእውቀት ጉድለታቸውን እያጋለጡ ስለመጽሐፉ ለመናገር ወኔ አላገኙም፤ የኢትዮጵያውያን ባህላዊ ማምለጫና መብለጫ በሆነው የብልጣብልጥ ዘዴ ተጠቅመው በእነሱ ግምት እነሱን ከፍ እኔን ዝቅ አድርገው ለማሳየት ሞከሩ፤ ጭፍሮቹ በሙሉ እውቀቱ ስለሌላቸው መጽሐፉን ረሱት፤ ስለዚህም ራሳቸውን የሥነ ምግባር ሊቃውንት አደረጉና ትንሽነታቸውን ወደበላይነት ለመለወጥ ጣሩ፤ ይህ ብልጣብልጥነት እንደማያዋጣ ስለገባቸውና የእውቀታቸውንም ጎደሎነት ስለተገነዘቡ ማንነታቸውን ሳይገልጹ ስማቸውን ደብቀው በአደባባይ ደነፉ፤ ደስ አላቸው፤ አስደሰቱ፤ ‹‹ያንን ፕሮፌሰር ነኝ ብሎ የሚኮፈስ ሰውዬ ልክ ልኩን ነገርነው! ልኩን እንዲያውቅና ከእኛ የማይሻል መሆኑንም ነገርነው!›› አንዳንዶቹ የእውቀት ደረጃቸውን አዘቅት ሲያወርዱ ከመስፍን ጋር ፕሮፌሰርነትንም አብረው ይኮንናሉ! አይ ፕሮፌሰርነት! እንዲህ ከሆነ ይቅርብን! እያሉ ዘላበዱ።

ተመካክረው የተነሡት በእነሱ ሚዛን ስለመስፍን ወልደ ማርያም ምግባረ-ብልሹነት ለዓለም ለመንገር ነው፤ አዋጃቸውን እንቀበለው፤ ስለመስፍን ወልደ ማርያም አንድ እውቀት ያስጨብጠናል፤ ዋናው ጉዳይ ግን መስፍን ወልደ ማርያም አይደለም፤ ዋናው ጉዳይ መጽሐፉ ነው፤ እንግዲህ ስለመጽሐፉ ምንም የማያውቅ ሰው ስለመስፍን ወልደ ማርያም መናገር የሚችለው ስንት ገደሎችን ዘልሎ ነው? ሁሉም ያሉት መስፍን ወልደ ማርያም ለአቶ ዳንኤል የሰጠው መልስ ስድብ ነበር የሚል ነው፤ ነገር ግን ከመሀከላቸው አንድም ሰው ስድቡ ምን እንደነበረ አልተናገረም፤ አንዱም ደህና አድርጎ ያላነበበውን ደጋግሜ አንቤዋለሁ ብሎ ሐሰት የተናገረን ሰው ሐሰት ተናግረሃል ማለት፣ የማያውቀውን አውቃለሁ ብሎ የተናገረ ሰውን አታውቅም ማለት፣ የማያውቀውንና ያልሆነውን ነገር ሲለጥፍብኝና የተናገረውን መልሶ ምሥጢር በማድረጉ የደብተራ ተንኮል ማለት፣ ለእኔ ስድብ አይደለም፤ እውነትን መናገር፣ ወይም ፈረንጆች እንደሚሉት አካፋን አካፋ ብሎ መጥራት ነው፤ ማሰብ የሚችል ሰው ለተናገርሁት ማስረጃ እንዳይጠይቀኝ ማስረጃዎቼን ሁሉ ቁልጭ አድርጌ አቅርቤአለሁ፤ እንዲያውም ትልልቅ ግድፈት የምላቸውን ነገሮች አልገባሁባቸውም፤ እዚያ ብገባ የበለጠ አንጫጫ ነበር፤ ከጭፍሮቹ አንዱም እንኳን መጽሐፉን ያነበበ አይመስለኝም፤ ከጭፍሮቹ አንዱም እንኳን በአቶ ዳንኤል ጽሑፍ ውስጥ ምንም እንከን አላዩም፤ ሊያዩም አይችሉም፤ ከስድብም አልፎ ወንጀል ሊለጥፍብኝ ሲከጅለውም አልታያቸውም፤ ወንጀልን በሰው ላይ መለጠፍ አላዋቂነት፣ ተንኮል፣ ውሸት ቢባል ስሕተቱ ምኑ ላይ ነው? እውነት ከማይከበርበት ቤት የወጡ ጭፍሮች እውነትን አላዩም ብሎ መውቀስ ባይቻልም አለማየታቸውን መናገር ግን ተገቢ ነው፡ የአቶ ዳንኤል ጭፍሮች የመጽሐፉን ቁም-ነገር መጨበጥ ስላቃታቸው የሥነ-ምግባር ጉድለት የመሰላቸውን የመመጻደቅ ስብከት አወረዱት፤ ነገራቸው ሁሉ እንደአህያ መልክ አንድ ዓይነት ነው፤ ራሳቸውን አፋፍ ላይ እኔን ደግሞ ገደል ውስጥ ጨምረው እንደናዳ ሊያወርዱብኝ ሞከሩ፤ ከጭፍሮቹ መሀል አንድም እንኳን እሱም ራሱ ሆነ ጓደኞቹ የጻፉት የምግባረ





ብልሹነት መግለጫና ማረጋገጫ መሆኑን የመገንዘብ ችሎታ ያለው አልተገኘም፤ በነዚህ ጭፍሮች የማሰብ ችሎታ እውነት መናገርን እንደስድብ ከመውሰዳቸው በላይ እነሱ ግን ለመሳደብ ልዩ ፈቃድ ያላቸውና የሥነ ምግባር ደረጃቸውም የተለየ ነው፤ እነሱ ሲሳደቡ የሥነ ምግባር ብልሽት አይታያቸውም! እውነትን በደረቅ ቋንቋ ከመስማት ይልቅ ውሸትንና ተንኮልን በለስላሳ ቋንቋ መስማት የሚበልጥባቸው ጭፍሮች አቶ ዳንኤል ለተናገረው ዓይኖቻቸውን ሸፍነው እኔ በሰጠሁት መልስ ላይ ማተኮራቸው ያጋደለ የሆዳምነት ሚዛናቸውን በገሀድ ያሳያል፤ ውሸት የተናገረን ውሸታም ማለት፣ ተንኮልን የሸረበን ተንኮለኛ ማለት ትክክል ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእውነት የተራበ፣ ለእውቀት የተራበ ሆኖ ለብዙ ሺህ ዓመታት ባለህበት ሂድ ሲል የኖረው በእንደነዚህ ያሉ የእውነትና የእውቀት ጸር የሆኑ ጭፍሮች እየታገተ ነው።

ሳያውቁት **የመክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ** ዋናውን መልእክት በተግባር አሳዩ፤ እውነትንና እውቀትን (ሁለቱን መለየት አይቻልም፤ እውነትን የማይቀበል እውቀትን አያገኝም፤ እውቀትን የማይቀበል እውነትን አያገኝም፤) አርክሰው እነሱ ጨዋነት የሚሉትን አወጁ፤ አንዱ በማያሻማ መንገድ ገልጦታል፤ መስፍን ኃይለ ማርያም ነኝ የሚል እንዲህ አለ፤ ‹‹ከእርስዎ ምሁራዊ ስድብ የዳንኤል ክብረት ጨዋዊ መሃይምነት በእጅጉ ይሻላል።›› ይህ ሰው እሱና ጓደኞቹ በያዙት ሚዛን ‹‹ስድብ›› ያሉትን ተቀብሎ ከመታረምና ወደእውነትና ወደእውቀት መንገድ ከመግባት ይልቅ ‹‹ጨዋዊ መሃይምነትን›› መርጦ ለመኖር መወሰኑ ያሳዝናል፤ የዳንኤል ክብረትን አስመሳይነት፣ ደፋርነት፣ አላዋቂነትና ተንኮል በማያሻማ ቋንቋ ለመግለጥ የወሰንሁት በእንደዚህ ያሉ ምስኪን ‹‹ጨዋዊ መሃይሞች›› ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ገምቼ ልከላከልላቸው ብዬ ነበር፤ ተመችቶናል ስላሉ እግዚአብሔር ያውጣቸው፤ ሌሎች ሕመሙ እንዳይጋባባቸው ይጠንቀቁ!

በመጨረሻ በእውቀት ጉዞ ይሉኝታ፣ መግደርደር፣ መሽፋፈን፣ ማድበስበስ፣ መቀላመድ፣ የተጠሉና የእውቀት ጸር በመሆን የሚፈረጁ ዝንባሌዎች ናቸው፤ ሀ ማለት ሁለት ነው፤ ለ

ማለት ሦስት ነው፤ ከተባለ ሀ+ለ አራት ነው ሲል የተጻፈውን አላነበብህም፤ ወይም አልገባህም፤ ስለዚህም መልስህ ልክ አይደለህም ማለት መማር ለፈለገ ነውር አይደለም፤ እውነትንና እውቀትን ለማራመድ መንገዱ ይህ ነው፤ የተገነዘበው ይራመዳል፤ እውነትን የሚፈራው ወደኋላ ይቀራል፤ መክሸፍ ማለት እንዲህ ነው።

************************************************************

ስድስት በብርሃኑ ደቦጭ ትችት ላይ

የብርሃኑ ደቦጭ የምኞት ትችት
መስፍን ወልደ ማርያም መጋቢት 2005

ብርሃኑ ደቦጭ (ከስሙ ጋር የታሪክ ተመራማሪ የሚል አለ፤) ስለመክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ ለመተቸት ተነሣና እሱን ሲያገላላው የቆየውን ነገር ሁሉ ጻፈ፤ እንዲያውም ገና ሲጀምር ስለመክሸፍ ያለበትን ሁሉ አልነካውም በማለት ይናገራል፤ መጽሐፉ ስለመክሸፍ ነው፤ ብርሃኑ ደቦጭ የመክሸፍን ነገር አይወደውም ይመስለኛል፤ ስለዚህ ለምን አልተወውም? መጽሐፉን ትቶ ወደኔ! እኔን ሲደቁሰኝ ቢውል እንደመክሸፍ አልጠጥርበትም! እንግሊዝኛን በአማርኛ ፊደል መጻፍ የሚችል መሆኑን አወቅሁለት።

መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክን ብርሃኑ ደቦጭ የተጠቀመበት በአእምሮው ውስጥ መውጫ አጥተው ሲገላሉ የነበሩ ሌሎች በጭራሽ ያልተያያዙ ቅንጭብጫቢዎችን ለመዘርገፊያ አጋጣሚ ማግኘቱ ይመስላል፤ የጠቃቀሳቸውንም ነገሮች ፍሬ-ነገራቸውን አልነገረንም፤ በዚህ ዓይነት ጽሑፍም ሊነግረን አይችልም፤ ፍሬ-ነገሩን ሊነግረን ያልቻለውን ነገር እያነሣ ማለፍ ብቻ እውቀትን አይጨምርም፤ እንዲያውም የአስመሳይነት ስሕተት ውስጥ ይከታል፤ ለምሳሌ እኔን ‹‹በማርክሲስት የሚያስፈርጀውን ገጽታ ይላበሱና ...››[74] ይላል፤ አሁን ይህ ለምን ያገለግላል? ከየት አምጥቶ ነው የሚለጥፍብኝ? ተልእኮው

[74] ቀደም ሲል ታምራት ነገራ ቀኝ-ዘመም ጠላ ጠማቂ አድርጎኝ ነበር!





ያነጣጠረው በመጽሐፉ ላይ እንዳልሆነ የሚያሳዩ ብዙ እንደዚህ ዓይነት ምልክቶች አሉ፤ ይኸው ይበቃኛል።

የደርግ የጽሑፍ ተቆጣጣሪ (በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅና በለንደን ታሪክ የተማረ የታሪክ ተመራማሪ ካድሬ ነበር) አሁን ለትችት በቀረበውና ባልተተቸው መጽሐፍ ረቂቅ ላይ ‹‹የቷ ኢትዮጵያ? የማን ኢትዮጵያ?...) እያለ ጽፎ እንዳይታተም ከለከለ፤ ዛሬ ደግሞ ብርሃኑ ደቦጭ መጽሐፉ ከታተመ በኋላ ‹‹የመስፍን ኢትዮጵያ›› ብሎ ለጠፈባት! ‹‹በመጽሐፉ ከተነሡት ጉዳዮች የክሽፈት ታሪክ ስለተባሉት ጉዳዮች፣ የአርበኞችና የባንዳ ሚና ታሪክ አዘጋገብ እና የአድዋ-ማይጨው-ጅጅጋ ትርክት በዚህ አስተያየት ያልተካተቱ መሆናቸውን ከወዲሁ መግለጽ እወዳለሁ፤ ..›› ያልተመቸውን እየተወና የፈለገውን እየለወጠና እያነበጠ ስለመጽሐፉ መተቸት ምን የሚሉት አዲስ ፈሊጥ ነው? እንደተማረው የተለያዩ የርእዮተ-ዓለማዊ አመለካከቶችን ስሞች ጠቅሶ የእኔ መጽሐፍ አንዱም ውስጥ አልገባልህም ስላለው አልተመቸውም።

ከክብረ ነገሥት የተጠቀሰው ብርሃኑ ደቦጭን አላስደሰተውም፤ ምናልባትም ጊዜው ያለፈበት ብሎ ይሆናል፤ ጊዜ ስላለፈባቸው መጻሕፍት በሌላም ቦታ ተናግሮአል፤ የመስፍን አዲሱ መንገድ ‹‹በብዙ መልኩ ጊዜ ያለፈባቸው መጻሕፍት›› መጥቀስ ነው ይላል፤ መጻሕፍት፣ በተለይም የታሪክ ፍልስፍና መጻሕፍት ጊዜ የሚያልፍባቸው እንዴት ነው? የብርሃኑ ችግር ስለሁነት ያነበበውን ስለአስተሳሰብ፣ ስለአመለካከት ያደርገዋል፤ ምናልባት በፊዚክስ ጊዜው ያለፈ መጽሐፍ ሊኖር ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን የቶይንቢ ‹‹የታሪክ ጥናት›› የተሰኙትና ሌሎችም ጊዜያቸው መቼም አያልፍም፤ የመጻሕፍትን ባሕርይና ዋጋ ለፈተና ከመጥቀማቸው ውጭ ማየት ካልተቻለ የብርሃኑ አመለካከት በዓለም ያሉ ቤተ መጻሕፍትን ያራቁታል፤ በኋላ የተነገረው የተሻለ የሚባልበት ሁኔታ ስላለ በኋላ የተነገረው ሁሉ የተሻለ ነው ማለት አጉል አስተሳሰብ፣ ወይም በብርሃኑ ቋንቋ ‹‹ፋውል›› ነው።

‹‹የአንድ አገር ታሪክን ለማጥናት የአገር ተወላጅነትን ግድ የሚያደርግ›› ይህ አስተሳሰብ የኔ አይደለም፤ እሱ ለራሱ ዓላማ የደነቀረው ነው፤ እኔ ያልሁት ‹‹...ባዕድ የሆነው የሌላ ሕዝብ ታሪክን ሲጽፍ ሁለት ምክንያቶች አሉት፤ አንዱ ለእንጀራ ነው፤ ሁለተኛው የእውቀት ፍላጎት ነው፡፡›› የቱ ላይ ነው ብርሃኑ ‹‹ግድ›› የሚለውን ያነበበው? ብርሃኑ ታሪክን የሚያጠናው ለእንጀራ ብቻ መሆኑን ሳይናገር አስረዳን! እኔ ያልሁት ‹‹የውጭ ሊቃውንቱ ጥናት ልዩ ጥቅም ቢኖረውም ባይኖረውም ለራሳቸው ሲሉ የሚያደርጉትን ጥናት በጭራሽ ልንቃወም አንችልም፤ የምንቃወመው እነሱ እኛን እነሱ እንደፈለጉ አድርገው ሊቀርጹን የሚያደርጉትን ሙከራ ነው፤ እኛም እንደጥቁር ሰሌዳ የእነሱን ነጭ ጠመኔ የባሕርይ አድርገን መቀበላችንን ነው፡፡›› ብርሃኑ ደቦጭ ይህንን የመቃወም መብት አለው፤ የራሳችን ሰዎች ብቻ መጻፍ ግዴታ ነው አላልኩም፤ ብርሃኑም እንኳን ይህንን አይልም፡፡ እንደገናም ‹‹ታሪክን ማጥናት የሚገባው የአገር ተወላጅ ብቻ ነው የሚለው አስተሳሰባቸው ...›› ይላል፤ ይህንን ሐረግ በእኔ መጽሐፍ ውስጥ ላገኘ ሰው አምስት መቶ ብር እሰጣለሁ፤ የምሬን ነው! ብርሃኑ የራሱን እምነት ለማራመድ እኔን ምክንያት ያደርጋል፤ በብርሃኑ አመለካከት አንድ ስዊድናዊ ስለኢትዮጵያ ሲጽፍና ሌላው ከአንደኛው የኢትዮጵያ ጎሣ ሲጽፍ ያው ነው፤ ይህ የእሱ አመለካከት ይሆናል፤ እኔ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ጎሣዎችን ሁሉ አንድ አድርጎ የሚያመሳስላቸውና ከስዊድናዊው ወይም ከሌላው የውጭ አገር ሰው የሚለያቸው ነገር አለ ብዬ አምናለሁ፤ ይህ ለእኔ ይታየኛል፤ ለብርሃኑ አይታየውም፤ ልዩነታችን ነው፡፡

በጽሑፉ መጨረሻ ላይ ብርሃኑ ንዴቱ እየባሰበት ሄዶ ከመጽሐፉ ወጣ፤ ከመጽሐፉ ትችት ተሰናበተና ወደዘለፋ ገባ፤ ምክንያቱ አልገባኝም፤ ተለውጦአል ይለኛል፤ ለውጡን አይናገርም፤ የማያስፈልግ ሙግት፤ ከዚያም ከዚህም እየቀነጫጨበ የሚማታበት ልምጭ ይሰበስባል፤ አንዱ ስለታደሰ ታምራት የጥናት ዘመን (1270-1527) የሳትሁ አስመስሎ ወደዘለፋ የገባበት ነው፤ በትክክልና በቀና መንፈስ ላነበበ የሚከተለውን ብያለሁ፤--





*‹ምንም እንኳን የታደሰ መጽሐፍ የጊዜ ገደቡ ቢያበቃም በመጨረሻው ምዕራፍ አጼ ምኒልክን ከአጼ ዓምደ ጽዮን ጋር በማመሳሰል በአሥራ አራተኛው ምዕተ-ዓመት ዓምደ ጽዮን ቀርስቲያን ኢትዮጵያንእንዳስፋፋ ሁሉ አጼ ምኒልክም ይህንን የመስፋፋት ተግባር ፈጸሙ ፤ ... ፕሮፌሰር ታደሰ ከግራኝ ወረራ ቀደም ብሎ ዝርዝር የታሪክ ጥናቱን ከአቆመ በኋላ፣ አራት መቶ ሃምሳ ዓመት ያህል ጭው ባለ ዝምታ ዘሎ ወደአጼ ምኒልክ ዘመን ተስፈንጥሮ ይገባል፤ ይህንን ጭው ያለ የአራት መቶ ሃምሳ ዓመት የጊዜ ገደል አልተሻገረውም፤ ለዚህ ዋናው ምክንያት ታደሰ መስፋፋት በሚል ርእስ የጻፈውን ሁሉ የሚያስተባብልበት ታሪክ የሚገኘው በዝምታ ሊዘልለው በሞከረው አራት መቶ ሃምሳ ዓመት ውስጥና ...››*

ብርሃኑ ደቦጭም እዚያ ገደል ውስጥ ሆኖ ነው ዘለፋውን የሚያሰማው! አንድ ዓረፍተ ነገር ይዞ ለነቀፋ ከመቸኮል ሁሉንም አንብቦ መገንዘብ የተሻለ ክብርን ያመጣል፡፡

ሌሎች ከባድ ከባድ የሆኑ የአገር ጉዳዮች በብርሃኑ ጽሑፎች ውስጥ አሉ፤ እነዚህ ውስጥ አልገባም፤ ዋናው ምክንያቱም ብርሃኑ እንዳለው ‹‹የመስፍን ኢትዮጵያ›› የሌሎቹ በተለይ የወጣቶቹም ካልሆነች እኔን ከሌላው ይበልጥ አይነካኝም፤ ብርሃኑ ደቦጭ ከማን ጋር ተማክሮ እንደሆነ የመጨረሻ ጥይት የሚል ውሳኔ ላይ የደረሰው አላውቅም፤ መገመት ቢቻል ዝናሬ ገና ሙሉ ነው! ያለጥርጥር የብርሃኑ ደቦጭ ጽሑፍ ያነጣጠረው መጽሐፌ ላይ ሳይሆን እኔ ላይ ነው፤ ምክንያቱን አላውቅም፤ ስለዮሐንስና ስለምኒልክ ባለው ውዝግብ እኔን ወደምኒልክ ገፍቶ ከዮሐንስ ሊያርቀኝ ይሞክራል፡፡

የታሪክ ተመራማሪው ብርሃኑ ደቦጭ ርእሱን ብቻ ያመለከተውን የመጽሐፉን እምቡጥ አልነካውም፤ ወይ ደስ አላለውም፤ ወይ ግራ ገብቶታል፤ እንዲህ ያለ የመጽሐፍ ትችት አይቼም አላውቅም፤ በግድ መጻፍ አለብህ ካልተባለ በቀር ፍየል

ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ የሚባልለት ጽሑፍ ነው፤ ባይጽፈው ይሻለው ነበር፤ ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር ከፉኛ ይወርዳል።

***********************************

## *ሰባት በማስረሻ ማሞ ትችት ላይ*

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሐተታ ሌላው የአዲስ ነገር ጋዜጠኛ፣ ማስረሻ ማሞ በጻፈው ላይ ነው፤ ብዙም የግለሰብ ትንኮሳ ሳይኖርበት መጽሐፉ ባዘላቸው ቁም-ነገሮች ላይ ያተኮረ ነው፤ በመጽሐፉ ቁም-ነገር ተስማማም አልተስማማ መጽሐፉን በደንብ አድርጎ አንብቦ ገብቶታል፤ ዋናው ነገርም ይሄው ነው።

ሆኖም ከማስረሻ ጋርም ትንሽ ልዩነት አለን፤ ‹‹ልዩነት ይኑር!›› ይላሉ ፈረንሳዮች! ልዩነት ባይኖር አንነጋገርም ነበር፤ ከማስረሻ ጋር ዋናው ልዩነታችን በእግዚአብሔር ላይ ነው፤ እንደገባኝ ማስረሻ እግዚአብሔርንና ሃይማኖትን በመናቅ የተማሩና የተመራመሩ ለመምሰል ከሚሞክሩት አስመሳዮች ውስጥ አይደለም፤እኔም በእግዚአብሔር አምናለሁ፤ ነገር ግን እምነቱን በአንባቢው ላይ ለመጫን አልፈለግሁም፤ የተረዳሁት በዚህ መንፈስ ስለሆነ መልሴም በዚያ መንፈስ ይሆናል።

*ፕሮፌሰር መስፍን የእግዚአብሔር ጎልቶ መውጣት ላይ በዝርዝር አልሄዱበትም። ካስቀመጡት ትክክለኛ የታሪክ ትንታኔ እና ትርጓሜ አንጻር ታሪክ የሰው ልጆች የሥራ ውጤት ነው። ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መዝገብ ነው። ትውልድ እና ትውልድን የሚያስተሳስር ሰንሰለትም ነው። በዚህ ትርጓሜ ከተስማማን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ፈቃድ እና ጥላቻው ጣልቃ እንዲገባ መፈቀዱ እና መወሰኑ አሁን ላለው ኋላ-ቀርነት አስተዋጽኦ ማበርከቱን በዝርዝር ያዩት አልመሰለኝም። አንድም ሃይማኖታዊ የኾነውን ማኅበረሰብ ለመኀነጥ በዚህ ሰዓት*





*አልፈለጉም ወይም ከዋናው መሠረታዊ ችግር ይልቅ ኽሕጻንነቱ" እና በሐላፊነት አልሸከም ባይነቱ ላይ ማተኮርን መርጠዋል።*

ከዚህ በላይ ያለውን የጻፈው ማስረሻ በእንቅልፍ ልቡ ሆኖ ይመስላል፤ ከዚያ በፊት ከጻፈው ሁሉ አስተሳሰቡ የተለየ ሆነብኝ፤ አንደኛ ‹የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ፈቃድና ጥላቻው ጣልቃ እንዲገባ መፈቀዱ› እኔን፣ መስፍን ወልደ ማርያምን ምን አድርጎኝ ነው ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመስጠት ያበቃኝ! የእግዚአብሔር ጣልቃ-ገብነት ለኋላ-ቀርነት አስተዋጽኦ አበርክቷል፤ ይልና ይህንን አለማየቱን ይነግርልኛል፤ ሁለተኛ ሃይማኖታዊ ማኅበረሰቡን ‹‹መኀነጥ›› (የሱው ቃል ነው) ፈርቼ ሀሳቤን እንደገታሁ ይናገራል፤ ከየት ወጬት? ሕገ ኀልዮት ስማር አንድ አጉል ጥያቄ ሰምቼ ነበር፤ ‹‹ሚስትህን መደብደብ ትተሃል ወይ?›› ማናቸውም መልስ ከወንጀል አያድነውም፤ እኔ ግን ለማስረሻ ያለኝ መልስ በአጠቃላይ እስላሙ ወሎዬ እንደሚለው እንዲህ ያለ ከሴ ላይ አልሰግድም! ነው፤ እግዚአብሔር በዚህ ጉዳይ አያገባውም፤ ወይም መግባቱ ትክክል አይደለም፤ እንድል ፈልጎ እንደሆነ ትልቅ ስሕተት ነው፤ በእኔ እምነት የእግዚአብሔርንና የኢትዮጵያን ጥብቅ ግንኙነት ለመናገር ቦታው አይደለም፤ ሆኖም ማስረሻ እምነትም ባይኖረው በእውቀት ደረጃ የእግዚአብሔርን ባሕርይ በትክክል አለመገንዘቡ ሌላ ስሕተት ነው፤ በተረፈ እሱ ሳይታየው አየሁ የሚለውን ባለማየቴ ይወቅሰኛል፤ ትክክል አይመስለኝም ለትችት የቀረበው መጽሐፍ አእምሮን የሚመለከት ነው፤ ትችቱም ከአእምሮ ጋር የተዛመደ መሆን የሚያስፈልገው ይመስለኛል።

የእግዚአብሔርን ኃያልነት ማመንና የሰውን ለራሱ ኑሮ ኃላፊነትን መቀበልን ለይተው ማየት ካልቻሉ ከእግዚአብሔር ጋር እንታገላለን ሲሉ የሰውን የተጠያቂነትና የኃላፊነት አበሳ ጭራሹኑ ያደበዝዙታል፤ በፖሊቲካም ይሁን በሌላ እምነት የሰው ልጅ ኑሮውን ለመምራት የሚፈልገውን መንገድ ከመረጠ የሚደርሰው ልማትም ሆነ ጥፋት በእግዚአብሔር ላይ እምነት መኖር ወይም አለመኖር ውጤት አይደለም፤ የሰዎች የአእምሮ ሥራ ውጤት

ነው፤ አጉል ታቦት ሰባሪ መሆን ጉብዝና ወይም አዋቂነት መስሎ የሚታያቸው አስመሳዮች ጋር መሰለፍ አያስፈልግም።

የእኔን እምነት ግን ልገልጽለት እችላለሁ፤ እንደእኔ እምነት እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሁሉ ሰጥቶናል፤ በተጨማሪ በክርስትና ሃይማኖት እያንዳንዱ ሰው ለሚያደርገውና ለሚናገረው ኃላፊነቱ የግሉ ነው፤ የጅምላ ፍርድ የለም፤ ሰው ሙገሳንም ሆነ ወቀሳ የሚቀበለው በግል ሥራው ነው፤ የምናስብበት አእምሮ ሥራችንን የምንመዝንበት ኅሊና ሰጥቶናል፤ ሌሎችም አካላዊ መሣሪያዎች ሰጥቶናል፤ ስለዚህም እኛ ባጎደልነው እግዚአብሔርን ማማረር ተገቢ አይደለም፤ በአእምሮአችን ሳንጠቀምበት ቀርተን ወደኋላ ብንቀር፣ ዓይኖቻችንን ጨፍነን ገደል ብንገባ፣ ኅሊናችንን አደንዝዘን ክፉና በጎውን መለየት ቢያቅተን፣ እግዚአብሔር እንጀራ ጋግሮና ወጥ ሠርቶ ያጎርሰናል ብለን እየጠበቅን ቢርበን ኃላፊነቱ የራሳችን ነው፤ እግዚአብሔርን ልንወቅስ አንችልም።

ማስረሻ ያነሣው ሌላ ያልገባኝ ነጥብ ክሽፈትንና እውነትን እኩያና መንትያ ማድረጉ ነው፤ በምን ዓይነት ሕገ ኀልዮት የእውነት እጦት ውጤት የሆነው ክሽፈትና የክሽፈት ማስረጃ የሆነው እውነት እኩያና መንትያ እንደሆኑ አልደረስሁበትም።

ማስረሻ ያመጣው አንድ ረቂቅ ሀሳብ የእኔን አስተሳሰብ ቅራኔ ውስጥ ለመክተት የተደረገ ሙከራ ነው፤ ማስረሻ የሚከተለውን ይላል፤

*እንግዲህ ኢትዮጵያ እንደ አገርም ኾነ እንደ ሕብረተሰብ በተረጋገጠ እውነት (ሳይንሳዊ በኾነ) ላይ ካልተመሠረተች ያልከሸፈ ታሪክ ባለቤት መኾን እንደምን ይቻላታል?*

ማስረሻ ተገንዝቦትም ይሁን ሳይገነዘበው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ የከሸፈ ብቻ ሳይሆን ምንጊዜም ከመክሸፍ የማይወጣ ነው የሚል መደምደሚያ መስጠቱ ነው! ከሰውነት ደረጃ ከወረድንና የመማር ችሎታችን ወደእንስሳት ደረጃ ከደረሰ ማስረሻ ትክክል ነው፤ ኢትዮጵያውያን ሰዎች ከሆኑ፣ ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው ልምድም ሆነ ከሌሎች መማር የሚችሉ ከሆኑ





ወደሳይንሳዊ ማኅበረሰብነት የማይሸጋገሩበት ምን ምክንያት አለ? ከዚያም በላይ ማስረሻ ‹ሳይንሳዊ› ያለውን ነገር ቁሞ-ቀር እንዴ በተለጠፈበት የሚቀር አድርጎ ተገንዝቦታል፤ ይህ ጭራሽ ልክ አይደለም።

ማስረሻ አንድ ጥሩ ጥያቄ አንሥቷል፤ ባህላዊ ማኅበረሰብ እንዴት የሳይንሳዊ ማኅበረሰብን ባሕርይ ሊያገኝ ይችላል? ከኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ከመክሸፍ ሌላ ምን ይጠበቃል? በሌላ አነጋገር በእውቀት ያልተገነባ ማኅበረሰብ ከመክሸፍ አይድንም የሚል ጥሩ ነጥብ ነው፤ በዚህ በአሁኑ ጽሑፍ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ሞክሬአለሁ፤ በፊትም በመክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ በሰያፍ ተመልሶ እንደነበረ ማስረሻ አላመለጠውም፤ ግን አላጠገበውም ይመስለኛል፤ እዚህ ላይ እግረመንገዴን ስለእኔ የአጻጻፍ ዓላማ ልግለጽ፤ ሁሉንም ነገር ዝርዝር አድርጌ የአልጫ መረቅ ፍትፍት አድርጌ አላቀርብም፤ ሁለት ምክንያቶች አሉኝ፤ አንደኛ አንባቢው የማንበብ ችሎታ ካለው የግንዛቤ ችሎታውን ለማዳበር የሚያስችለውን፣ ማለትም የሚያሳስበውን መንገድ እንዲይዝ እመኛለሁ፤ ሁለተኛ የአንባቢውን የአእምሮ ችሎታ አሳንሼ አልገምትም።

የእግዚአብሔር ውሳኔ በኢትዮጵያውያን የታሪክ አስተሳሰብ ውስጥ መግባቱን ‹‹አሁን ላለው ኋላ-ቀርነት አስተዋጽኦ ማበርከቱን በዝርዝር ያዩት አልመሰለኝም።››

## የሌሎች ሰዎች ትችቶች

የሌሎች ሰዎች ትችቶች የምላቸው ብዙዎቹ ጥያቄዎች ናቸው፤ በመሠረቱ የመጽሐፉን ዋና ርእስ ትተው በንዑሳን ጉዳዮች ላይ ያተኩሩ ናቸው፤አንዳንዶቹ ለዋናዎቹ ትችቶች በሰጧቸው መልሶች ውስጥ ገብተዋል፤ አንዳንዶቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡-

ከሽፈ ለተባለው የተሰጠው ማስረጃ አብዛኛው ሕንጻ ነው፤ ዘለፋም አለበት፤‹‹የሰሜኑን ‹የድንጋይ ሥራ ጥበብ› ታሪክ መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ መክሸፍ መመልከት የተንሸዋረረ የታሪክ ትንታኔ ከማለት ውጭ ሌላ ማለት እጅግ አስቸጋሪ ነው።››

በእውነት የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞቹን ገድሏል ወይ? ይህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች፣ ጥያቄዎችም አይደሉም፤ አለማወቅን ለማሳወቅ የሚሰጡ መግለጫዎች ናቸው።





# ምዕራፍ ፩
# መደምደሚያ

## ምኞት ክልክል ነው

ከምኞት እንነሣ፤ የተሻለ ኑሮ መመኘት፣ የተሻለ ቤት መመኘት፣ የተሻለ ምግብ መመኘት፣ የተሻለ ልብስ መመኘት፣ በቅሎ መመኘት፣ ፈረስ መመኘት፣ ሜዳ ሙሉ ከብቶች፣ በጎችና ፍየሎች መመኘት የተፈጥሮ አይደለም? ከሆነ ለምን አናየውም? ካልሆነ በሌሎች አገሮች የምናየው እንዴት ሆነ? የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮውን ለማሻሻል አያስብም፣ ኑሮውን ለማሻሻል አይጨነቅም ማለት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከእንስሳ ደረጃም ዝቅ ማድረግ ነው፤ ከብትም የተሻለ ሳር ወዳለበት ይሄዳል፤ መልሱን የምናገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮውን ለማሻሻል እንዳይጥር የሚያደርጉትን ምክንያቶች ስናገኝ ነው፤ አስቀድመን አንዳንድ የአነጋገር ፈሊጦችን እንመልከት፡-

- **ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል፡** ይህ አባባል ዓላማው ሰዎች ያሉበት ሁኔታ ምንም ያህል አስከፊ ቢሆንም መንፈሳቸው እንዲቀበለው ማድረጉ ምሬቱን ይቀንስላቸዋል ማለት ሳይሆን አይቀርም፤ አስከፊውን ሁኔታ እንዳይከፋበት ያደርጋል ማለት ነው፤ ይህ ራስን ማታለል አይደለም፤ ይህ ራስን ለውጩ ሁኔታ ማዘጋጀት ነው፤ ራስን ማታለል የቂሎች ሥራ ነው፤ ራስን ማዘጋጀት፣ ራስን ማመቻቸት ጥልቅ አስተሳሰብ ነው፤ ለውጥ ያሬፈልጋል፤ ነገር ግን ከቁጥጥር ውጭ ያለውን ለመለወጥ

መሞከር እርባና የለውም፤ ስለዚህ የመጣውን ለመቀበል ራስን ማዘጋጀት ብልህነት መስሎ የታያል።

- **ጎምን በጤና፡** መቃብርን እንደቤት አድርጎ ለተቀበለ ጎመን በጤና አያስቸግረውም፤ ጎመን በልቶ በጤና ማለት አማራጩ ችግር አለበት ማለት ነው፤ ችግሩን ለማስወገድ ከመሥራት፣ ከመጣር፣ ከመልፋት ጎኑን በልቶ በጤና መተኛት!
- **ለምን ያለው ስልቻውን ጫን ያለው ኮርቻውን፡** ወደፊት የሚሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር የተወሰነ ነው፤ እያንዳንዱ ሰው የሚያገኘው በቅድሚያ ከእግዚአብሔር የተደለደለለትን ነው፤ እንደዚህ ያለውን እምነት የሚያራምዱ ሃይማኖቶች አሉ፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ከእስልምና ውጭ ሌላ የለም፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም በኩል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ይህ እምነት የሚስፋፋ ይመስለኛል።
- **ልፋ ያለው በሕልሙ ዳውላ ይሸከማል፤** አርፎ የአግዚአብሔርን ስጦታ በመጠበቅ ፋንታ በራሱ ጥረት አገኛለሁ ብሎ በከንቱ የሚውተረተር ሰው ድካሙ ከንቱ ነው፤ እግዚአብሔር ካልፈቀደ አንኳን ቀን ሌሊትም እረፍትን አያገኝም፤
- **የማይችሉት ባላጋራ ከወዳጅ ይቆጠራል፤** መታገል አቅምን አውቆና ማሸነፍ የሚቻል መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ነው፤ መሸነፍ ከታወቀ ትግል ለምን ይጠቅማል? ከዚህ የምንረዳው ለኢትዮጵያውያን ትግል ማለት በአሸናፊነት የሚወጡበት መሆኑን ነው።

የኢትዮጵያውያንን ሥነ ልቡና በአጠቃላይ ለመገንዘብ ያህል ከዚህ በላይ ያሉት ይበቃሉ እንጂ በጣም ብዙ መጥቀስ ይቻላል።

!!!! ከላይ የተባለው ሁሉ ወደመክሸፍ እንቡጥ ውስጥ ያስገባናል፤ «*መክሸፍ እንደኢትዮጵያ ታሪክ*» ከታተመ በኋላ መክሸፍ የሚለውን ቃል ብዙ ጊዜ እሰማዋለሁ ወይም አነበዋለሁ፤ ነገር ግን እኔ መክሸፍ የምለውና ሌሎች የሚጠቀሙበት ትርጉም አንድ አይመስለኝም፤ ሌሎች ሲጠቀሙበት የአንድ አፍታ ወይም የአንድ ጊዜ ጥፋት ወይም ስሕተት አድርገው ነው፤ ጥይት ከሸፈ





ሲባል አንድ ጥይት ነው፤ ጥይት ሁሉ ሲከሽፍ ችግሩ የአንድ ጥይት ብቻ መሆኑ ይቀራል፤ እንዲያውም የጥይቱ መክሸፍ ምክንያት ጠመንጃው ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህ ብዙ ጥይቶች መክሸፋቸውን ከተረዳን በኋላ ተኩሱን መቀጠል ምን ውጤት አለው? ምናልባትም ውጤቱ መክሸፍ ይሆናል፤ እንግዲህ አንዱ አማራጭ ጥይቱ ሁሉ እስቲያልቅ ድረስ እየተኮሱ ማክሸፍ፣ ወይም ሌላው አማራጭ መተኮሱን አቋርጦ ጥይቶቹንም ጠመንጃውንም፣ ከግንኙነታቸው ጋር መመርመር ይሆናል።

ጥይቶቹንም ጠመንጃውንም፣ በሁለቱ መሀከል ያለውንም ግንኙነት ስንረዳ ምን ልናገኝ እንችል ይሆን? የምርመራችን ውጤት የሚከተለው ይሆናል፤

ወይ ጥይቱ ብልሽት አለው፤
ወይ ጠመንጃው ብልሽት አለው፤
ወይ የጥይቱና የጠመንጃው መገናኛ ብልሽት አለው፤
ወይ ሦስቱም ነገሮች ብልሽት አላቸው፤

እንዲህ የመክሸፍን ብልት አውጥተን ከመረመርን በኋላ ሕመሙ የት እንደሆነ፣ ምን እንደሆነ ለማወቅ እንችላለን፤ ፈውሱ ወይም መፍትሔው ምን እንደሆነ እንረዳለን፤ ከዚያ በኋላ መክሸፍ አለቀለት!

በገፍ ጥይት እየገዙ መክሸፍ እንደወያኔ መሆን ነው፤ ዩኒቨርሲቲ ምን እንደሆነ ሳያውቁ ማፍረስ፣ የኒቨርሲቲ ምን እንደሆነ ሳየውቁ ሕንጻዎችን መገንባት፤ ባቡር ምን እንደሆነ ሳየውቁ የተሠራውን መንገድ ማፍረስ፣ ለኢትዮጵያውያን መኖሪያ ቤት ምን እንደሆነ ሳየውቁ ሕንጻዎችን መገንባት፣ አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይልና ውሀ ከባድ ችግር በሆነበት አራትና አምስት ፎቆች መሥራት፣ ለአሮጊቶችና ለሽማግሌዎች፣ ለሕመምተኞች አለማሰብ፣ ለጤንነት አለማሰብ ... ይህ ሁሉ የመክሸፍ አካሄድ ነው፤ ውሳኔ ሰጪዎቹ ሁሉ እውቀት የጎደላቸው ብቻ ሳይሆኑ ጸረ እውቀትም ናቸው፤ባይሆኑ ለሥራቸው ሁሉ የሚመክራቸው ይፈልጉ ነበር።

ሌላ በደንብ ግልጽ ሆኖ እንዲገባን የሚያስፈልገው የምንነጋገርበት የመክሸፍ ዓይነት ግለሰቦችን ብቻ የሚነካ አይደለም፤

የምንነጋገረው ስለማኅበረሰባዊ መክሸፍ ነው፤ የምንነጋገረው ስለአገር መክሸፍ ነው፤ ለግለሰብ መክሸፍም ቢሆን ኃላፊነቱን የሚወስደው ማኅበረሰቡ ነው፤ አንደኛ አጼ ኃይለ ሥላሴ በትውልድ ያገኙትንና በባህል ያጸደቁትን ሥልጣን ለመቀማት ያሰፈሰፉትና የቀናቸውም ከባህል ምንም መነሻ መሠረት የላቸውም፤ ባህሉን በዘመናዊ የፖሊቲካ አስተሳሰብ ሊያሻሽሉት ነው እንዳይባል ይህም የለበትም።

ለሥልጣን ያሰፈሰፉት ሁሉ ከኢትዮጵያዊ ባህል ላይ የተተከለውን አገዛዝ በአዲስና ዘመናዊ አገዛዝ (አስተዳደር አይደለም) ለመለወጥ ከመፈለግ በቀር ሌላ ምንም ዓላማ የላቸውም፤ ሁሉም የተለያዩ ጥላቻዎችን በተውሶ አስተሳሰብ ለውሰው የኢትዮጵያን ሕዝብ መጋት የሚፈልጉ ናቸው፤ ከቡድኖቹ ውስጥ አንዱም ከራሱ ከድርጅቱ የፈለቀ ሀሳብ የለውም፤ ሁሉም **ማርክሳዊ-ሌኒናዊ** ነን-ባዮች መስለው በደንብ ያልገባቸውን ሁሉ የሚየነበንቡ ናቸው፤ እኔ ይህንን በተጨባጭ አረጋግጫለሁ፤[75] ስለዚህ ከባህል ውጭ ከመሆናቸው ሌላ የያዙት ድንቁርና ነው፤ ከተውሶው ሀሳብ ጋር ገንዘብና መሣሪያም አግኝተው ይሆናል፤ እንግዲህ የእነዚህ የአምስት ቡድኖች ውዝግብና ንትርክ ወደጠብ እየተለወጠ በሺህ የሚቆጠሩ የልጆችንና የወጣቶችን ሕይወት ቀጠፈ፤ ዛሬ እነዚህን ለጥይት ማገዶ ያደረጓቸውን ልጆችና ወጣቶች ለአገር መስዋእት እንደሆኑ እያስመሰሉ ያቀርቧቸዋል፤ እውነቱ ግን የሞቱትን ለማክበር ሳይሆን እኩይ ተግባራቸውን ለመሸፈን ነው።

**ከብዙ የንትርክና የመገዳደል ዓመታት በኋላ የሚደንቅ ነገር ሆነ፤ ድንቁርና አሸነፈ!** በአንጻራዊ አነጋገር የተማሩ የሚባሉ ወጣቶች የነበሩባቸው ኢሕአፓና መኢሶን ድራሻቸው ጠፍቶ ሦስቱ በትምህርት የማይታሙት በድል አድራጊነት ወጡ፤ **ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድል ነው? ወይስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባህል?** ምንም ትንሽ ቢሆን ቁጥሩን አትናቁት፤ ሁለት ለሦስት ናቸው!

[75] ታየ ረታ በሰብሳቢነት የሚመራው የአስተዳደር ክልሎችን (ወረዳ፣አውራጃ፣ ክፍለ ሀገር) ለመፍጠር በደርግ የተቋቋም ኮሚቴ ውስጥ ስለነበርሁ ከሚምሉባቸው መጻሕፍት ምንጭ ሳልሰጥ እየጠቀስሁ አንድ ወረቀት ስለብሔረሰብ አቅርቤ ጭንቅላታቸው ዞሮ ነበር።





የመክሸፍን ኃይል ይበልጥ እንድትገነዘቡት በሌላ መንገድ እንሂድ፤ የወታደሩ መሀይም ራሱን አስተባብሮ **ጃንሆይን ከዙፋናቸው ሲያወርድ አንድ እልልታ!** ትምህርት ያልተስማማው የትግራይ ወጣት ጫካ ገብቶ ከሻብያ ጋር ተረዳድቶ አዲስ አበባ ሲገባና **መሀይሙን ወታደር ከዙፋን አስወርዶ ሲወጣበት ሁለተኛ እልልታ!** **ሻቢያ በኤርትራ ያለውን የወታደር ኃይል ደምስሶ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለይቶ ሌላ ጎረቤት አገር ሲፈጥር ሦስተኛ እልልታ!**በነዚህ የለውጥ አዙሪት ውስጥ የኢሕአፓና የመኢሶን ርዝራዦች ወደአሸነፈው እየተጠጉ ሎሌ ሆነዋል።

ትምህርቱ ባይገባቸውም የተማሩትና ጫካም የገቡት ከተማውም ጫካውም አውሬ ሆኖባቸው፣ ከጫካቸው ወጥተው በደርግ ፈረስ ላይ የተፈናጠጡትም የደርግ ፈረስ ደንብሮባቸው ሲበታተኑና በየፈረንጅ አገር ከተማ ሱቅ እየከፈቱ መነገድ ጀመሩ፤ ከነፍጠኛነት ወደነጋዴነት! የተማረ ለኢትዮጵያ እንደማይሆን ሌላም ማስረጃ አለ፤ በ1966 ለውጥ ጊዜ የጸጥታ ኮሚሽን የሚባል የተማሩ መኮንኖች ቡድን ተቋቋሞ ነበር፤ የማስታውሳቸው ሁለቱ ያየር ኃይል መኮንኖች ኮሎኔል ተሰማ አባደራሽና ኮሎኔል ጌታቸው ኃይሌ ነበሩ፤ ኮሎኔል ተሰማ (ነፍሱን ይማረውን በቅርቡ ዐረፈ፤) የኤሌክትሪክ መሀንዲስ ሲሆን ሕግም ለጥቂት ዓመታት ተምሯል፤ ኮሎኔል ጌታቸው የሕግ ምሁር ነው፤ ምንም ወታደር ቢሆኑ እውቀትና ጥርጣሬ አይለያዩምና የተማሩት መኮንኖች ሲያቅማሙ ደርግ መሀይሙ መጣና ሥልጣኑን በጉልበት ያዘው፤ የክብር ዘበኛስ በምን ከሸፈ? በደርግ ዘመንስ የነጄኔራል ፋንታ በላይ፣ ጄኔራል መርዕድ፣ ጄኔራል ደምሴ ቡልቱ … ሀሳብስ ምን አጨናገፈው?

ሌላውን ሁሉ ትተን በቀጥታ ወደደርግ እንግባ፤ እነዚያ መቶም ይሁኑ መቶ ሃያ ተሰብስበው ማዕርጋቸው ምን ነበረ? ከተራ ወታደር እስከሻለቃ ድረስ ብቻ ነበሩ፤ በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ውስጥ በርከት ያሉ ሌፍቴናንት ጄኔራሎች ነበሩ፤ የባሕር ኃይል አድሚራሎች ነበሩ፤ ከእንግሊዙ ሳንድኸርስት፣ ከፈረንሳዩ ሳን ሲር፣ የጀርመኑንና የአሜሪካኑን ስሞቻቸውን አላስታውስም፤ ከእነዚህ የጦር ማሠልጠኛ ቤቶች

የወጡ መኮንኖች ነበሩ፤ ከዚያም ሲወርድ በጣም ገናና ከነበረው የሐረር የጦር ቤት ሠልጥነው የወጡ ብዙዎች ነበሩ፤ ከነዚህም ውስጥ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በተለያዩ ትምህርቶች፣ በምህንድስናም ጭምር የተመረቁ መኮንኖች ነበሩ፤ **የደርግ ምርጫ እነዚህን ሁሉ አልፎ ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምና ሻለቃ አጥናፉ አባተ ላይ እንዘጭ ብሎ የወደቀው በአቦ-ሰጡኝ ነው? ወይስ በባህል ተጽእኖ?**

እንግዲህ ከዚህ በላይ ባየናቸው ሁነቶች የአዳፍኔን ኃይልና የመክሸፍን ውጤት እርግጠኛነት ለመቀበል ለሚያስቸግራቸው ተጠራጣሪዎች ወደኋላ እንሂድና ማስረጃ እንሰብስብ፤ የኢጣልያ ወረራ ካበቃ በኋላ በጃንሆይ የተሾሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው ናቸው፤ ቢትወደድ መኮንን ተክለ ሰውነታቸው፣ መልካቸው ዓይኖችን የሚማርክ ነው፤ ምናልባትም በዚሁ ምክንያት ይሆናል የጃንሆይን የወንድም ልጅ ልዕልት የሻሸ ወርቅን ያገቡት፤ ቢትወደድ እንዳልካቸው ከዚህ ሌላ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚያበቃቸው ነገር መኖሩን አላውቅም፤ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ግን ራስ እምሩ ከሳቸው የተሻሉ ናቸው ብዬ አምናለሁ፤ ለሎሌነት ግን ቢትወደድ ከራስ እምሩ የሚሻሉ ይመስለኛል፤ ለዚህ ነው ራስ እምሩ በአሜሪካ፣ በህንድና በሶቭየት ኅብረት በአምባሳደርነት ሲንከራተቱ ቢትወደድ ከአዲስ አበባ ያልወጡት፤ ‹‹**አልሞትኩም ብዬ አልዋሽምን**›› ይጽፉ ነበር! ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትም ነበሩ፤ አቶ ይልማ ዴሬሳም ነበሩ፤ ልዕልት ተናኘ ወርቅን ያስወለዱት አቶ አበበ ረታም ነበሩ፤ ግን በጊዜው ከራስ ቢትወደድ የተሻለ ታማኝ ሎሌ አልተገኘም።

ለአዳፍኔ እውቀት ያለው፣ ብልህና አስተዋይ ሰው ጸሩ ነው፤ ይህንን ያውቃል፤ ስለዚህም ሁለቱ አዳፍኔና አዋቂ ሊወዳጁ አይችሉም።

## አዳፍኔና የፍርሃት ሰንሰለቱ

አዳፍኔ በሚገዛው ዓለም ውስጥ በልቡ አዳፍኔን ለመሆን የማይመኝ የለም፤ አዳፍኔ የፍርሃት አባት ቢሆንም ይፈራል፤





ስለዚህም ልጆቹን ፍርሃትንም ይሁን መክሸፍን ይፈራቸዋል፤ የመክሸፍ አባት ቢሆንም ሊከሽፍ ይችላል፤ ረዥሙ የፍርሃት ሰንሰለት የመጀመሪያው ቀለበት በአዳፍኔ አንገት ላይ ነው፤ አዳፍኔ አንገት ላይ ያለው የፍርሃት ቀለበት ሰንሰለት እየሠራ በአዳፍኔ ስር ያሉ ትላልቅ ሹማምንትና አዛገሮች አንገት ላይ እንዲይዝ ተደርጎ ይጠልቃል፤ በአዛገሮቹና በሹማምንቱ አንገት ላይ ካለው ሰንሰለት ሌላ አነስ ያለ ሰንሰለት በመካከለኛ ደረጃ ያሉት ሹሞች አንገት ላይ ይገባል፤ ከአዳፍኔ ጀምሮ እስከመጨረሻው ተራ ጸሐፊ፣ ተራ ወታደር፣ ፖሊስ፣ ዓቃቤ ሕግ፣ ዳኛ፣ የምክር ቤት አባል፤ አስተዳዳሪ፣ የቀበሌ ሠራተኛ፣ አምባሳደር፣ ወዘተ. … ከአዳፍኔ ደመወዝ እያገኘ ትእዛዞችን የሚፈጽም ሁሉ በአንዱ ወይም በሌላው የፍርሃት ሰንሰለት ውስጥ የተያዘ ነው።

የመክሸፍ ታላቅ ወንድም ፍርሃት ነው፤ የአዳፍኔ ዋና ልጅ ነው፣ ቀኝ እጁ ነው፤ የአዳፍኔን ምኞት ሁሉ የሚያስፈጽም ፍርሃት ነው፣ የአዳፍኔ ዋና መሣሪያ ሆኖ የጭካኔና የማሰቃየት ተግባርን የሚያስፈጽም ፍርሃት ነው፣ በአዳፍኔ የማሳመምና የመግደል ችሎታ ሰውን የሚያደነዝዘው ፍርሃት ነው፣ የአዳፍኔን የመቀማትና የመዝረፍ፣ የማራቆትና የማስራብ፣ የማዳከምና የማደህየት ጉልበት የሚያጠነክረው ፍርሃት ነው፤ ፍርሃት አዳፍኔን በሚያጠነክረው መጠን ሌሎችን በነፋስ ላይ እንዳለ ቅጠል በፍርሃት እንዲንቀጠቀጡ ያደርጋቸዋል፤ አዳፍኔ ያለፍርሃት አይኖርም፤ ፍርሃትም ያላዳፍኔ አይኖርም፤ አባትና ልጅ በፍርሃት ተቆራኝተው እየተጠባበቁ ይኖራሉ።

አዳፍኔ ከአንድ ሰው ጉልበት የማያልፍ ትንሽ ነገር ነው፤ ነገር ግን የሰውን ልብ ለማፍረስ፣ የሰውን አንጎል ለመበተን፣ የሰውን ሕይወት እንደቅጠል ለመበጠስ እንደጉንዳን የሚርመሰመሱ ቅልብ ሠራዊት አሉት፤ ከአዳፍኔ ቃል እስቲወጣ አይጠብቁም፤ ፊቱን አይተው እርምጃ ይወስዳሉ፤ ፊቱ ፈካ ሲል አገር በሞላ በከበሮ ድምጽ ይሞቃል፤ ፊቱ ጨለም ሲል አገር ሁሉ በቅልብ ሠራዊት ይታመሳል፤

በሌላ በኩል ደግሞ ያንን ትንሽ ቁካሉን የጎልያድን እያሳከሉ አግዝፈው የሚስሉት ጋዜጠኞችና ጸሐፊዎች እየተባሉ የሚጠሩ

የእውነት ግልምጫ ገርፏቸው የማያውቁ ዓይነ ደረቅ ውሽታም ሠራዊት አሉት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዙሪያውን ከበው ዘመድ እንኳን እንዳይጠጋው የሚጠብቁት የወታደር፣ የፖሊስና የደኅንነት ሠራዊት አሉት፤ መከታው፣ አለኝታው፣ ኃይሉ ቢሆኑም ልባቸውን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር አይቻልም፤ አዳፍኔ ቅልብ ሠራዊቱን ልባቸውን ለመቆጣጠር ሲል ከሚያስፈልገው በላይ ይጨነቅላቸዋል፤ ጭንቀቱ ለራሱ ነው፤ ቅልብ ሠራዊቱን ጨምድዶ ለመያዝ ነው፤ አንድ ቀን ፍርሃት ከቅልብ ሠራዊቱ ጋር ፍቅር ቢይዘው በማለት አዳፍኔ ይሰጋል፤ ቅልብ ሠራዊቱ ከሆዱ በላይ ምንም ስለሌለ ሆዱን የበለጠ የሚሞላው ካገኘ ፊቱን እንደሚያዞር የታወቀ ነው፤ ስለዚህ ሠራዊቱንም ሙሉ በሙሉ አያምነውም፤ ዋናውን ልጁንም ሙሉ በሙሉ አያምነውም፤ የአዳፍኔ የስጋት ኑሮ!

ባለሥልጣንና የባለሥልጣን ሎሌ ሁሉ በአንገቱ ላይ ያጠለቀው ሰንሰለት ማስፈራሪያ ወይም የፍርሃት ምልክት ብቻ አይደለም፤ እንዲህ ብቻ አድርገን ከወሰድነው ከውሻ ሰንሰለት የተለየ አይሆንም፤ ሰዎች ናቸውና ሰንሰለቱ የኃላፊነትና የተጠያቂነት ስሜትን የሚያሳይ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፤ በኢትዮጵያ የክርስቲያን ባህል ማተብ የነበረውን ተግባር ለፍርሃት ሰንሰለቱ ሰጥቼ አየዋለሁ፤ እያንዳንዱ ሹም በአጠለቀው የፍርሃት ሰንሰለት ቀለበት ትልቅነት መጠን የጉልበቱን መጠን፣ የታዛገሮቹን ብዛት፣ በየሄደበት የሚያገኘውን ክብር፣ ሥልጣኑ የሚያስገኝለትን ጥቅም፣ መፈራቱን ይገነዘባል፤ በዚህ ጊዜ የሚያድርበት የኩራትና የበላይነት ስሜት ለኃላፊነትና ለተጠያቂነት አያበቃውም የሚል ክርክር ለእኔ ፊር የለቀቀ ይመስለኛል፤ ሌላው ቀርቶ ከአዳፍኔ አገዛዝ ውስጥ ከወጣ በማናቸውም አቅጣጫ ለተሠራ ነገር ሁሉ ከተጠያቂነት የሚያመልጡ አይመስለኝም፤ አንድ ጽንፈኛ ምሳሌ ላቅርብ፤ በቀይና ነጭ ሽብሮች ዘመን የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች ነን የሚሉ ሁሉ፣ ለከፍተኛ ሕግ፣ ለአምላክ ትእዛዝ የቆምን ነን እያሉ በየቤተ ክርስቲያኑና በየቤተ መስጊዱ የሚሰበኩ ሰዎች አደባባይ ወጥተው ያንን የደም መፋሰስ ለማውገዝ፣ ለማስቆም አለመቻላቸው የሚያሳየው በአንገታቸው ያጠለቁት የፍርሃት





ሰንሰለት ምን ያህል ጠንካራ እንደነበረ የሚያመለክት ነው፤ የቀይና ነጭ ሽብር ጉዳይ አይመለከታቸውም ለማለት የሚዳዳው ከአለ የሃይማኖትና የማኅበረሰብ ግንኙነትን እንደገና ይመርምር።

የሃይማኖት ሰዎችን የመንፈሳዊ መሪዎች ናቸው ብለን የመንፈስ ግዴታ ብንጭንባቸው ተገቢ ነው፤ ለሌላው ግን አይሆንም የሚል ክርክር ይመጣ ይሆናል፤ ለሌላውም ቢሆን አንደኛ በሰብአዊነት፣ ሁለተኛ በዜግነት ኃላፊነቶችና ተጠያቂነቶች አሉ፤ ስለዚህ ማንም በተለያዩ የአገዛዝ ሥራዎች ላይ የነበረ ሁሉ የጅምላ ኃላፊነት መጋራት ግዴታ ይሆንበታል፤ እስዚያ ለተፈጸሙ ወንጀሎች ሁሉ ፈጻሚዎቹን ግለሰቦች እየፈለግን እናሸክማቸው ከተባለ እንደገና ደሃው ተጠያቂ ሆኖ ሊቆም ነው፤ ለምሳሌ አንድ ሰው በአገዛዙ ሲፈለግ ወደቤቱ ሄዶ የሚይዘው ሰው፣ የሚከሰው ዓቃቤ ሕግ፣ የሚፈርድበት ዳኛ ሁሉ ምንም ሳያደረጉትም ተብሎ ለምርመራ ተብሎ የደበደቡትንና በመጨረሻም የሞት ፍርዱን የፈጸመውን ብቻ ተጠያቂ ልናደርግ ነው? አገዛዙን በተለያዩ የሥራ ድርሻዎች ሲገነቡትና ሲደግፉት የነበሩት ሰዎች ሁሉ የአገዛዙ አካል አልነበሩም ለማለት እንዴት እንችላለን? በዚህ ሂሳብ አዳፍኔም ራሱ በግሉ ፈጸመ የሚባል ወንጀል ላይኖር ይችላል፤ (መንግሥቱ ኃይለ ማርያም እኔ ዝምብም አልገድልም ብሎ የለም!) ዞሮ ዞሮ በማናቸውም አገዛዝ ለሚፈጸም ዘግናኝ ወንጀል ሁሉ በኃላፊነት የሚጠየቁት ታች ያሉት ለዕለት እንጀራቸው ሲሉ የታዘዙትን ሁሉ የሚፈጽሙት ናቸው ማለት የቆየ የፍርደ-ገምድልነት ባህላችንን ማጠናከር ነው፤ ዛሬ ዓለም በደረሰበት ደረጃ ኃላፊነት በይበልጥ የሚደለደለው በወንጀል ጠንሳሽነት፣ ቀያሽነትና አዛዥነት ላይ ነው።

ስለዚህ የአዳፍኔ አጋፋሪዎችና ታላላቅ ባለሥልጣኖች የነበሩ ሰዎች ሁኔታዎች ሲለወጡ መጻሕፍትን እየደረሱና በራድዮና በቴሌቪዥን እየተናገሩም ‹‹**ኅሊናዬ ንጹሕ ነው፤ ይቅርታ የምጠይቅበት ምክንያት የለኝም፤ ይቅርታ የምጠይቀው ማንን ነው? ወዘተ....**›› እያሉ ሲናገሩ እንሰማለን፤ አንገታቸው ላይ ያጠለቁትን የፍርሃት ሰንሰለት ደብቀውታል እንጂ አላወለቁትም፤ የአዳፍኔን የፍርሃት ሰንሰለት በአንገታቸው ላይ እንደተሸከሙ

ስለሆኑ ከአዳፍኔም ሆነ ከፍርሃቱ ገና አልተላቀቁም፤ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ በታሪክ ማስታወሻ እንደገለጹት አውልቀው ለመጣል የማይፈልጉ ሰዎች በድፍረት እየወጡ ነው፤ የፍርሃት ሰንሰለቱ ከአንገት ሊወጣ የሚችለው አዳፍኔ ባለበት ዘመን ከፍርሃት ነጻነትን በማወጅ፣ ወይም ሰንሰለቱን የያዘው እጅ ሲሰበርና የአዳፍኔን ወንጀል በንስሐ በመሻር ነው፤ ንስሐ ማለት አንድ ሰው በአዳፍኔ ሥርዓት ውስጥ በሠራበት ጊዜ በአጠቃላይ የአዳፍኔ አገዛዝ በፈጸመው ወንጀል ያለውን ድርሻና በግሉ ደግሞ የፈጸመውን ወንጀል ማውረድ ነው፤ ኅሊናን ማጠብና ማሳጠብ ነው፤ አእምሮን ማቃናትና አመለካከትን ማስተካከል ነው፤ ምን ሠራሁና እያሉ መመጻደቅ አእምሮንም፣ኅሊናንም ለማስተኛት የሚደረግ አጉል ጥረት ነው፤ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ!

ሲሾሙ ኃላፊነቱ ምንድን ነው ብለው ለመጠየቅ ያልደፈሩ ሰዎች ከወንበራቸው ሲወርዱ እኛ ምን እናድርግ! ወይም በሥርዓቱ ኃጢአት የለሁበትም ማለት የሚችሉት እንዴት ነው? ከነሱ ውጭ ሥርዓቱ እንደሌለ ሳይገባቸው ቀርቶ ነው? እነሱ የገነቡትና ደግፈው ያቆሙት ሥርዓት ወንጀሎችን ሁሉ ሲፈጽም እነሱ የት ነበሩ? ወይስ የሥርዓቱ የወንጀል ተካፋይ አለመሆናቸውን ያወጁበት ሁኔታ ነበረ ወይ? አንድ ጄኔራል ከአንድ ሃምሳ አለቃ ሰላምታ እየሰጠ ትእዛዝ ተቀብሎ ከፈጸመ በኋላ ‹‹እኔ ምን ላድርግ፤›› ምክንያት ሊሆንም፤ **መቀበል የማይገባውን ትእዛዝ ተቀብሏል፤ መፈጸም የሌለበትን ድርጊት ፈጽሟል፤ ትእዛዙን ለመቀበልም ሆነ ትእዛዙን ለመፈጸም ኃላፊነትን ለመውሰድ ወኔውን ማጣት በአንገት ላይ ከሥልጣን ጋር ያጠለቁትን የፍርሃት ሰንሰለት አለማውለቅ ነው።**

ከዚህ ወኔ ማጣት ጋር ልንረዳቸው የሚገባን ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች አሉ፤ አንደኛ የፍርሃት ሰንሰለቱ በአንገት ላይ ተጠምልሎ ራስን ከልብ በመለየቱ ወኔን ያመነምናል፤ በዚህም ምክንያት ወኔ-ቢስነት በቤተሰብም የሚተላለፍ እንዲሆን ዕድልን ይፈጥራል፤ ሁለተኛ ማኅበረሰቡ ለሥልጣን ያለውን አመለካከት በጣም ያዛባዋል፤ ሥልጣንን ከፍርሃት ጋር በጣም በማዛመድ ፍርሃትን በማኅበረሰቡ ላይ ይኮተኩታል፤ ሥልጣን በሌላ መልኩ





ከሀብት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ፍርሃትና ሀብት ተቃቅፈው ማኅበረሰቡን በሙስና ያሽመደምዱታል፤ ሦስተኛ ማኅበረሰቡ በንስሐ እየታደሰ፣ ስሕተትን እያረመ እንዲያድግና እንዲሻሻል የሚያደርግ ሁኔታ እንዳይፈጠር ያደርጋል።

በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ የሚያስደንቀኝ ነገር አለ፤ ለአንዳንድ ሰዎች ይህ በአንገት ላይ የተንጠለጠለው የፍርሃት ሰንሰለት ሥርዓቱ ፈርሶ አዳፍኔ ከዙፋኑ ተዋርዶ ከወረደም በኋላ አንቆ ይዞአቸው ይታያል፤ አንዳንድ ሰዎች ዛሬም እየተሸቆጠቆጡ በአክብሮት ስለ ‹ጓድ ሊቀ መንበር› ሲናገሩ ያስደንቃሉ፤ በእርግጥ በፍርሃት ተይዘው አይመስለኝም፤ ግን የቆየና የጠነከረ ልማድ ሆኖባቸው ይመስለኛል፤

## ትምህርትና እውቀት

ቀደም ሲል ስለትምህርት በትንሹም ቢሆን ተነጋግረን ነበር፤አሁን ስለትምህርት የምንነጋገረው ግን የተለየ ነው፤ ቁልፍም ነው፤ **በመክሸፍና ባለመክሸፍ መሀከል ያለው ልዩነት እውቀት ነው፤** በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያው ክፍል የተባለው ሁሉ ከእውቀት ጉድለት ብቻ የሚመጣ ነው፤ የሰው ልጅ በማኅበረሰብ ተደራጅቶ ሲኖር ከችግሩ እየተማረ፣ የትናንትናውን ስሕተት ዛሬ እያረመ፣ የትናንትናውን ችግር ዛሬ እየፈታ ለአዲስ ችግር አዲስ መፍትሔን እያዘጋጀ በእውቀት የሚራመድ ማኅበረሰብ ይፈጠራል፤ እውቀትን ለኑሮው ችግር መፍቻ የሚያደርግ ማኅበረሰብ የእውቀትን ጥቅም በመረዳቱ እውቀትን ያከማቻል፤ እውቀትን ይገነባል፤ ማኅበረሰቡም በእውቀት ይገነባል፤ እንዲህ ያለው ማኅበረሰብ ከድንቁርና ጋር እየተላተመ ያሸንፋል፤ ከመሀይም እምነትና አስተሳሰብ ጋር እየተላተመ ያሸንፋል፤ በዚያውም አእምሮውና የማሰብ ችሎታው ይጎለብታል።

እስከአጼ ምኒልክ ዘመን ድረስ ዓለማዊ እውቀት የሚገበይበት ትምህርት ቤት አልነበረም፤ ምናልባትም የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የመጀመሪያው ይሆናል፤ አንድ በሺህ ዓመታት የሚቆጠር ታሪክ ያለው አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ

ትምህርት ቤት በሃያኛው ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ ላይ ማግኘቱ ለታሪኩ አንካሳነት ተጨባጭ ማስረጃ ነው፤ በዚህም የተነሣ ኋላ-ቀርነት መጣ፤ እስቲ አጼ ምኒልክ የገፈፉትን ጨለማ እንይ፡-

**ውሀ በቧምባ መዘውር ማስገባት፣ የኤሌክተሪክ መብራት፣ በመንገድ ላይ የሚሄድ የሰርኪስ ባቡር፣ በሐዲድ ላይ የሚሄድ ባቡር፣ የድንጋይ ንጣፍ መንገድ፣ ብር፣ አሳድ፣ ሩብ፣ ተሙን፣ በመልካቸውና በስማቸው ማስቀረጽ፣ የብር ቤት መኪና፣ አውቶሞቢል፣ ጥይት ቤት፣ የቤት ክዳን ቆርቆሮ፣ የጽሕፈት ማተሚያ መኪና፣ ፖስታ ቤት፣ ስልክ ቤት፣ ባንክ፣ ሀኪም ቤት፣ ሆቴል፣ ... ድልድይ የባህር ዛፍ ...** [76]

የብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ ያለው አገር እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን የእድገት መሠረቶች ከጣለ ገና አንድ መቶ ዓመት ግድም ብቻ መሆኑ አንድ ዘገምተኛነት ነው፤ ያም ሆኖ ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ የተሠራውም አጥጋቢ አለመሆኑ መሠረታዊ ችግራችንን ያሳያል፤ የአክሱምን ሐውልት የከበቡት የጭቃ ጎጆዎች፣ በዓለም ብቸኛ የሆኑትን የላሊበላ ሕንጻዎች ከበው የሚገኙት ደሳሳ ጎጆዎች፣ በፖርቱጋሎቹ የቤተ መንግሥት ሕንጻዎች ዙሪያ ያሉትን ቱኩሎች እያስተያዩ ከእነዚህ ትልልቆቹ አስደናቂ ሕንጻዎች ጎን የሚገኙት ኮሳሳ የደሀዎች መኖሪያዎች በጉልህ የሚያሳዩት እውቀት ወደሕዝቡ ሳይወርድ እንደቀረ ነው፤ ከላይ እውቀትን ወደታች ለማስተላለፍ ፈቃደኛነት አልነበረም፤ ከታችም እውቀትን ለማግኘትና ለራሱ ጠቀሜታ ለማዋል አለመቻሉ በአጠቃላይ የማኅበረሰቡን መክሸፍ የሚያመለክት ነው፤ እውቀትን ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ ዋናው ድልድይ ፊደል ነው፤ ፊደል ያለው ማኅበረሰብ የተለያዩ እውቀቶችን ለልጆች ማስተላለፍ አለመፈለጉ ወይም አለመቻሉ ከላይም ሆነ ከታች የእውቀት ፍላጎት አለመኖሩን ያሳያል።

[76] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ (ብላታ)፣ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ፣ ካየሁትና ከሰማሁት፡1896-1922፣ አዲስ አበባ፣ 1999፣ ገ. 39.





ሌላም ለእውቀት ቁልፍ የሆነ ነገር ይጎድለናል፤ ለምንም ነገር መለኪያ ወይም መስፈሪያ የለንም፤ ለስፋትም ሆነ ለእርዝማኔ፣ ለርቀትም ሆነ ለጥልቀት፣ ለክብደትም ሆነ ለፈሳሽ መጠን፣ ለመሬትም ይሁን ለማናቸውም ምርት፣ ለውሀ፣ ለጠላ፣ ለጠጅ፣ ... ለምንም ነገር መለኪያ የለንም፤ **ሳይንስ የሚባለው** ዘመናዊ እውቀት ያለመለኪያ ወይም መስፈሪያ ማናቸውም ዓይነት እውቀትን ለማዳበርና ለማስፋፋት አይቻልም፣ ከዚያም በላይ ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ አይቻልም፤ ፊደል ቢኖረንም ተዛማጁን የእውቀት መሣሪያ ትክክለኛ የመለኪያ ወይም የመስፈሪያ ዘዴ ስላልፈጠርን ትክክለኛ እውቀትን ለመመዝገብና ለማስተላለፍ አልተቻለም።[77]

ስለዚህም ከመሀይም ማኅበረሰብ እምብዛም አንለይም፤ አእምሮአችንን ምን ያህል ዝቅ አድርገን እንዳጠርነው ዋናው ማስረጃ ከሺህ በላይ ትክክለኛ ቁጥር አለመኖሩ ነው! መክሸፍ! መክሸፍ! መክሸፍ! ለእውቀት መዳበር ከመለኪያ ጋር ሆኖ ቁጥር በግድ አስፈላጊ መሣሪያ ነው፤ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ከተዋወቅን በዙ ምዕተ-ዓመታት አሳልፈናል፤ ነገር ግን ምንም አልተማርንበትም።

ኢትዮጵያ የራስዋ ፊደል ባለቤት ከሆነች ብዙ ምዕተ-ዓመታት ተቆጥረዋል፤ የጊዜውን ርዝመት ስናስብ መጻሕፍት አልተጻፉም ለማለት እንችላለን፤ ፊደሉ እያለ ለመጻፍ ያልተቻለበት ምክንያት ከአዳፍኔ ሌላ ሊሆን አይችልም፤ መጻሕፍት መጻፍን መገደብ ማሰብን መገደብ ነው፤ የሀሳብን ስርጭት መገደብ ነው፤ መጻሕፍትን ካለመጻፍ ጋር የተጻፈውንም አለማባዛትና ለሰዎች እንዲዳረስ አለማድረግ አብሮ የሚሄድ ችግር ነው፤ ይህ አዳፍኔ የፈጠረው ችግር ነው፤ የኢትዮጵያን ታሪክ ከዚህ ከአዳፍኔ ተንኮል መለየት አይቻልም፤ **አዲስ እውቀት እንዳይገባ፣ አዲስ ነገር እንዳይታሰብ፣ አዲስ ነገር እንዳይፈጠር፣**

[77] ስንዝር፣ ክንድ፣ ቁና፣ ማሳ፣ ጋሻ፣ ገንቦ፣ ... ለትክክለኛ መለኪያነት አይጠቅሙም፤ ምክንያቱም ከቦታ ቦታ ይለያያሉ፤ አንድ ሜትር ከቻይና እስከአሜሪካ ያው ነው፤ ኪሎም እንደዚሁ።

የነበረው እንደነበረ ሳይናጋ ለምዕተ-ዓመታት እንዲቀጥል ማድረግ የአዳፍኔ ተልእኮ ነው::[78]

ከታች ያለው እውቀትን ለማግኘትና ለራሱ ጠቀሜታ ለማዋል እንዳይችል መደረጉ በአጠቃላይ የማኅበረሰቡን መክሸፍ የሚያመለክት ነው፤ የሕንጻዎች ሥራ እውቀት አልነበረም እንዳይባል የሚያስተባብሉ እጹብ-ድንቅ የሚባሉ ጉልህ ማስረጃዎች አሉ፤ ወይም እውቀቱ በጣም ውድ ነበር፤ ወይም ከሕዝቡ ምሥጢር ነበር፤ ግራም ነፈሰ ቀኝ ከላይ ሆነው በተሻሉ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩት ነገሥታትና መሳፍንት ሕዝቡ የተሻሉ ቤቶችን እየሠራ እንዲኖር አለማድረጋቸው ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን መክሸፍ ነው፤ እውቀት እውቀት ኑሮን ለማሻሻል በተግባር አልዋለም፤ እውቀት በትክክል አልተመዘገበም፤ እውቀት በትክክል አልተላለፈም::

<u>የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት</u>

እስቲ እዚህ ላይ ቆም ብለን በአለፉት አርባ ዓመታት ግድም በመጀመሪያ በኢትዮጵያ የአመራር ደረጃ ላይ የነበረውን የእውቀት ደረጃ እንገምት፤ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዙሪያ የነበሩት ዋነኛዎቹ ባለሥልጣኖች ትምህርታቸው ባህላዊና ሃይማኖታዊ ነበር፤ አንዳንዶቹ ትንሽ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ችሎታ ነበራቸው፤ በዓለማዊ እውቀት የጎደላቸውን በፈሪሃ እግዚአብሔርና በመንፈሳዊ እውቀት ሞልተውታል፤ ሌላውን ለመምራት የሚፈልጉት እነሱ ራሳቸውን በሚመሩበት ቁም-ነገር ነበር፤ ሆኖም የዘመናዊ እውቀትን አስፈላጊነት ጠንቅቀው ያውቁና ልጆቻቸውም እንዲማሩ ይፈልጉ ነበር፤ ምናልባት ከፍተኛ ዋጋ አይሰጡትም ነበር ይሆናል፤ የፈረንጅ አገሮችን የጎበኙ መሳፍንትና መኳንንት ከባርሜጣና አንዳንድ ልብሶች ውጭ ምንም ለውጥ በውስጣቸው የነበረ አይመስልም፤ ሲወርድ ሲዋረድ ለዘመናት የቆየውና እነሱ

---

[78] ለዚህ አንድ ጉልህ ማስረጃ ዘርዓ ያዕቆብ ነው፤ የራሱን ሀሳብ ለመጨመር ስለፈለገ ብቻ ከትግራይ ተሰዶ ሸዋ አንድ ሀብታም ቤት አስተማሪ አስቲሆን ድረስ አንድ ዋሻ ውስጥ ኖረ::





ዘንድ የደረሰው ‹‹ከእኛ በላይ ማን አለ!›› የሚል አጉል ኩራትና ለሌሎች የነበራቸው ንቀት እንደተመረገ መልሰው ይዘውት መጥተዋል::

ምናልባት የኢትዮጵያ አገዛዝ ለመጀመሪያ ጊዜ የእውቀትን አስፈላጊነት ለመገንዘብ የተገደደው በፋሺስት ኢጣልያ ወረራ ዘመን ሳይሆን አይቀርም፤ የእውቀትን ኃይልና የበላይነት በማያጠራጥር መንገድ በተጨባጭ መረዳት ግዴታ ነበር፤ ነገር ግን የበለጠ ኃይለኛ ወራሪ ጠላት ኢትዮጵያን ለመጀመሪያ የገጠማት በ1928 በፋሺስት ኢጣልያ ወረራ አይደለም፤ የናፒየር የእንግሊዝ ጦርነት ነበር፤ የአድዋ ጦርነት ነበር፤ ኢትዮጵያውያን ከሁለቱም ጦርነቶች ምንም ሳይማሩ በ1928 የፋሺስት ኢጣልያ ወረራ መጣ፤ የናፒየር ጦርነት በቴዎድሮስ ራሱን መግደል እንድናቅራራና የመሸነፉን ምክንያት ሁሉ እንድንረሳ አደረገን፤ የአድዋ ጦርነት ደግሞ አርባ ዓመታት ሙሉ እንድንፎክር ምክንያት ሰጠን፤ የሚደንቀው በማይጨውም ቢሆን በሰማይ ባይመጣና መርዝ ባይነሰንስ እያልን እንፎክራለን!

በኢጣልያ የመወረር ቁጭት የመጣው በኋላ ቀስ እያለ ነው፤ የንጉሠ ነገሥቱ መሰደድ እንደትልቅ የትግል ስልት ሲወደስ፣ የአርበኞች በየገደሉና በየዱሩ መንከራተትና መሰቃየት ተረሳ፤ የማይሆነው እየሆነ፣ የሚሆነው እየቀረ፤በአንጻሩ ለኢጣልያ የገበሩት የገዛ ወገኖቻቸውን እያሰቃዩ በሐፍረት መኖር -- ይሄ ሁሉ ተደምሮ የኢትዮጵያውያንን ኋላ-ቀርነትና ደሀነት፣ አላዋቂነትና ደካማነት ከኢትዮጵያውያን በቀር በገሀድ ለዓለም አሳየ::

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የኢትዮጵያን ልጆች ለማስተማር ዓለም-አቀፍ ግፊት ነበር፤ ዓለም-አቀፍ እርዳታ ነበር፤ ልብስና ደብተር ሳይቀር እርዳታ ይመጣልን ነበር፤ ስለዚህም ትምህርት ቤቶች በያለበት ተከፈቱ፤ አስተማሪዎች ከያለበት ከውጭ አገር ተቀጠሩ፤ በአሥራ ዘጠኝ መቶ አርባዎቹ ተማሪዎችን ወደትምህርት ቤት ለመሳብ እርሳስና ደብተር ብቻ ሳይሆን ልብስም እየተሰጠ፣ እንዲያውም በተቻለ መጠን ብዙዎቹን አዳሪ በማድረግ እዚያው እየበሉና እየኖሩ የሚማሩበት ሁኔታ

ተፈጠረ፤ ስለትምህርት የሚደረገው ማስታወቂያ በውጭም በውስጥም ከፍተኛ ነበር፤ እንዲያውም ትምህርት አንዱና ዋናው የአጼ ኃይለ ሥላሴን አርቆ-አስተዋይነትን መግለጫ በመባሉ የትምህርት ሚኒስትርን የበላይ ሥልጣን ራሳቸው መያዛቸው ይወራ ነበር።

ከሁለተኛ ደረጃ የሚወጡ ተማሪዎች እየበረከቱ በመሄዳቸው በዶር. ሉሲዬ ማት (የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ዲሬክተር የነበረው ካናዳዊ የካቶሊክ መነኩሴ) መሪነት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲ ኮሌጅ ተከፈተ፤ ብዙ የውጭ መንግሥታትም የነጻ ትምህርት ዕድል ለኢትዮጵያ ተማሪዎች በመስጠታቸው ብዙዎች በያመቱ ወደተለያዩ አገሮች በታወቁ ዩኒቨርሲቲዎች ተሰማሩ፤ ከዚህም በኋላ ብዙ የአውሮፓ አገሮችና አሜሪካም ነጻ የትምህርት ዕድል ለኢትዮጵያውያን እየሰጡ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በብዙዎች የታወቁ የአውሮፓና የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ይማሩ ጀመረ፤ ከዚያ ሲመለሱም በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ተደለደሉ፤ በነዚህ ከውጭ የተመለሱ ወጣቶች የዓባይና የአዋሽ ሸለቆዎች ጥናቶች ተካሄዱ፤ በቴሌኮሚዩኒኬሽን፣ በመብራትና ኃይል፣ በባንክ፣ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ትልልቅ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ ከነዚህም ጋር ተያይዞ የካርታና ጂኦግራፊ ኢንስቲትዩት ተቋቁሞ በዓየር የተነሣውን የዓባይ ሸለቆ የዓየር ፎቶግራፎች መመርመር ጀመረ።

ከተለያዩ የውጭ አገሮች በተለያዩ ትምህርቶች ተመርቀው የመጡት ወጣቶች በአራት መቶና አምስት መቶ ብር ደመወዝ ከልባቸው እየሠሩ ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነበር፤ በአጠቃላይ ሲታይ የእውቀት ተፈላጊነት እየጎላ በመሄድ ላይ ነበር፤ ቀስ እያለ በየመሥሪያ ቤቶቹ የተማሩት ወጣቶች ቁጥር ከስር እየጨመረ ሲመጣ ከላይ ተደላድለው ከተቀመጡት መኳንንት ጋር መጋጨት የማይቀር ሆነ፤ መኳንንቱ ለእውቀት ጎንበስ ማለት አቃታቸው፤ ወጣቶቹም ለሥራ ልምድና ለሽምግልና ጎንበስ ማለት አቃታቸው፤ 1953 ዓ.ም. የነጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ለመጀመሪያ ጊዜ የዚህን ግጭት ውጤት አሳየ፤ አገሪቱ ከሁለቱም በኩል ብዙዎችን አጣች፤ ሥልጣን በእውቀትና





በምክክር ሊሸነፍ ሳይችል ቀረ፤ **በጉልበት የተጨበጠውን ሥልጣን በጉልበት ለማስለቀቅ የተደረገው ሙከራ ከሸፈና ብዙ ሰዎችን በላ።**

## እውቀትና ሥልጣን ሲታገሉ

ምናልባት 1953 እውቀትን ጨብጠው በልበ-ሙሉነት በስዒረ መንግሥቱ የተሳተፉት በጣም ጥቂት ወጣቶች በአንድ በኩል፣ በሥልጣን ላይ የተደላደሉት መሳፍንትና መኳንንት በሌላ በኩል ቢያንስ በጥርጣሬ የተመረዙት በዚህ ዘመን ነው ለማለት የሚቻል ይመስለኛል፤ ይህ የጥርጣሬ «**ያልጠረጠረ ተመነጠረ**» በሚል ባህል ያደገውን የመሳፍንትና የመኳንንት ክፍል በስጋት ላይ መጣሉ አልቀረም፤ አጼ ኃይለ ሥላሴም በሁለቱ መሀከል ሚዛን ጠብቀው የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ ሲጥሩ፣ የተፋጠጡትን ሁለቱን ኃይሎች (የመሳፍንቱንና የመኳንንቱን በአንድ በኩል፣ በጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ የሚመራውን የተማረውን ክፍል በሌላ በኩል) ወደጎን ትቶ የወታደሩ ክፍል መሀከሉን ሰንጥቆ ፊት ለፊት ጃንሆይን ገጠመ፤ በ1953 የክብር ዘበኛ ብቻውን ከጥቂት የተማረ ኃይል ጋር ነበረ፤ በ1966 የጦር ኃይሉ በአንድነት ቆመና ክብር ዘበኛ ተዳመጠ፤ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ፍጻሜ አበሰረ፤ በ1967 እንደታየውም ፍጻሜው የአጼ ኃይለ ሥላሴ ብቻ ሳይሆን የዘውዱም ፍጻሜ ሆነ።

ብዙ ዘመናትንና ብዙ ጉዳዮችን በጥድፊያ ቃኘን፤ ዋናው ፍሬ-ነገር በዘመናውያን ወጣቶችና በሽማግሌዎቹ መሀከል ለተፈጠረው ቅራኔ ‹አንተ ይህ ችሎታ ስላላህ ይህንን አድርግ፤ አንተ ደግሞ ይህንን ስለምትችልበት አንተ ይህንን አድርግ› በማለት ሥራ ለማከፋፈልና ለኃላፊነትና ለተጠያቂነት ሕግን ማውጣት የሚችል ጠፋ፤ **ለእውቀት እውቅናን የሚሰጥ ሥልጣን ጠፋ፤ ለእውቀት እውቅናን የሚሰጥ ሕጋዊ ሥልጣን ጠፋ፤ ስለዚህም ሕገ አራዊት የእውቀትን ቦታ ያዘ፤** የኢትዮጵያ ሕዝብ እውቀትን አያውቅም፤ ሕገ አራዊትን ግን ጠንቅቆ ያውቃል፤ ስለዚህም ‹**መንግሥት› እውቅና ላልሰጠው እውቀት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት ብሎ ድጋፉን ይስጥ!** ሕገ አራዊት ግን ቆመጡን

ከፈለገም ክላሹን ይዞ የፈለገውን ያነሣል፤ የፈለገውን ይጥላል፤ የፈለገውን ያከብራል፤ የፈለገውን ያደኸያል፤ ሥልጣኑ ጠመንጃው **ነው፤ እውቀት ሥልጣን የለውም::**

እውቀት ሥልጣን የለውም፤ ይህንን ለመረዳት ስምንተኛ ክፍል መጨረስ፣ ትእግስቱ ከተገኘ አሥራ ሁለተኛ ክፍልን መጨረስ በቂ ሆኖላቸዋል፤ ለዚህ ነው አምስቱም በአንድ ዘመን የተፈጠሩ የፖሊቲካ ቡድኖች ሁሉ ማርክሳዊ-ሌኒናዊ የሆኑት፤ ለዚህ ነው የሁሉም የፖሊቲካ እምነት አንድ ቢሆንም መስማማት አቅቷቸው ሲጋደሉና ሲያጋድሉ የቆዩት፣ ለዚህ ነው ሁሉም ለሕዝብ ተቆርቋሪ መስለው የተነሡትና ሕዝብን ጉልበታቸው አድርገው ያደኸዩት::

**አገዛዝና ሕዝብ እውቀትን ከሥልጣን ውጭ ለማድረግ በተስማሙበት ማኅበረሰብ እውቀት እየደበዘዘና ጉልበት እየፈረጠመ ይሄዳል፤** በኢትዮጵያ ውስጥ በኛው ዕድሜ እውቀት ሦስት ጊዜ ከሽፏል፤ አንድ ጊዜ በ1953. ሁለተኛ ጊዜ በ1966. **በ1983 እውቀት ጉርጓድ ተቆፍሮለት ተቀበረ፤** በሥልጣን ወንበር ላይ የወጡት በጉርምስናቸው ዘመን በምርጫቸው ከትምህርት ገበታቸው ተነሥተው ወደጫካ የገቡ ሰዎች ናቸው፤ በጠመንጃ ሥልጣን የያዘውን ደርግ ወያኔ በጠመንጃ አወረደው፤ ለደርግም ሆነ በተለይ ለወያኔ እውቀት ቦታ አልነበረውም::

ወያኔ በተለይ ጸረ-እውቀት መሆኑን ገና ከገባበት ሰሞን ጀምሮ በንግግር ብቻ ሳይሆን በድርጊት ሲገልጽና ሲያሳየው የነበረው ነው፤ ገነት ዘውዴን የትምህርት ሚኒስትር ከማድረግ ጀምሮ እስከመምህራንን ከዩኒቨርሲቲ ማባረር የተደረሰው በጸረ-እውቀት ስሜት ነው፤ በወያኔ ዘመን ያለምንም ሐፍረት ማታለልና ማጭበርበር እውቀትን ተኩ፤ እአአ በ1995 ኢሰመጉ (የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ) የወያኔን የማታለል አመራር ለዓለም ለማሳወቅ ሞክሮ ነበር::[79]

[79] The Ethiopian Human Rights Council, Democracy, Rule of Law and Human Rights in Ethiopia: Rhetoric and Practice, ADDIS Abeba, March 1995. የአማርኛው ትርጉም በኅዳር 1988 ታትሟል::





የወያኔን ጸረ-እውቀት አቋም በግልጽ የሚያሳየው ማስረጃ ከዚህ በታች ያለው መረጃ ነው፤ እነዚህ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሙሉ የፕሮፌሰርነት ደረጃ የደረሱ ምሁራን በጣም በታወቁ ከአሜሪካና ከአውሮፓ ዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው የወጡና በሥራቸው ለብዙ ዓመታት እውቀታቸውን ያስመሰከሩ ምሁራን ናቸው፤ እንኳን እንደኢትዮጵያ ላለ ኋላ-ቀር አገር ይቅርና በአውሮፓና በአሜሪካም አገሮች ተወዳድረው መሥራት የሚችሉ ናቸው፤

1. ዓሥራት ወልደየስ
2. ታየ መኩሪያ
3. አየነው እጅጉ
4. ዓለማየሁ ተፈራ

እነማንና ስንቶቹ የወያኔ ባለዲገሪዎች ቢጨፈለቁና ቢጋገሩ ከነዚህ አንዱን ይወጣቸዋል?

ወያኔ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ‹‹በችሎታ ማነስ›› ብሎ ያስወጣቸው መምህራን ሁሉ በአውሮፓና በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች በመምህርነት ተቀጥረዋል፤ በእነሱ ቦታ የተተኩት የድንጋይ ማምረቻ ከሚባለው ማሠልጠኛ ጣቢያ የወጡ ናቸው፤ ልንገነዘበው የሚገባን ዋናው ነገር ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እስከወያኔ ዘመን የተካበውን እውቀትና የሥራ ልምድ በሃያ ዓመታት ውስጥ ወያኔ የእውቀትን እርምጃ እንዴት አድርጎ ገደል እንደከተተው ነው፤ ይህ የእውቀት ውድቀት ለወያኔ ስውር አልነበረም፤ ይህ የተደረገው በድንቁርና ነው፤ ነገር ግን ድንቁርናቸው እንደተጋለጠ ከዚያም ከዚህም ሲሰሙ ራሳቸውን ከአባረሯቸው ምሁራን ጋር ያስተካከሉ ለመምሰል ሲሉ ሌላ የድንቁርናቸውን መከሰቻ አሳዩን፤ በየኪዮስኩ ድግሪ በከባድ ዋጋ እየገዙ ባለዲግሪዎች ለመሆን ጣሩ! ድንቁርናውን በኪዮስክ ዲግሪ እንሸሽገዋለን ብለው ድንቁርናውን አጎሉትና ተጋለጡ! አንደኛ ከሰባተኛና ከአሥረኛ ክፍል በዝልያ ወደዩኒቨርሲቲ ግቢ አይደረስም፤ ሁለተኛ ዲግሪ ወይም ማንኛውም የትምህርት ደረጃ

ከኪዮስክ በተውሶ እንጎል አይሸመትም፤ ሦስተኛ እውቀቱ ያለው የገዙት ዲግሪ ላይ ሳይሆን ያልሄዱበት መንገድ ላይ ነው፤ የትምህርትን ነገር ረግጠው ወይም ምናልባት ረግጦአቸው ወደጫካ የሄዱ ጊዜ ያከተመ ነገር ነው፤ በ1983 ከጫካ ሲወጡ የያዙት ሀሳብ ያንኑ በ1967 ጫካ ሲገቡ የነበራቸው ነበር።

እውቀት ሥልጣን የለውም፤ ኢትዮጵያንና እንደኢትዮጵያ ያሉ ኋላ-ቀር አገሮች በድንቁርና፣ በችጋርና በበሽታ አቆራምደ በደሀነት አዘቅት ውስጥ የጨመራቸው ለእውቀት ሥልጣን አለመስጠታቸው ነው፤ ፊደል መቁጠርን እንደትምህርት ተቀብሎ ራስን ከሰው በላይ ለማድረግ መሞከር በይፋና በአደባይ በአለፉት አርባ ዓመታት ደጋግመን ያየነው ነው፤ በአሁኑ ጊዜ እየተባባሰ ነው፤ ማናቸውም ነገር ወደመክሸፍ የሚያመራው እውቀት ሥልጣን እንደሌለው ሲታወጅና እውቀት የሥልጡን ታዛዥ ባሕርይ ሲኖረው ነው።

ከአርባ ዓመታት በፊት የተፈጠሩ አምስት የፖሊቲካ ቡድኖች (ደርግ፣ ኢሕአፓ፣ መኢሶን፣ ወያኔ፣ ሻቢያ) ሁሉም ማርክሳዊ-ሌኒናዊ የሆኑት ለሥልጣን ነው፤ የሁሉም የፖሊቲካ **እምነት** (እውቀት አይደለም) አንድ ቢሆንም መስማማት አቅቷቸው ሲጋደሉና ሲያጋድሉ የቆዩት ለዚህ ነው፤ ለሕዝብ ተቆርቋሪ መስለው በእኩይና በድንቁርና አስተሳሰብ ኢትዮጵያን ወደገደል አፋፍ ያደረሷት ለዚህ ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መጨረሻ ላይ በእርሻና በሌላም የልማት ዘርፍ ከፍተኛ እድገት ከአሳየበት እያቆለቆለ የሄደው ከእውቀት ጋር የተጣሉና እውቀትም የተጣላቸው ጎረምሶች ሥልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ነው።



በእኔ ግምት ከኢጣልያን ወረራ በኋላ ኢትዮጵያን የገጠማት ዋና እንቅፋት በ1953 ዓ.ም. የነጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ ስዒረ መንግሥት መክሸፍ ነው፤ የዚህ ሙከራ መክሸፍ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ የበጀ ቢሆንም ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ እድገትን





ያሰናከለ እንቅፋት ነበር፤ በዚህ ሙከራ ውስጥ የነበሩት ሰዎች በቀጥታ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓት የወጡ ናቸው፤ ባህላዊ ሥርዓቱን የሚያውቁ፣ ዘመናዊ የፖሊቲካ አመለካከት ያላቸውና በቅን መንፈስ የተነሳሱ ናቸው፤ የዱሮውን ሥርዓት ያደገበትና ጠንቅቀው የሚያውቁት ሲሆን አዲሱንና የሚፈለገውን ዘመናዊ ሥርዓት በውጭ አገሮች ያዩና የተረዱ ሰዎች ነበሩ፤ ሳይሳካላቸው ቀረ።

በ1953 የእነጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ ሙከራ ተሳክቶ ቢሆን የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ ሌላ አቅጣጫ ይይዝ ነበር ይሆናል፤ ከላይ በሥልጣን ላይ የነበሩትና ከታች ሆነው እነሱን ለመሻር የተነሡት በብዙ መንገድ ይቀራረባሉ፤ ስለዚህም ያልሻከረ ሽግግር ለማድረግ አይከብድም ነበር ለማለት ያስደፍራል፤ ለማናቸውም ቢሆን ኖሮ ብሎ ታሪክ የለም፤ ፍሬ ነገሩ አልተሳካላቸውም ነው፤ ነገር ግን ከሃያ ዓመታት በኋላ መምህራን፣ ታክሲ ነጂዎችና ተማሪዎች በፈጠሩት ግርግር ተጠቅሞ በ1966 መጨረሻ ላይ የጦር ኃይሉ ደርግ በሚባል ስብስብ የሥልጣን ወንበሩን ያዘ።

በዚያን ጊዜ ገና በትምህርት ላይ የነበሩ ጎረምሶች አዲስ የሥልጣን ትግል ከጀመሩ ጥቂት ዓመታት ሆኗቸው ነበር፤ ደርግ በተመሠረተበት ዘመን አካባቢም በነሱ እምነት የመጀመሪያው የፖሊቲካ ፓርቲ፣ **የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ** (ኢሕአፓ) የሚባል ለመመሥረት ተቃርበው ነበረ፤ በትምህርት ላይ ያሉ ልጆችንና አንዳንድ አስተማሪዎችን አባሎች አድርገው ነበር፤ የኢሕአፓ ጎረምሶች ከአጼ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ጋር ያልተለመደ ግብግብ ለመግጠም በማኩበኩብ ላይ ነበሩ፤[80] ደርግ የሥልጣን ወንበሩን ቀድሞ ያዘባቸው።

---

[80] ዓመቱን ባላስታውሰውም በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በነበርንበት ዘመን ብርሃን መስቀልንና ዋለልኝን ጠርቼ በቢሮዬ አነጋግሬአቸው ነበር፤ ፍሬ ነገሩ በመጀመሪያ አንድ ጥያቄ፡- እናንተ ሥልጣን ነው የምትፈልጉት ወይስ ለውጥ የሚመጣበትን መንገድ ለማፋጠን ነው? እንደማያችሁ ሥልጣን የምፈልጉ ይመስለኛል፤ እናንተ አጼ ኃይለ ሥልሴ ዙፋን ላይ ለመውጣት ፈልጋችሁ እንደሆን አሁን የማይሆን ምኞት ነው፤ ዕድሜያችሁ ገና ነው፤ ወደፊት ያደርሳችኋል፤ ብያቸው ምንም ሳይናገሩ ተለያየን።

ኢሕአፓ ዋናው የትግል መሣሪያው ያደረገው የትንንሾች ልጆች ሠራዊት ነበር፤ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ ማድረግ ትልቁ ዓላማ ነበር፤ አንቀበልም የሚሉትንም ልጆች በብዙ ዓይነት ማስፈራሪያዎች በስጋት ውስጥ ይጨምሩ ነበር፤ ወላጆችም እየተጨነቁ በየትምህርት ቤቱ ለጥበቃ ማንኀበብ ጀምረው ነበር፤ በማስፈራራት ሳይሳካላቸው ሲቀር የወሰዱት የተስፋ መቁረጥ እርምጃ የአረመኔ ነበር፤ የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ዲሬክተርና (መኮንን ሽጌ) የመድኃኔ ዓለም ትምህርት ቤት ዲሬክተር (ፊቃደ ?) በኢሕአፓ የተገደሉት ‹ጥፋታቸው› ኀበዝ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ሆነው ተማሪዎቻቸው በትምህርት ቤት እንዲገኙ ማድረጋቸው ነበር፤ ትምህርት አናቆምም በማለታቸው ብቻ የተገደሉት ተማሪዎች ቁጥር ብዙ ነው።

ለኢሕአፓ ጨካኝ ግድያ ደርግ የሰጠው ምላሽ የዚያኑ ዓይነት ጨካኝ እርምጃ ነው፤ በሁለቱም በኩል **ነጭ ሽብርና ቀይ ሽብር** እየተባለ ብዙ ልጆች አለቁ፤ ብዙ ቤተሰቦችም በሐዘን ተጎዱ፤ ምሕረት በሌለበት ጭካኔ ደርግ ኢሕአፓንና መኢሶንን አጠፋቸው፤ ከስደት የመጡትም ወደነበሩበት ተመለሱ፤ ሌሎቹም በአውሮፓና በአሜሪካ አዲስ ስደተኞች ሆነው ይኖራሉ።

የኢሕአፓም ሆኑ የመኢሶን ሰዎች የእነሱ የሥልጣን ወንበር ላይ መውጣት ከከሸፈም በኋላ በሥልጣን ላይ ለወጣው ሁሉ ጥገኛ አገልጋይ መሆናቸው ዋናውን ዓላማቸውን ያሳያል፤ ለደርግም ሆነ ለወያኔ በሎሌነት አገልግለዋል፤ እያገለገሉም ነው፤ በመጀመሪያ የሥልጣን ጥሙ የበረታባቸው የኢሕአፓ ጎረምሶች ፈራ ተባ እያሉ ወደደርግ ለመጠጋት ሞከሩ፤ ከተለያዩ የአውሮፓ አገሮች የተሰባሰቡት የመኤሶን ጎረምሶች በበለጠ ቁርጠኛነት ደርግን ተጠጉ የኢሕአፓና የመኢሶን ፉክክር ደርግን አጠነከረው፤ በአንጻሩ ግን ሁለቱንም የጎረምሶች የፖሊቲካ ቡድኖች የደርግ ጥገኞች አደረጋቸው፤ ከመግደል በቀር ምንም ዓይነት ሕጋዊ ሥልጣን ደርግ ሊያጎናጽፋቸው አልፈቀደም፤ በመጨረሻም እርስበርሳቸው አጋደላቸው።





እንግዲህ በአንድ ወቅት አጼ ኃይለ ሥላሴን ለመተካት ከተመኙት ቡድኖች ውስጥ ሁለቱ ከሸፉ፤ የኢሕአፓ መሸፈትም በወያኔ ተተካና አከተመ፤ ኢሕአፓና መኢሶን የጫኑትን ትግል ለሻቢያና ለወያኔ ትተው ወደስደት ወይም ወደጥገኝነት ገቡ፤ ስለዚህም ካምስቱ ተፎካካሪዎች ሦስቱ ብቻ ቀሩ፤ ደርግ ፣ ሻቢያና ወያኔ።

የአጼ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለመጣል በተማሪ ቤት ሆኖ የተደራጀው ኢሕአፓ፣ከኢትዮጵያ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደተለያዩ የአውሮፓ አገሮች ለትምህርት በተላኩ ወጣቶች የተቋቋመው መኢሶን፣ ከሁለተኛ ደረጃና ከዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን እያቋረጡ የሸፈቱ የትግራይና የኤርትራ ወጣቶች (የኤርትራ ነጻ አውጪና የትግራይ ነጻ አውጪ የሚባሉት) የወታደሩን ኃይል በተቆጣጠረው ደርግ ተበለጡ፤ አምስቱም የፖሊቲካ ሃይማኖታቸው አንድ ነበር፤ ማርክሳዊ-ሌኒናዊ ነበሩ፤ ሆኖም ለሥልጣን ያላቸው ፍቅርና ምኞት የፖሊቲካ እምነት አንድነታቸውን ሰርዞት በከፋ ጠብ ላይ ነበሩ።

ደርግ ፈረሱ ላይ ተቀምጦ ሲጋልብ መኢሶን ተፈናጠጠ፤ የመኢሶን ዓላማ ሲመቸውና ሲያጋጥመው ጠምዘዝ ቦታ ላይ ደርግን ገፍትሮ የሥልጣን ኮርቻው ላይ ለመደላደል ነበር፤ ኢሕአፓ ግን ዓላማው ሕዝብን ይዞ ደርግንና መኢሶንን አውርዶ የሥልጣን ፈረሱ ላይ ለመውጣት ነበር፤ ደርግ አልተሞኘም ሁለቱንም ቆሻሻ ጠራጊ ከማድረግ ያለፈ ሥልጣን አልሰጣቸውም፤ በትምህርትና በዕድሜ መኢሶኖች የሚቀድሙና ከኢሕአፓ ጋር ሲነጻጸሩም በሰል ያሉ ነበሩ።

የኢትዮጵያ ሁኔታ በአምስት ቡድኖች ፉክክር የተወሳሰበ መሆኑ ሳያንስ ደርግ አሜሪካን አስወጥቶ ሶቭየት ኅብረትን የሙጥኝ አለ፤ ወያኔና ሻቢያም በፖሊቲካ እምነታቸው ወደሶቭየት ኅብረት የሚያጋድሉ ቢመስሉም ከኋላ-ቀር ሀብታም የአረብ አገሮችንም አጋርነት ይዘው ነበር፤ ስለዚህም ኢትዮጵያ ከውስጥ ሶማልያን ጨምሮ በሦስት ተገንጣይ ቡድኖች፣ ከውጭ ደግሞ ከሱዳን ጋር በሌሎች የአረብ አገሮችና በአሜሪካ ተወጥራ ነበረ፤ ደርግ የፖሊተካ ጨዋታውን አላወቀበትም፤ ስለዚህም የተደገፈው

በሶቭየት ኅብረት ላይ ብቻ ስለነበረ ሶቭየት ኅብረት ሲፈርስ ደርግም መፈራረስ ጀመረ፤ ኢትዮጵያና ሶማልያ ተቆሳሰሉ፤ ተደካከሙ።

በአሜሪካና በሱዳን ድጋፍ ወያኔና ሻቢያ እየተረዳዱ ጉልበት አገኙ፤ ውጤቱም ሁለቱ ተቀናጅተው በሲአይኤ እርዳታ ኢትዮጵያን በአጠቃላይ መቆጣጠርና የየራሳቸውን ድርሻ መውሰድ ሆነ፤ እንግዲህ ከአምስቱ ማርክሳዊ-ሌኒናዊ የሥልጣን ተፎካካሪዎች ውስጥ ሁለት ብቻ ቀሩ፤ እነዚህ የቀሩትም የፖሊቲካ ሃይማኖታቸውን ለውጠው ነበር! በኋላ ግን ሻቢያ ከሲአይኤ ጋር ተቃቃረና ሲአይኤንና ወያኔን ይበልጥ አቀራረባቸው።

የአምስቱን ተፎካካሪ የፖሊቲካ ቡድኖች (ደርግ፣ ሻቢያ፣ ወያኔ፣ ኢሕአፓ፣ መኢሶን) መጨረሻ ስናይ ኢትዮጵያን ጎዱ እንጂ አንዳቸውም አልተጠቀሙም፤ አዲስ ተረት የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ ሁሉም ጥሬ! እንዲያውም የኢትዮጵያ ጦስ ለሶማልያና ለሱዳን ተረፈ! በሶማልያ በኩል የሚታየው ከቀጠለ የኢትዮጵያ ጦስ ለኬንያም ሳይተርፍ አይቀርም፤ የትኛውም የውጭ ኃይልም የተጠቀመ የለም።

ከዚህ የምንማረው ምንድን ነው? በመቀጠል ላይ ያለው የአለፉት አርባ ዓመታት ታሪክ የሚጀምረው በአምስቱ ‹ማርክሳዊ-ሌኒናዊ› ቡድኖች የመጠፋፋት ፋክክር ነው፤ ሁሉም የአንድ ትውልድ ልጆች ናቸው፤ ዛሬ ዕድሜአቸው ከሃምሳ አምስት እስከሰባ አምስት የሚሆን ነው፤ አሁን ከታሪካቸው እንደምንረዳው አንዳቸውም ምንም ሃይማኖት ወይም እምነት የላቸውም፤ የሚነዳቸው የሥልጣንና የንዋይ ፍቅር ብቻ ነው።

ይህ ትውልድ በአንድ በኩል በሥልጣን ጥም በሌላ በኩል በጉልበት አሸንፎ በመግዛት ምኞት ተወጥሮ የተያዘና ትምህርቱን ትግል በሚለው ያቋረጠና የለወጠ፣ ጉልበት ከእውቀት ይበልጣል ብሎ ያመነ፣ አንድነት የልዩነት ማሰሪያ መሆኑን ሳይገነዘብ ስለልዩነት የሚጮህ፣ ኢትዮጵያንና አገዛዝን መለየት የተሳነው፣ ዛሬም የተለየ ሀሳብ ለመስማት የማይችል፣ በሰላም ክርክርና በመግባባት የማያምን ትውልድ ነው፤ ተምሮ እንዳልተማረ የሚሆን፤ ፈረንጅ አገር እየኖረ የጫካ አስተሳሰብ የሚያራምድ፣






በብልጣብልጥነት የሚያምን ትውልድ ነው፤ የሚያሳዝነው አሁንም ለሥልጣን የሚጠራሩትና ያንኑ የጉልበት ዘዴ ይዘው የተነሡት የዚያው ትውልድ ሰዎች ናቸው፤ ከተሳካላቸው በስድሳ ስድስት የጀመሩትን ትርምስ ለመቀጠል ቆርጠው ተነሥተዋል።

በአርባ ዓመታት ውስጥ ይህ በሥልጣንና በጉልበት የሰከረ ትውልድ በአካላዊ ጀግንነትም ሆነ በመንፈሳዊ ወኔ ያሳየው ነገር የለም፤ እርስበርስ መገዳደልና ሌሎችንም ማጋደል ዋናውና ትልቁ ሥራው ሆኖ ቆይቶአል፤ የሚያሳዝነው ይህ በሃምሳ አምስትና በሰባ አምስት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ጉደኛ ትውልድ ሁኔታዎችም ምቹ ሆነውለታል፤ ከሱ የቀደመው ትውልድ በፍቅረ ንዋይ ያበደና ማኅበራዊና ፖሊቲካዊ አቅዋሙ ወደግለኛነት ስለሚያዘነብል በፈቃዱ ከጨዋታ ውጭ ሆኖለታል፤ አሁን ደግሞ አብዛኛዎቹ አርጅተዋል፤ ተሰደዋል፤ ከሃምሳ በታች፣ ማለትም ከሠላሳ አምስት እስከሃምሳ አምስት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለው ከፍተኛ ትምህርት ለብ-ለብ ከሆነ በኋላ፣ የወጣቱ ማኅበራዊና ፖሊቲካዊ እንቅስቃሴ በደርግ ተቀጭቶ በወያኔ ተገንዞ ከተቀበረ በኋላ የመጣ በመሆኑ ለዕለት ጉርሱ ሲል በምንም ዓይነት የሎሌነት ተግባር ለማገልገል የተዘጋጀ ነው፤ የጫት መግዣ ካገኘ ራሱንም ጭምር ማንንም ምንንም በምንም ዋጋ ለመሸጥ ዝግጁ ነው፤ ይህ እውነት ከሆነ ከሃምሳ አምስት እስከ ሰባ አምስት ያለው ትውልድ የመሪነቱንና የበለያነቱን ስፍራ እንደያዘ መቀጠሉ ነው፤ እግዚአብሔር ወይ የእነሱን ልብና አእምሮ ያቃናልን፤ ወይ ከሁለቱ ተራርቀው ከሚገኙት ትውልዶች (ከ35-55ና ከ75-95) መሀከል ሰዎች ያፍራልን!

የእግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ ትክክል የሚሆነው መጀመሪያ እሱ የሰጠንን ልብና አእምሮ ጠርገንና አጽድተን ዝግጁነታችንን ስናሳየው ይመስለኛል፤ ስለዚህም የወደፊቱ እንዲሰምርልንና ጠልፎ ከያዘን የመክሸፍ አባዜ እንድንወጣ ከፍርሃትና ከድንቁርና አዙሪት ውስጥ መውጣት አለብን፤ ይህ ቀላል አይደለም፤ ፍርሃትም ድንቁርናም የግለሰብ የመሆናቸውን ያህል የማኅበረሰብም ናቸው፤ ስለዚህ መፍትሔው ሁለቱንም

በአንድ ጊዜ የሚነካና መሠረታዊ ለውጥን የሚያመጣ መሆን አለበት።

**የፍርሃትና የድንቁርና አዙሪት**




መክሸፍ በኢትዮጵያውያን ስሜትና አስተሳሰብ ውስጥ የመሸገ በመሆኑ አውቀውና ሆን ብለው ካልነቀሉት እያቆጠቆጠ ይቀጥላል፤ ለምንድን ነው አበሻ በማህበረሰብ ደረጃ ሲሆን የአገርና የወገን ፍቅር፣ በግለሰብ ደረጃ ሲሆን የግል ጥቅምና ፍቅረ ንዋይ የሚገዛው? ለምንድን ነው ከኢትዮጵያ ውጭ ያለው አበሻ አገሩን የሚናፍቅ ሲሆን ውስጥ ያለው ደግሞ የውጪው የሚናፍቀው? ለምንድን ነው ነጻነትን፣ ፍትሐዊነትን፣ እኩልነትን በእየአደባባዩ እየተመኘን በየቤታችን የማናገኘው? ለምንድን ነው የሚበልጠንን ሰው ወይም ቡድን የምንጠላው? ለምንድን ነው ከሚበልጠን መማር የማንወድደው? ለምንድን ነው የእውቀት ጠላት የሆንነው? እነዚህን ጥያቄዎች በትክክል ሳንመልስ የኢትዮጵያን ታሪክ ለመረዳት እንችላለን ወይ?

## ጅብ መጥራት

ጅብ መጥራት የእኔ ቋንቋ አይደለም፤ የአንድ የደፋት ገበሬ ስጋት መግለጫ ነው፤ ከሚያርሰው መሬት ሌላ እንዳለው





ስጠየቀው ሌላ ማሳም እንዳለው ነገረኝ፤ ለምን ያንንም እንደማያርሰው ስጠይቀው ‹እሱን ጨምሬ ባርሰው ጅብ ይጠራብኛል፤› አለኝ፤ የዚህን ገበሬ እምነትና ሀሳብ በዝርዝር ለማስረዳት ራሱን የቻለ መጽሐፍ ያስፈልገዋል፤ ባጭሩ የገለጸው፣ አገሩ ጅቦች ያየሉበት፣ ነጻነት የሌለበት፣ የሕግ ከለላ የሌለበት፣ ፍርሃት የነገሠበት አገር 'መሆኑን ነው፤ ገበሬው የገለጸው የአንድ ሰው አበሳ አይደለም፤ የአንድ ማኅበረሰብ፣ የአንድ አገር አበሳ ነው፤ መክሸፍ በግዴታ ከመጫኑ በፊት መክሸፍን በውዴታ መቀበልም ባህል መሆኑን ያረጋግጣል፤ በግዴታ የሚቀበሉት መክሸፍ ያሳምማል፤ በውዴታ ሲሆን ቀለል ይላል፤ የጅቡን መኖር ከማወቅ ጋር ጅብን መፍራትን እንድንቀበል ያደርጋል፤ ።

ልብ በሉ፤ ጅብ መኖሩን ማወቅ ትልቅ ነገር ነው፤ አንድ ሰው፣ ወይም አንድ ማኅበረሰብ ያለበትን አደገኛ ሁኔታ ማወቅ ነው፤ እንግዲህ ጥያቄው ይህ አደገኛ ሁኔታ (ጅብ) መኖሩን ማወቅ ጥቅም አለው ወይ? ለደፋቱ ገበሬ ጥቅሙ ከአንድ ማሳ በላይ መሬት እንዳያርስ ማድረግ ነው፤ የበለጠ መሬት ቢያርስና የበለጠ ምርት ቢያገኝ ጅቡ ይጋራዋል፤ ስለዚህ ከጅቡ ዝርፊያ ለማምለጥ ደሀ መሆን የተሻለ መስሎ ታይቶታል፤ ገበሬው ለፍቶ ባመረተው ሌላው የሚከብርበት ምክንያት የለም፤ ስለዚህም የገበሬው ምርቱን የሚያርሰውን መሬት በመቀነስ ምርቱን መቀነሱ ራሱን ለማደህየት ሳይሆን ጅቡን ላለማበልጸግ ነው፤ በሌላ አነጋገር፣ ከጅቡ ማምለጥ የሚቻለው ምንም ሳይኖረኝ ሲቀር ነው፤ ከሌለኝ ጅቡ አይመጣብኝም፤ ስለዚህም በባህላዊው አባባል **አህያ የለኝ ከጅብ አልጣላ** በሚለው መመሪያ መኖር አለብኝ ማለት ነው።

ይህንን የምታነቡ ሁሉ እንድትወያዩበት እጋብዛለሁ፤ የደፋቱ ገበሬ የወሰነው፣ ማለት ጅቡን ላለማበልጸግ ሲል ራሱን ለማደህየት የመረጠው በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ነው? መቼም ያለምንም ጥርጥር ገበሬው በፍርሃት ቆፈን ተይዟል፤ ስለዚህም እንደልቡ ለመሆን ነጻነት የለውም፤ የጅቡን ጥቃትና ጭቆና የሚያቀልለት ሕጋዊ ሥርዓት የለም፤ ነጻነት ባለመኖሩ ሀሳቡን እንደልብ እየገለጹ በስብሰባ ለመወያየትና ለመደራጀት ዕድሉ የለም፤ ስለዚህም ለሚተባበርና የኅብረት እርምጃን

ለመውሰድ አይቻልም፤ ስለዚህም እያንዳንዱ በፍርሃት ቆፈን የተተበተበና ነጻነት የሌለው ሰው በጅቡ ወይም በአዳፍኔ ፍላጎት እየተመራ መኖር ነው፤ ከዚህ ለመውጣት ከፈለገ ምን ማድረግ ያስፈልገዋል?

እውቀት የተጠላበት፣ እውነትና ሕጋዊ ሥርዓት የማይፈለግበት፣ ነጻነት የሌለበት፣ በአደባባይ መነጋገርና መወያየት የማይቻልበት፣መደራጀት የማይፈቀድበት የአዳፍኔ የጭካኔ አገዛዝ ውስጥ ሌላ ምርጫ አለ ወይ?

ለእኔ እንደሚመስለኝ ከአዳፍኔ የጭካኔ ጭቆና ለመውጣት የእኔ **አሠርቱ ቃላት** የሚከተሉት ናቸው፡ --

1. ነጻነት -- ከጭቆናና ከፍርሃት፣ ከደሀነትና ከረሀብ፣ በማናቸውም መንገድ ሀሳብን የመግለጽ፣ የመሰብሰብና የመደራጀት፣ ለመንግሥት ሥልጣን ለመምረጥና ለመመረጥ፣
2. ትምህርትና እውቀት -- የመማርና የመመራመር መብት ያለምንም ልዩነት ለዜጎች ሁሉ ማዳረስ፣ መጻሕፍትን፣ መጽሔቶችን፣ ጋዜጦችን በርካሽ የማሳተምና የማሰራጨት መብት
3. ሥራና ሀብት -- ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ በብልሃቱና በጥበቡ ሠርቶ ወይም ፈጥሮ ሀብት የማፍራትና የአገርን ልማት ማፋጠን
4. ፍትሕና እኩልነት -- ማንም ኢትዮጵያዊ በአገሩ ሥልጣንና በአገሩ ሀብት የመጠቀም ዕድሉ የምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት ሚዛናዊና ያልተዛነፈ መሆኑን ሕግ የሚያረጋግጥለት
5. ማደግና መሻሻል -- ማንም ኢትዮጵያዊ በግሉም ሆነ ከሌሎች ጋር በመተባበር ሀብትና ንብረት እያፈራ የማደግና የመሻሻል እንቅስቃሴ መብቱ ሲሆን ለማኅበረሰቡም ያለበትን የኃላፊነት ግዴታም አጣምሮ እንዲመለከት
6. የማኅበረሰቡ ሰላም --
7. የማኅበረሰቡ ኅብረት





8. የማኅበረሰቡ የአካል፣ የአእምሮ፣ የመንፈስ ጥንካሬ
9. የማኅበረሰቡ የሥልጣን ባለቤትነት
10. አዳፍኔን መሻርና እንዳይመለስ ማረጋገጥ

# ማስታወሻ

ለኢትዮጵያ ህልውና ሲሉ፣ ለኢትዮጵያውያን ክብር ሲሉ፣ ማለት ለእኛ በኢትዮጵያዊነት ለምንኮራው ሁሉ፣ በኢትዮጵያዊነት ለምንከበረው ሁሉ ሕይወታቸውን የሰጡ ሰዎች አሉን፤ አቡነ ጴጥሮስ ልዩ ኢትዮጵያዊ ናቸው፤ መስቀላቸውን ይዘው ከኢጣልያ መትረየስ ጋር ፊት ለፊት የተጋፈጡና ያሸነፉ መንፈሳዊ አባት ናቸው፤ በአለፉት መቶ ዓመታት ውስጥ፣ ምናልባትም ከዚያም በፊት ለረጅም ጊዜ፣ ኢትዮጵያ እንደጴጥሮስ ያለ መንፋሰ-ጠንካራ የመንፋሳዊ አባት የነበራት አይመስለኝም፤አቡነ ጴጥሮስ ኢትዮጵያዊነትን ወደከፍተኛ ደረጃ ሰቅለውታል፡፡

እንደዚህ ያሉ ሰዎች በሌሎች አገሮች ስማቸው በልዩ የክብር መዝገብ ላይ ተጽፎ ከትውልድ ወደትውልድ ይተላለፋል፤ ለተከታታይ ትውልዶችም አርአያ እንዲሆኑ ገድላቸው በአደባባይ ይነገራል፤ የኢትዮጵያ ሰማዕታት ይህንን ዕድል አላገኙም፡፡

እንዲያውም ከጠላት ጥይት ያመለጡትን እኛ ገድለናቸዋል፤ ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህል አበበ አረጋይ፣ መስፍን ስለሺ፣ በላይ ዘለቀ፤ እነዚህ ከገደልናቸው ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው፤ በቁም የገደልናቸው ደግሞ በጣም ብዙዎች ናቸው፤በደሀነትና በበሽታ የደቀቀ ኑሮ ውስጥ እንዲኖሩ ያደረግናቸው የማናውቃቸው ሞልተዋል፡፡

ራስ አበበ በ1953 ዓ.ም. በቀድሞው የአጼ ኃይለ ሥላሴ ቤተ መንግሥት በዛሬው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በጥይት ተደብድበው ተገደሉ፤ ይበልጥ የሚያሳዝነው ደግሞ ለኢጣልያ ከገበሩ ባንዶች ጋር በአንድ ላይ መገደላቸው ነው፤ አንድ የእንግሊዝ ጸሐፊ ራስ አበበን የዓለም የመጀመሪያው ጀግና ብሏቸዋል፤ ቢትወደድ አስፍሐ ደግሞ ለእኔ እንደነገሩኝ እንደራስ አበበ ያለ ጀግና፣ ፍትሕና ርትዕ አዋቂ፣ ማድላት የሚባል ነገር የማይታይባቸው አስተዳዳሪ፣ በንዴና በቁጣ ሰውን የማስደንገጥ በሕርይ የሌላቸው፣ ሁሉንም ‹‹ጌታዬ ነህ›› እያሉ የሚያናግሩ





ትልቅ ሰው ነበሩ፤ ቢትወደድ አስፍሐ ባንዳ ቢሆኑም ናዚ ወደአገሩ ሊወስዳቸው ቢፈልግም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተው ለብዙ ዓመታት ከራስ አበበ ጋር በተለያዩ ቦታዎች ሠርተዋል፤ ስለዚህም በጣም ያውቋቸዋል፡፡

በላይ ዘለቀ የአርበኝነት ድካሙ ሳይወጣለት ከስደተኛው ንጉሠ ነገሥት ጋር ቅራኔ ውስጥ ገባ፤ እንደሰማሁት በደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ የተመራ ጦር በበላይ ላይ ዘምቶ እንዲይዘው ተደርጓል፤[81] ለማናቸውም ተይዞ እንደተራ ወንጀለኛ ከታሰረበት ሲያመልጥ እንደገና ተይዞ በአዲሱ ከተማ ከሌሎች ጋር ተሰቀለ፤ አርበኛውን ባንዶች ገደሉት፡፡

ስለኢትዮጵያ አርበኞች በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ ሊባል የሚቻለውን ያህል ተብሏል፤ ከዚህ ቀጥሎ ፎቶግራፎቻቸው የሚታዩት ባጋጣሚ በተገኙ ናቸው፤[82] ኢጣልያኖች የተማሩ ኢትዮጵያውያንን እንዳውሬ እያደኑ ይገድሉ በነበረበት ጊዜ እነዚህን ወጣቶች ከመግደላቸው በፊት እያንዳንዳቸውን ለመዝገባቸው ያነሡአቸውን ዘጠኝ ፎቶግራፎች ለማሳወቅ ነው፡፡

ማንነታቸውን መረጃው ባለኝ መጠን ባጭርባጭሩ አመለክታለሁ፤ በትልልቆቹ ለመጀመር ደጃዝማች ወልደ አማኑኤልን የሚያውቅ ሰው አላገኘሁም፤ ከወጣቶቹ ጋር ለሞት የተሰለፉበትም ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡

አቶ **በሻህውረድ ሀብተ ወልድ** የመርሐቤቴ ሰው ሲሆኑ የኔ ልጆች ወንድ አያት ናቸው፤ ሴት አያታቸው **ወይዘሮ ማራ ገብረየሱስ** የአድዋ ሰው ናቸው፤ አቶ በሻህውረድ በአሜሪካ በኦሀዮ ተምረው የተመለሱ ነበሩ፤ አጼ ኃይለ ሥላሴ ወደአውሮፓ ሲሸሹ እሳቸውና **ሻቃ በልሁ** አብረው ሄደው ነበር ይባላል፤ ነገር ግን ሁለቱም ሳይቆዩ ወደአገራቸው ተመለሱ፤ ለኢጣልያ ለመገበር ፈቃደኛ ባለመሆናቸውም በጣም ከአሰቃዩአቸው በኋላ በጭካኔ ገደሏቸው፡፡

[81] በዚህ ዘመቻ እንዲከተቱ የታዘዙ ሌላ አርበኛ ጦሙይን አልወጋም፤ አሻፈረኝ ማለታቸውን ሰምቻለሁ፡፡

[82] እነን በጣም አመሰግናለሁ፡፡

1. አቶ በሻህ ውረድ በተ ወልድ

2. አቶ መሸሻ ገብሩ ፡ የሆለታ መኮንን፣ ምናልባት የከንቲባ ገብሩ ልጅ፣ የአሥራ ዘጠኝ ዓመት ወጣት

3. አቶ ብንያም ወርቅነህና 3. አቶ ዮሴፍ ወርቅነህ በእንግሊዝ አገር በከፍተኛ ትምህርት ላይ የነበሩ ወደኢትዮጵያ መጥተው የተያዙ

አቶ ዮሴፍ ወርቅነህ

5. አቶ ደስታ ወልደ ኢየሱስ፡ የሆለታ መኮንን የነበረ፤

6 አቶ ዮሐንስ በሩ

7. አቶ ተክለ ማርያም ወልደ ገብርኤል፡

8. ደጃዝማች ወልደ አማኑኤል

9. አቶ አሰፋ አድማሱ፤ የሆለታ መኮንን የነበረ፤

10. አቶ አሰፋ ተድላ፣ የሆለታ መኮንን፤

11. ሺቃ በልሁ

12. አቶ ደበበ ገብሩ

ስለነዚህ ሰዎች የምታውቁ ሰዎች በተቻላችሁ መንገድ ሁሉ መረጃው ይፋ ብታደርጉት ለሞቱት ውለታ እንደሠራችሁ ይቆጠርላችኋል።








አቶ በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ
(1)



አቶ በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ
(1)




መሸሻ ገብሩ
(2)



ብንያም ወርቅነህ
(3)



ዮሴፍ ወርቅነህ
(4)




ደስታ ወልደ ኢያሱስ
(5)



አዳፍኔ ፍርሃትና መክሸፍ



ዮሐንስ ቦሩ
(6)




ተክለ ማርያም ወ. ገብርኤል
(7)



ደጃዝማች ወልደ አማኑኤል



አሰፋ9)



አሰፋ ተድላ
(10)



ሻቃ በልሁ
(11)



ደበበ ገብሩ
(12)



አሰፋ ተድላ
(10)



ሻቃ በልሁ
(11)



ደበበ ገብሩ
(12)



አዳፍኔ ፍርሃትና መክሸፍ

## ለንባብ


1. ተክለ ጻደቅ መኩሪያ፣ ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት፣አዲስ አበባ፣ 1982
2. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት፣ አዲስ አበባ 1981
3. ተወልደ ትኩእ፣ የኢትዮጵያ አንድነትና ኢጣልያ፣ አዲስ አበባ፣ 1990
4. ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ፣ የአናብስት ምድር፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት የታሪክ ዘገባ (ከ1927-1983 ዓ.ም.) አዲስ አበባ፣ 1999.
5. ኮሞዶር ጣሰው ደስታ፣ የኢትዮጵያ አንድነት፣ ትዝታና ትግል፣ ሃይ ፖይንት ኖርዝ ኖርዝ ካሮላይና፣ 1990 ዓ.ም.
6. ዶር. አሰፋ ነጋሽ፣ ተደብቆ የቆየው የኢሕአፓ ታሪክ ገጽታ፣ ታኅሣሥ 2/2006፣ አምስተልፌን
7. ብርሃነ መስቀል ረዳ ወልደ ሩፋኤል፣ ለፖሊስ የሰጠው ቃል፣ ጳጉሜን 2/1969
8. ኃይሌ ፊዳ ኩማ፣ ለደኅንነት የሰጠው ቃል፣ 1/10/71
9. ተድላ ዘዮሐንስ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፡ ከወልወል እስከጎንደር፣ ግንቦት 1927-ኅዳር 1934ዓ.ም.፣ አዲስ አበባ፣ 2004.
10. ጃገማ ኬሎ የበጋው መብረቅ (የሕይወት ታሪክ) ፍቅረ ማርቆስ ደስታ እንደጻፈው አዲስ አበባ በ2001 ዓ.ም
11. ሺፈራው መንገሻ፣ የሻቃ በቀለ ወያ ታሪክ፡ «የትውልድ አርአያ»፣ አዲስ አበባ፣ 1993.
12. ስንዱ ገብሩ፣ የልቤ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ 1942.
13. ጳውሎስ ኞኞ ፣ ኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት፣ አዲስ አበባ፣ መስከረም 1980 ዓ.ም
14. ጳውሎስ ኞኞ፣ አጤ ምኒልክ፣ አዲስ አበባ፣ 1984 ዓ.ም.
15. መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን መንግሥት ፣ አዲስ አበባ፣ 1994
16. ጳሓፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፣ ታሪክ ዘመነ ዘዳግማዊ፡ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፡ አዲስ አበባ 1959 ዓ.ም
17. ማም ውድነህ፣ አሉላ አባ ነጋ፣ ታሪካዊ ልቦለድ፡
18. ሜጀር ጄኔራል ነጋ ተገኝ፣ የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት አመሠራረት፡ 1855- 1974 ቶሮንቶ፣ ካናዳ፣ እአአ 1993.
19. ገሪማ ታፈረ ዘብሔረ ጐንደር፣ ጐንደሬ በጋሻው፣ አዲስ አበባ፣ 1949
20. ገሪማ ታፈረ፣ አባ ታጠቅ ካሣ፡ የቋራው አንበሳ፣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ፣ 1961
21. ብርሃኑ ድንቄ፣ ከወልወል እስከ ማይጨው፣ አዲስ አበባ፣ 1942.

22. ጥንታዊት ኢትዮጵያ አገራዊ የጀግኖች ማኅበር፣ ማኅበረ ስማዕታት መዋዕያን መሠረታዊ ደንብ፣ አዲስ አበባ ---- ዓ.ም
23. በመቅደላ ታሪኩ ዓይኔ፣ ጀግና አንድ ቴዎድሮስ ቆራጥ እንደጴጥሮስ፣ ብርጋዲየር ጄኔራል ታሪኩ ዓይኔ፡ 1931 – 1980፣ ?1995?
24. ቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ፣ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ (አባመላ) 1844-1919፣ አዲስ አበባ፣ 1997
25. አልቤርቶ ስባኪ፣ ትርጉም በአምሻው ዓለማየሁ፣ ኢትዮጵያ፡ በኢጣልያ ፋሺስት የወረራ ዓመታት፡ 1928-1933፣ አዲስ አበባ፣ 2002
26. Institute of Ethiopian Studies, The Centenary of Dogali: Proceedings of the International Symposium, Addis Abeba-Asmera, 1987
27. Alberto Sbacchi, Legacy of Bitterness: Ethiopia and Fascist Italy, 1935-1941, Lawrenceville (NJ), 1997.
28. Mesfin Wolde-Mariam and others, Welenkomi: A socio-Economic and Nutriotional Survey of a Rural Community in yhe Central Highlands of Ethiopia, The World Land Use Survey Publication, Tonbridge, 1971.
29. Haggai Erlich, Ethiopia and Eritrea During the Scramble for Africa: A Political biography of Ras Alula, 1875-1897, African Studies Center, Michigan State University, East Lansing, 1982.





# ዝርዝር ማውጫ

ወያኔ፣9, 10, 20, 23, 28, 31, 35, 36, 37, 45, 56, 64, 66, 73, 81, 87, 91, 125, 134, 138, 141, 151, 186, 187, 202, 213, 217, 238, 253, 254
ኤርትራ፣9, 23, 27, 29, 69, 83, 90, 134, 146, 149, 151, 193, 240
ኢትዮጵያዊነት፣15, 22, 23, 26, 33, 34, 37, 149, 156, 172, 186, 187, 189, 193, 195, 196, 205, 211, 217
ትግሬ፣..............22, 23, 26, 28, 69, 193
ነጻነት፣7, 8, 17, 19, 23, 24, 35, 49, 52, 54, 55, 56, 57, 58, 90, 98, 132, 150, 156, 192, 210, 220, 245, 262
ታሪክ፣9, 10, 11, 12, 15, 17, 19, 21, 22, 23, 24, 25, 26, 27, 29, 33, 34, 35, 36, 37, 38, 39, 41, 45, 46, 62, 63, 64, 66, 68, 69, 70, 82, 84, 85, 86, 90, 91, 94, 97, 98, 99, 100, 101, 108, 110, 112, 113, 130, 131, 132, 134, 138, 142, 145, 149, 150, 151, 155, 156, 157, 159, 160, 161, 162, 164, 165, 167, 170, 171, 172, 173, 174, 175, 176, 177, 178, 179, 180, 184, 185, 187, 188, 194, 195, 197, 200, 208, 209, 210, 212, 216, 218, 219, 220, 226, 227, 228, 230, 231, 234, 235, 237, 245, 247
ነገ 4, 5, 7, 9, 10, 11, 12, 13, 15, 16, 17, 18, 19, 21, 23, 24, 25, 26, 27, 28, 29, 33, 34, 36, 37, 38, 39, 40, 42, 43, 45, 46, 47, 50, 51, 53, 54, 55, 56, 57, 60, 62, 63, 64, 65, 66, 67, 70, 71, 72, 73, 74, 75, 78, 79, 80, 81, 82, 83, 84, 85, 87, 88, 90, 91,먼92, 94, 96, 98, 99, 100, 106, 108, 109, 110, 111, 112, 113, 115, 116, 118, 119, 121, 122, 127, 128, 130, 131, 132, 134, 142, 143, 144, 145, 146, 147, 149, 154, 155, 156, 157, 160, 162, 164, 166, 167, 168, 170, 171, 172, 173, 174, 175, 176, 178, 179, 180, 181, 182, 183, 184, 186, 187, 188, 189, 190, 192, 193, 195, 197, 198, 205, 206, 209, 210, 211, 212, 213, 215, 216, 217, 219, 220, 221, 222, 223, 224, 225, 227, 228, 229, 230, 231, 234, 236, 237, 238, 239, 240, 241, 243, 244, 246, 248, 249, 250, 252, 254, 255, 256, 257, 259, 260, 262, 272, 273
ጎሣ፣12, 14, 15, 16, 22, 23, 24, 25, 26, 33, 59, 146, 147, 200, 210, 229
ፖሊቲካ፣9, 20, 22, 25, 27, 29, 30, 37, 39, 63, 64, 133, 211, 212, 216, 233, 239
አገዛዝ፣9, 18, 21, 22, 24, 25, 28, 31, 32, 35, 36, 44, 45, 52, 56, 66, 67, 68, 70, 75, 77, 80, 82, 83, 85, 125, 141, 156, 169, 200, 244, 245, 250, 253
አማራ፣22, 23, 28, 74, 84, 141, 147, 150, 190, 237, 238
ዜግነት፣......................12, 22, 23, 26, 244
እርሻ20, 21, 38, 44, 54, 110, 116, 129, 187, 255
ባህል፣9, 10, 20, 21, 31, 33, 37, 38, 49, 64, 71, 87, 98, 101, 107, 109, 111, 134, 164, 167, 171, 192, 195, 207, 208, 239, 240, 241, 243, 252, 262
ሥልጣን፣9, 19, 20, 21, 29, 30, 31, 37, 44, 58, 64, 66, 73, 76, 82, 83, 87, 156, 175, 177, 186, 189, 190, 191, 192, 199, 222, 239, 243, 246, 251, 252, 253
ሃይማኖት፣19, 20, 21, 26, 53, 54, 55, 57, 82, 83, 146, 147, 189, 190, 191, 193, 197, 210, 231, 233, 244
ወሎ፣.................21, 26, 79, 82, 139, 232
ትምህርት፣7, 8, 10, 12, 15, 17, 18, 20, 21, 25, 35, 37, 39, 42, 44, 51, 52, 53, 54, 55, 56, 57, 58, 59, 63, 66, 75, 86, 89, 98, 108, 111, 120, 134, 139, 146, 149, 163, 164, 169, 171, 180, 210, 211, 218, 240, 246, 247, 250, 251, 253, 255
ቤተ ክርስቲያን፣20, 53, 175, 214, 222, 237
እውቀት፣7, 8, 9, 10, 17, 20, 26, 37, 51, 52, 53, 54, 56, 57, 58, 59, 66, 78, 81, 82, 88, 90, 92, 93, 97, 98, 99, 101, 107, 112, 113, 179, 191, 208, 209, 210, 214, 218, 220, 221, 224, 226, 227, 229, 232, 234, 238,

240, 242, 246, 247, 249, 250, 251, 252, 253, 254, 274
ትውልዶች፣17, 18, 19, 32, 33, 36, 44, 46, 65, 66, 80, 91, 92, 93, 94, 95, 96, 101, 108, 134, 164, 165, 173
አሜሪካ፣12, 13, 14, 19, 27, 29, 35, 48, 65, 66, 70, 73, 80, 92, 108, 110, 111, 134, 200, 214, 215, 241, 251, 254
ስደት፣18, 29, 34, 36, 37, 40, 71, 130, 134, 138, 140, 141, 155, 156, 180, 188
ለውጥ፣13, 18, 28, 30, 31, 37, 39, 45, 55, 56, 60, 62, 63, 100, 101, 107, 108, 109, 121, 236, 240, 249
ጭቆና፣ ...........18, 24, 25, 162, 178, 196
ኋላ-ቀርነት፣17, 58, 81, 94, 172, 175, 232, 234, 250
ሽለላ፣ ..............................17, 32, 33, 97
ፉከራ፣..............................17, 32, 33, 97
አረብ፣..............................17, 20, 110, 140
ችጋር፣.16, 21, 45, 77, 78, 79, 80, 218
ጋቢ፣ ........................16, 19, 21, 174, 227
አሮምኛ፣ ..........................................15, 26
ደርግ፣15, 24, 26, 28, 30, 31, 35, 36, 37, 42, 45, 47, 54, 55, 56, 66, 67, 69, 71, 72, 73, 74, 77, 81, 84, 86, 87, 88, 96, 111, 125, 134, 141, 169, 172, 178, 199, 213, 219, 221, 227, 228, 239, 240, 244, 246, 247, 253
ትግራይ፣9, 15, 23, 45, 72, 79, 80, 82, 86, 91, 122, 136, 138, 139, 148, 149, 151, 155, 240, 249, 258
በሽታ፣ .....14, 49, 56, 78, 101, 207, 221
አውሮፓ፣14, 19, 39, 62, 70, 80, 91, 251, 254
ደቡብ አፍሪካ፣12, 13, 35, 48, 75, 126, 167
ሐውልት፣.................13, 35, 68, 97, 247
ህንድ፣.................12, 13, 27, 29, 210, 241
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣9, 10, 12, 17, 53, 87, 130, 154, 155, 206, 209, 210, 241, 254
ማይጨው፣11, 40, 66, 79, 82, 132, 158, 161, 162, 228
ኬንያ፣....10, 35, 48, 60, 126, 195, 259
አዳፍኔ፣8, 29, 31, 42, 44, 46, 47, 48, 49, 50, 51, 52, 55, 56, 57, 58, 81, 85, 107, 108, 141, 149, 241, 242, 243, 244, 245, 246
አርበኞች፣3, 5, 7, 36, 40, 66, 71, 82, 85, 116, 117, 118, 119, 120, 121, 122, 123, 124, 125, 127, 130, 131, 132, 133, 134, 136, 138, 143, 148, 150, 151, 155, 156, 157, 193, 228, 250
ድንቁርና፣7, 9, 56, 96, 97, 101, 221, 239, 247, 254
መሬት፣5, 48, 49, 64, 69, 72, 78, 79, 97, 98, 100, 112, 115, 116, 166, 186, 189, 200, 214, 215, 248, 262
ትናንት፣4, 24, 25, 64, 65, 66, 67, 69, 71, 72, 73, 74, 78, 79, 80, 81, 88, 90, 96, 215, 247
ጎሠኝነት፣4, 19, 59, 60, 97, 146, 149, 218
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፣9, 10, 12, 87, 206, 209, 210, 241, 254
ታንዛንያ፣ ....................................10, 18, 48
ፋሺስት ኢጣልያ፣3, 5, 36, 117, 120, 122, 127, 128, 132, 138, 142, 146, 147, 154, 155, 157, 163, 250
ማርክሳዊ-ሌኒናዊ፣ .............9, 19, 31, 239
ጋና፣ ................................................3, 10, 136
ሀርቨርድ ዩኒቨርሲቲ፣ ..............................14
ኃይለ ማርያም ማሞ፣.............................119
ሕወሓት-ወያኔ፣ ......................................128
ሕዝብነት.......................18, 161, 167, 177
ለማ ወልደ ገብርኤል፣ ..........................133
ልዕልት የሻሸ ወርቅ፣ ............................241
መለስ፣45, 60, 68, 70, 71, 73, 74, 75, 80, 91, 111, 160, 171, 181, 186, 187, 190, 199, 206, 207, 213, 217, 221, 234
መሸጦነት፣.....................................81, 209
መብራት ኃይል፣.....................................135
መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፣42, 221, 241, 245
መኤሶን፣......................................128, 258
መኮንን ወልደ አምላክ፣..............................7
ማሠልጠን፣..............................................51
ማርቲን በርናል፣ ......................................110
ማርክሲስት-ሌኒንስት፣ ...............................9
ማዕርጉ በዛብህ፣ ...........5, 159, 207, 218
ሰለሜ ገብረ እግዚአብሔር፣...............120
ሰይፉ ፈለቀ፣ ..........................................86
ሱዳን፣ .....................................................13
ሣህለ ሚካኤል (ኮሎኔል)፣......................86
ስታሊን፣.................................................19
ስደተኛነት፣132, 134, 140, 141, 142, 156
ሶቅራጥስ፣ ..............................65, 70, 75
ራስ ኃይሉ፣ ........131, 139, 145, 146, 148
ራስ ሥየም፣ ..........................................146
ራስ ሥዩም...45, 80, 82, 139, 145, 146
ራስ አበበ አረጋይ፣ ...............................119
ራስ እምሩ፣ .................................29, 86, 241
ሮበርት ኡኮ፣ ...........................................10





ሸዋ፣26, 33, 121, 122, 123, 176, 179, 235
ሻቢያ፣.....128, 151, 240, 255, 258, 259
ሸመና፣ .....................................................21
ቂጣ፣ ..........................................................16
ቃል ኪዳን፣ ..............................33, 112, 142
ቆርጮ፣ ......................................................16
ቢትወደድ መኮንን፣ ...................................241
ቢትወደድ ዘውዴ፣ ....................................157
ባህላዊ ትምህርት፣ ..........53, 54, 55, 56
ባህላዊው ትምህርት፣ .................................54
ባንዳነት፣132, 134, 140, 141, 142, 146, 149, 155, 156
ባንዶች፣30, 36, 47, 72, 120, 130, 132, 133, 134, 142, 149, 150, 151, 155, 156, 157, 159
ቤተ መስጊድ፣ .............................................20
ብሉኮ፣ ......................................................16
ብላታ አድማሱ ረታ፣ .................................30
ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፣44, 153
ብሪታንያ፣ ...................................13, 209
ብርሃኑ ዘሪሁን፣ ........................................44
ተድላ ዘዮሐንስ፣ ....86, 116, 118, 119, 143
ተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤት፣.......................7
ተፈሪ ሻረው፣ ..........................................133
ቴሌኮሚዩኒኬሽን፣ ......................134, 251
ትጥቅ መፍታት፣........................................125
ትጥቅ ማስፈታቱ፣ ....................................125
ናኦሚ ቾምስኪ፣ .........................................111
ናይጀርያ፣ ..................................................10
ናፒየር፣........................................66, 250
ንዋይ ገብረ ጻድቅ፣ .....................................7
ንጉሥ ሚካኤል፣..........................................82
ንግሥት ዘውዲቱ፣ .......................................46
አለማሽ፣....................................................73
አልጄርያ፣ .......................................35, 126
አምባሻ፣ ...................................................16
አሰፋ ለማ፣ ..............................................133
አሰፋ ማሩ፣.....................................73, 75
አስኳላ፣.....................................................53
አሰፍሃ ወልደ ሚካኤል፣..........................133
አርመኖች፣................................................35
አርበኝነት፣40, 85, 115, 116, 121, 132, 133, 134, 138, 142, 146, 151, 156, 165
አርኖልድ ቶይምቢ፣ ...................................66
አቃ ሰለባ፣ ...............................................136
አበሻ፣.......................................................16
አቡነ ጴጥሮስ፣ .................................67, 142
አባ ተክለ ማርያም፣ ...................................144
አባ ጀቢር አባ ጅፋር፣ ................................144
አብቹ፣.....................................132, 158
አብዲሳ አጋ፣ .........................................3, 136
አቶ አበበ ረታ፣ .................................22, 241
አቶ አበበ ዘገኑ፣ .......................................144
አቶ ይልማ ዴሬሳ፣ ..........................22, 241
አድማሱ ረታ፣...........................................133
አድዋ፣11, 79, 82, 149, 161, 162, 228, 250
አድዋ ጦርነት፣ ........................11, 117, 250
አጼ ምኒልክ፣53, 82, 161, 209, 229, 247
አፈ ንጉሥ ገብረ መድኅን፣ ...................86
አፓርቴይድ፣..................................................8
ኢሕአፓ፣128, 199, 240, 255, 256, 257, 258, 259, 273
ኢትዮጵያን ሬጂስተር፣..................................73
ዓምደ ሚካኤል፣..............................133, 154
ዓምደ ሚካኤል ደሳለኝ፣..........................133
ዓየር መንገድ፣ ................................10, 135
እሙን፣ ...........................................7, 172
አቴጌ መነን ትምህርት ቤት፣ ....................75
እንግሊጣር፣ ......................................40, 44
እግዚአ-ደሀነት፣ ........................................49
ክበደ ሚካኤል፣..............................133, 154
አለቃ ታምራት፣ ...........................................7
ካህናት፣........................................53, 55, 71
ካሣ ወልደ ማርያም፣....................................12
ኩበረ ነገሥት፣ ....................................113, 228
ከትፎ፣..........................................................16
ኮንሶ፣ ..........................................................38
ወይዘሮ ገነት ወልደ ገብርኤል፣............155
ዋለልኝ፣ ..............................................19, 257
ዘርዓ ያዕቆብ፣...............................................14
ዘርዓይ ደረስ፣............................3, 135, 136
ዝናር፣...........................................................20
የመላው ኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ንቅናቄ፣30
የሠለጠነው ዓለም፣.......................................22
የሶቭየት ኅብረት፣.......................................92
የቤተ እሥራኤል፣ ......................................141
የቤት ግንባታ፣ ...........................................21
የትምህርት ታክስ፣......................................53
የነቢትወደድ ነጋሽ፣....................................28
የአብሮነት መንግሥቱ፣ ..............................29
የአገር ፍቅር፣ .............................................113
የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ፣...30
የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር፣............30
የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር፣............30
የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር፣ ...........30
የኢትዮጵያ ዓየር ኃይል፣.........................10
የኢትዮጵያ ዓየር መንገድ፣ .......................10

የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማኅበር፣ ...........30
የኢትዮጵያ ታሪክ9, 68, 90, 91, 110, 135, 150, 164, 172, 176, 248, 262
የኢትዮጵያ የዓየር ኃይል፣......................88
የኢጣልያ ወረራ፣....7, 82, 145, 193, 241
የዓየር ኃይል፣ ...............41, 42, 83, 240
የክብር ዘበኛ፣ ......................41, 240, 252
የውስጥ አርበኛ፣...........................72, 154
የጁ፣ ..................................................38
የጦር ሠራዊት፣ ......................41, 42, 86
ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣ .....47, 134, 227, 251
ዩጋንዳ፣ ..............................................10
ዮሐንስ ረምሀ፣ .................................155
ዮሐንስ ረምሐ፣.......................72, 155
ደሀነት፣49, 50, 52, 94, 97, 98, 101, 156, 250
ደርግ-ኢሠፓ፣........................................128
ደብረ ማርቆስ፣.......................................131
ደጃዝማች ሁብተ ማርያም፣..................144
ደጃዝማች መሸሻ ተወንድ በላይ፣........144
ደጃዝማች ማሞ ኃይለ ሚካኤል፣ .......144
ደጃዝማች በየነ፣.........................136, 145
ደጃዝማች ባልቻ፣...................................145
ደጃዝማች ታከለ፣ .................................28
ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት፣ .....133
ደጃዝማች ትከሉ መሸሻ.......................143
ደጃዝማች አበራ ካሣ................፣132, 158
ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉ፣ ..................145
ደጃዝማች እያሌው ብሩ፣..........144, 145
ደጃዝማች ዓመዴ፣.................................144
ደጃዝማች ከበደ ተሰማ፣......................245
ደጃዝማች የማነ ሀሰን፣.........................85
ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣.........................28
ደጃዝማች ግርማቸው፣ ......133, 134, 153
ዳቦ16, 74, 75, 77, 97
ዳዊት ዕቁበ እግዚእ፣.........................133
ዶላር፣............................................33, 109
ጀኔራል መኮንን ደነቀ፣ .......................30
ጁልየስ ኒየሬሬ፣.....................................48
ጂሩ፣ ....................................................38
ጃፓን፣.......................................66, 117
ጀኔራል ኃይሉ ለገሰ፣............................86
ጀኔራል መርዕድ፣ .......................28, 240
ጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ፣ ...........28, 40
ጀኔራል መኮንን ደነቀ፣.........................133
ጀኔራል አማን፣ ..............................42, 86
ጀኔራል ከፈለኝ ይብዛ፣..........................7
ጆርጅ ማጎምቤ፣ .....................................10
ገሪማ ታፈረ ..........................................116
ገብረ ወልድ እንግዳ ወርቅ፣..................133
ገነት ዘውዴ፣ ...............................10, 253
ገንዎ፣ ...................................................16
ገዢው መደብ፣ ......................................28
ግሪኮች፣ .......................................35, 110
ግርማቸው ተከለ ሐዋርያት፣.......133, 134
ግብጽ፣ ...............................48, 91, 110
ጎንደር፣.........................121, 123, 139, 156
ጎጃም፣.82, 121, 122, 123, 138, 144, 148
ጥላቻ፣56, 60, 101, 112, 150, 170, 174, 175, 178, 232, 239
ጳውሎስ ኞኞ፣ ..............82, 116, 137, 143
ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ፣ ሀብተ ወልድ..83
ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ወልድ እንግዳ ወርቅ፣ 30
ጸጋዬ ገብረ መድኅን፣...........................67
ፊታውራሪ ሣህሉ ወልደ ገብርኤል፣....144
ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ፣.....................144
ፊታውራሪ ተከለ ሐዋርያት፣ .........29, 241
ፍሥሐ ተገኝ፣ .......................................87
ፍትሐ ነገሥት፣.....................................113
ፐሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ፣ ......................39
ፓሪስ ዩኒቨርሲቲ፣..........................40, 63



ይደመቆ በተባለ ተራራ በሰኔ ወር 1932 የተነሳ ፎቶግራፍ

---

ከግራ ወደ ቀኝ መሃል ዝቅ ብለው የተቀመጡት ማሞ ሥዩም (በኋላ ደጃዝማች)፤ ከፍ ያለ ወንበር ላይ የተቀመጡት ግራዝማች ተሾመ ሸንቁጥ (በኋላ ደጃዝማች)፤ አጠገባቸው ወንበር ላይ የተቀመጡት ልጅ አበበ ሸንቁጥ (በኋላ ደጃዝማች)፤ አጠገባቸው ልጅ ተድላ መኮንን (በኋላ ሜ/ጀነራል)፤ ከሳቸው ላይ የቆመው ሕጻን ዓለማየሁ አበበ (በኋላ አምባሳደር)። ከግራዝማች ተሾመ ሸንቁጥ ጀርባ ወጣት ጫንያለው ተሾመ (በኋላ አምባሳደር)። ፊት ለፊት መሬት ላይ ከተቀመጡት መሃል ምልኬ ጨፋ (በኋላ ግራዝማች) በቀኝ ከሳቸው አጠገብ አጋፋሪ ሽሽጉ። ከጀርባ ከቆሙት መካከል ይታገሱ ጠጋው መታፈሪያ አዲሴ ካሣ የሚባሉ አሉበት።

ዋጋ69.00ብር

ግራፊክ አታሚዎች